ፍኖተ
# ነፃነት
ሁለተኛ ዓመት ቅጽ 2 ቁ. 43 | ዋጋው፦ 6 ብር | ፍኖተ ነፃነት ማክሰኞ ግንቦት 21 ቀን 2004 ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ሕዝብ የሉዓላዊ ሥልጣኑ ባለቤት እንዲሆን እንታገል!

## 10ሩ የድህረ-ግንቦት 20 ኪሳራዎች 2



## መለስ ኢትዮጵያን እንዴት እየመራት ነው? 3

## አቶ መለስ በደቡብ አፍሪካ ሊያደርጉት የነበረው ንግግር በተቃውሞ ተሰረዘ 13



## የቀበሌ ክበባት የማናቸው? 8

## በአንድነት ፓርቲ እና ኢቴቪ መካከል ለተመሰረተው ክስ ለብይን ተቀጠረ

አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍተህ (አንድነት) ፓርቲ "አኬልዳማ" በሚል ዘጋቢ ፊልም ስሜን አጥፍቷል በሚል በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እና ጋዜጠኛ አብዲ ከማል ላይ ክስ መመስረቱ ይታወቃል::

የፌዴራል መየመጀመሪያ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 9ኛ የፍትሐብሔር ችሎት ጉዳዩን እያየው ያለ ሲሆን ተከሳሽ ኢቴቪ በበኩሉ ጉዳዩ በከፍተኛ ፍ/ቤት በነአንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ እየታየ መሆኑን በመጠቀም ተቃውሞ ማቅረቡ ይታወሳል፡፡

ወደ ገፅ 8 ይዞራል....

## ወ/ሮ አዜብ መስፍን መሬት መውሰዳቸውን ያጋለጠው ሠራተኛ ታሰረ 13

## ጥቅምት 23፣ መስከረም 2 እና ግንቦት 20 4

**አምባገነኑን የኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም ወታደራዊ መንግስት ከከፍተኛ መስዋዕትነት በኋላ ያስወገደው ህውሓት/ኢህአዴግ፤ አምባገነኑን የአቶ መለስ ዜናዊን ስርአት ከማስቀመጥ ያለፈ ታሪክ አልሰራም የሚለው የነብዩ ኃይሉ ዳሰሳ የግንቦት 20ን ኪሳራዎች ይዘረዝራል፡፡**

# 10ሩ የድህረ-ግንቦት 20 ኪሳራዎች



ነብዩ ኃይሉ

አቶ መለስና ጓደኞቻቸው አምባገነን ስርአትን ለመቀየር ነፍጥ አንስተው፣ በጭቆና ላለመኖር ሲሉ በህይወታቸው ተወራርደዋል፤ አላማቸውን ለማሳካት ገድለዋል ሞተዋል፡፡ ድል ቀንቷቸው የዛሬ 21 አመት አምባገነኑን የደርግ ስርአት አስወግደው ምኒሊክ ቤተመንግስት ሲገቡ ኢትዮጵያን በለውጥ ጎዳና ሊመሩ፣ ዴሞክራሲን በማስፈን በሀገሪቱ አዲስ ታሪክ እንዲያኖሩ የሚያስችል ዕድል ነበራቸው ፡ ፡ አምባገነኑን የኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያምን ደርግ ካስወገዱ በኋላ ግን አምባገነኑን የአቶ መለስ ዜናዊን ስርአት ከማስቀመጥ ባለፈ በግንቦት 20 ድል ታሪክ ሊሰሩ አልቻሉም፡፡


ያ ሁሉ መስዋዕትነት የተከፈለበት፣ በተለያዩ ጎራዎች የተሰለፉ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን ህይወት ዶጋ አመድ አድርጎ ግንቦት 20, 1983 ዓ.ም የተቋጨው ጦርነት አንድን ወታደራዊ አምባገነን መሪ በኃይል በማስወገድ የይምሰል ዴሞክራሲያዊ ስርአትን(pseudo democracy) የገነባ ሲቪል አምባገነን መተካት የተወሰነ ቡድንን ወይም ግለሰቦችን ፖለቲካዊ የበላይነት(hegemony) ለማረጋገጥ ያለመ እንዳልነበር በትጥቅ ትግሉ ተሳታፊ የነበሩ ግለሰቦች ያረጋግጣሉ፡፡ የህወሓት ነባር ታጋይና የቀድሞው የትግራይ ክልል ፕሬዝዳንት አቶ ገብሩ አስራት ሰኔ 19,2002 ለወጣችው አዲስ ፕሬስ ጋዜጣ አሞራው ስለተባለ የህወሓት ጀግና ታጋይ ሲያስረዱ «አሞራው ቀና ብሎ እየተደረገና እየሆነ ያለውን ነገር ቢያይ ይገርመው ነበር» ካሉ በኋላ የአቶ መለስ መንግስት በአሞራውና በሌሎች ታጋይ ሰማእታት መስዋዕትነት ስልጣን እየነገደ መሆኑን አብራርተዋል፡፡

ህወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን የያዘበት ተመሳሳይ ወቅት አምባገነናዊ ኮሚኒስት ስርአቶችን በማስወገድ ዴሞክራሲያዊ ግንባታ የጀመሩት የምስራቅ አውሮፓ ሀገራት በአጭር ጊዜ ውስጥ አመርቂ ለውጥ ማምጣታቸውን Carleton University፡ Institute of European and Russian Studies አጥኚ የሆኑት ድራጎስ ፖፓ (DRAGOS POPA) ሮሜኒያንና ቡልጋሪያን ነቅሰው ያመላክታሉ፡፡ የባልካን ሀገራትም ሁለት አስርት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ዴሞክራሲያዊ እምርታ ማምጣታቸውን The democratic transformation of the Balkans በሚል ርዕስ የቀረበው የሮዛ ባልፈር እና ኮሪና ስትራቱላት (Rosa Balfour and Corina Stratulat) ጥናት ያመላክታል፡፡ ጥናቱ የባልካን ሀገራት በአጭር ጊዜያት ውስጥ ሶስት መሰረታዊ ለውጦችን ማስመዝገባቸውን ያስረዳል«ከጦርነት ወደ ሰላም፣ ከኮሚኒዝም የእዝ ኢኮኖሚ ወደ ነፃ ገበያ እንዲሁም ከአንድ ፓርቲ አገዛዝ ወደ መድብለ ዴሞክራሲ ተለውጠዋል» ይላል፡፡ በዚህ ረገድ በኢትዮጵያ ባለፉት 21 አመታት የታየውና አሁንም ያለው ነባራዊ ሁኔታ ለግንቦት 20 ድል የወጣውን የህይወት ግብር እና በድሉ ማግስት የተገኘውን የግንቦት 20 ፍሬ ስናወራርድ ውጤቱ ኪሳራን የሚያመላክት ነው፡፡

ይህ ጽሁፍ በህወሓት በስተመጨረሻም በህወሓት/ኢህአዴግ መሪነት ለ17 አመታት በተደረገው ፅኑ ትግል የተገኘው የግንቦት 20 ድል ሊያመጣ ያልቻላቸውን አስር አንኳር ነጥቦች ይፈትሻል፡፡

## ፩
## ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን መገንባት ያለመቻሉ

ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ግንባታ በሂደት ውጤት የሚያስገኝ ጥረት ነው፡፡ ጤናማ ሂደት እስከኖረ ድረስም የግንባታው እድገት አይቀሬ ውጤት ነው፡፡ ዛሬ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታቸው ምሳሌ የሚሆኑት ሀገራት በቅፅበታዊ ለውጥ/ክስተት ካሉበት ደረጃ ላይ አልደረሱም፡፡ ከ1983 ግንቦት 20 ወዲህ ኢትዮጵያ በዴሞክራሲያዊ ስርአት ግንባታ ሂደት ውስጥ መግባቷን የአቶ መለስ መንግስት ሲናገር ይደመጣል፡ ፡ ሆኖም ሂደቱ አንዴ ወደ ፊት ሌላ ጊዜ ደግሞ ወደኋላ ሲንሸራተት ቆይቶ በአሁኑ ጊዜ ተኮላሽቷል፡፡ ምርጫ




ቦርድም ሆነ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ወይም የእንባ ጠባቂ ተቋም በኢህአዴግ «ሞተር» የሚንቀሳቀሱ፣ በመንግስት ሳምባ የሚተነፍሱ በህዝብ አመኔታ የሌላቸው የስም ዴሞክራሲያዊ ተቋማት ናቸው፡፡ የአቶ መለስ መንግስት በ21 አመት የስልጣን ዘመኑ ዴሞክራሲያዊ ተቋማትን ለመገንባት አለመድፈሩ/አለመፈለጉ የድህረ ግንቦት 20 ኪሳራ ማሳያነው፡፡

## ፪
## ከተፅዕኖ ነፃ የሆኑ የፍትህ አካላትን መገንባት አለመቻሉ

በኢትዮጵያ ለህግ የሚሰጠው ቦታ ከፍ ያለ ነው፡ ፡ ህግን የማክበር እና ለፍትህ አካላት አመቴታና ክብር የሚሰጥ ባህላዊ መሠረትም አለ፡፡ ይህ ባህላዊና ሞራላዊ መሠረት በተለይ ከደርግ መንግስት ስልጣን መያዝ በኋላ የመሸርሸር ምልክት ማሳየት ጀመረ፡፡ “የደርግ ሹማምንት በፍትህ አካላት ላይ የተለያዩ ጫናዎችን በማሳደር ፍርድን ለማጣመም ጥረት ያደርጉ ነበር” የሚሉት አቶ አለማየሁ አዱኛ በህግ አማካሪና ጠበቃነት ይሰራሉ፡፡ አቶ አለማየሁ እንደሚሉት ከመንግስት አካላት ጫና ቢኖርም የፍትህ አካላቱ ከነበራቸው ጠንካራ መሠረት አንፃር ነፃነታቸውን ያስደፈሩ አልነበሩም፡፡ ይህ ሁኔታ የደርግ ባለስልጣናት ለሚወስዷቸው እርምጃዎች ህጋዊ ከለላ ከመስጠት ይልቅ ግልጽ ፖለቲካዊ እርምጃ ይወስዱ ነበር፡፡ የደርግ አምባገነንነትና ጨፍጫፊነት አጠያያቂ ባይሆንም እነዚህ ህገወጥ እርምጃዎች የሚወሰዱት በማናለብኝነት በተወጠሩ ባለስልጣናት “የጐበዝ አለቆች” እንጂ በፍትህ አካላት አልነበረም፡፡ ህወሓት /ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ግን ሁሉንም ተቋማት በአንድ የፖለቲካ አስተሳሰብ የማጥመድ አባዜ የፍትህ አካላትንም አልተወም፡፡ ፖሊስ፣ አቃቤ ህግ እና ፍርድ ቤቶች ከመጋረጃ ጀርባ በኢህአዴግ ባለስልጣናት የሚሰጡ ፖለቲካዊ ውሳኔዎችን “በህግ” ስም ያስተላልፋሉ፡፡ ኢህአዴግ እራሱ ያፀደቀውን ህገ መንግስት በመጣሱ የፍትህ አካላትን ነፃነት ከመጋፋት ባለፈም፣ ፖለቲካዊ ተፅዕኖ የሚያደርሱ አፋኝና ኢፍትህዊ «ህጐችንም» በማፅደቅ ፍትህንና ህጋዊ ስርዓትን የሚያዋርዱ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ ግንቦት 20 ነፃ የፍትህ አካላት እንዲለመልሙ አለማድረጉ ሌላው የድህረ-ግንቦት 20 ኪሳራ ነው፡፡

## ፫
## ብሔራዊ ስሜትን መናዱ (ኢትዮጵያዊነት ማኮሰሱ)

ብሔራዊ ስሜት መናድ ለአንድ ሀገርና በውስጧ ለሚኖሩ ዜጎች ደህንነት አደጋን ይደቅናል፡፡ የኢህአዴግ መንግስት ኢትዮጵያዊነት የሚንዱና ጎጣዊ ማንነት ላይ የሚያተኩሩ ፖለቲካዊ እሳቤዎችን በህዝቡ ውስጥ እንዲዘሩና እንዲስፋፉ ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል፡፡ የኢትዮጵያን ጥንተ ታሪክ በመካድ ህዝቦች በግድ የተጠፈሩባት «የአጤ ምኒሊክ ፍጡር» አድርገው ያስቀምጧታል፡፡ ይህ አስተሳሰብ ህወሓት ስልጣን ላይ ሳይወጣ ያራምደው እንደ ነበር ግልፅ ነው፤(የኤርትራ ህዝብ ትግል ከየት ወዴት 1979ን ልብ ይሏል) የአስተሳሰቡ መነሻ የኢትዮጵያን ጥንተ ታሪክ በመካድ ቢነሳም መጨረሻው የራስን እድል በራስ መወሰን እስከ መገንጠል የሚል ክፉ ድምዳሜ ላይ የሚያደርስ ነው፡፡ ይህ የፀረ ኢትዮጵያዊነት ውጤት በኢህአዴግ የስልጣን ዘመን መጀመሪያ ኤርትራን በማስገንጠል ተጀምሮ በ1987ቱ ህገ-መንግስት አንቀፅ 39ን በማካተት መሰረቱን አጠናከረ፡፡ ከኤርትራ መገንጠል በኋላ በተነሳው የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጦስ ከሁለቱም ሀገራት «ወደ ሀገራቸው› የተሸኙ ዜጎችን ሰቆቃ ለተመለከተ፣ የተሳሰረን ህዝብ «የራስን እድል በራስ በመወሰን» ሰበብ መነጠል የሚያመጣውን ስነልቦናዊ፣ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጦስ ለማገናዘብ አይቸግረውም፡፡ ሆኖም ኢህአዴግ አደገኛ አስተሳሰቡን ለማረቅ የሚፈልግ አይመስልም፡፡

የአቶ መለስ መንግስት አራምዳለሁ ለሚለው «የልማታዊ መንግስት» ፍልስፍና ብሔራዊ ስሜት የጎላ ሚና እንዳለው ምሁራን የተለያዩ ሀገራትን ልምድ በመጥቀስ ያስረዳሉ፡፡ በዚህ ተፋልሶ ውስጥ የሚዋትተው የአቶ መለስ ኢህአዴግ ከኢትዮጵያዊነት ጋር መላተሙ ሌላው የድህረ-ግንቦት 20 ክስረት አመላካች ነው፡፡

## ፬
## የብሔር ጥያቄ ምላሽ አለማግኘቱ

በ1960ዎቹ የተማሪዎች ንቅናቄ ይስተጋቡ ከነበሩ የፖለቲካ ጥያቄዎች ውስጥ የብሔር ጥያቄ አንደኛው ነው፡፡ ኢህአዴግ ይህን ጥያቄ እንደ ሰንደቅ አንስቶ የብሔረሰቦችን እኩልነት እንዳረጋገጠ ይናገራል፡፡ የብሔር እኩልነት የግንቦት 20 ፍሬ እንደሆነም ደግሞ ደጋግሞ ለማሳመን ጥሯል፡፡ ሆኖም ከግንቦት 20 በኋላም ተገፋን ተጨቆንን የሚሉ የብሔር ቡድኖች በየምክንያቱ ብቅ ብቅ ማለት ቀጥለዋል፡፡ ኢህአዴግ በቋንቋ ከመማርና ከመዳኘት ባለፈ ብሄረሰቦች ራሳቸውን የምር እንዲያስተዳድሩ የሚፈልግ አይመስልም፡፡ አቶ ገብሩ አስራትም በኢትዮጵያ የብሔረሰቦች መብት እንዳልተከበረ ያምናሉ፡፡ አቶ ገብሩ «ህወሓት ከጋርዮሽ አመራር ወደ አንድ ሰው ብቸኛ መሪነት» በሚለው ፅሁፋቸው ብሔሮች በአካባቢያቸው ጉዳይ ፖለቲካዊ ስልጣን ኖሯቸው እንደማይወስኑና በአካባቢያቸው ኢኮኖሚያዊ ልማት ተጠቃሚ እንዳልሆኑ ያስረዳሉ፡፡ ለዚህም ይመስላል ከህወሓትና ከፌደራል መንግስት የሚወከሉ አካላት

ወደ ገፅ 15 ይዞራል....



# ሰማዕታቱ ቀና ብለው ያዩት የቴሌቪዥንዋን ‹‹ ኢትዮጵያ ›› ነው



ኃይሉ አርአያ (ዶ/ር)

አቶ ሴኮቱሬ የኢህአዴግ የሕዝብና የውጭ ግንኙነት መምሪያ ኃላፊ ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓም ባወጣው ሰንደቅ ጋዜጣ ላይ ግንቦት 20ን አስመልክቶ ሰፋ ያለ የጥያቄና መልስ ውይይት አካሂደዋል፡፡ በውይይቱ ሂደት መጨረሻ ገደማ ጋዜጠኛው የሚከተለውን ጥያቄ ጠየቃቸው?፡-

« እስካሁን የተጓዛችሁበት ረጅም መንገድ አለ፡፡ በዚህ ረጅም ጉዞ ውስጥ ብዙ መስዋእት የሆኑ ዜጎች አሉ፡፡ እነዚያ በመስዋእትነት ያለፉት ጓዶች በአጋጣሚ ከሞቱበት የመንቃት እድል ቢገጥማቸው እስካሁን የተጓዛችሁበትን ጠንካራና ደካማ መንገዶች እንዴት የሚመለከቱት ይመስለዎታል ?»

አቶ ሴኮቱሬ ሲመልሱ፡- «እርግጥነው በርካታ ወጣቶች፣ ሕዝቦች ይህን ሥርዓት ለማምጣት ተሰውተዋል፡፡ ሰማእታቱ ቀና ብለው የማየት እድሉ ቢኖራቸው በአብዛኛው የሚደሰቱ ይመስለኛል» አሉ፡፡ በመልሱ ማጠር ያልረካ የመሰለው ጋዘጠኛ «እንዴት?» የሚለውን ጥያቄ አስከተለ፡፡ በዚህ ጊዜ ነው አቶ ሴኮ ቱሬ ሰማዕታቱን ያስደስታሉ ያሏቸውን ምክንያቶች መዘርዘር የጀመሩት፡፡ አለፍ አለፍ እያልን የሰጧቸውን ምክንያቶች እንመልከት፡፡

አንደኛው ሰማዕታትን ደስ የሚያሰኛቸው የተባለው የብሔር/ብሔረሰቦች መብት መረጋገጡ ነው ብለዋል፡፡ አቶ ሴኮቱሬ እውን የብሔር/ብሔረሰቦች መብት ተረጋግጧል? በወረቀት ላይ፣ አዎ፡፡ በተጨባጭ ግን ተሟልተው አልተረጋገጡም፡፡ ከተረጋገጡ ለምንድ ነው በአሁኑ ጊዜ የበርካታ ብሔር/ብሔረሰቦች ተወካዮች መብታችንን እናስከብራለን በሚል በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች መሣሪያ አንስተው በመታገል ላይ ያሉት? ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ ከዘጠኙ የሀገሪቱ ክልሎች በስምንቱ ማለትም በኦሮሚያ፣ በሶማሊያ፣ በአፋር፣ በሲዳማ፣ በጋምቤላ፣ በቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ በአማራና በትግራይ ውስጥ መብታችንን እናስከብራለን በሚል መሣሪያ አንስተው እየታገሉ ነው፡፡ በመሀሉም ኢትዮጵያውያንም ሆኑ የውጭ ዜጎች እየሞቱ ነው፡፡ ንብረት እየወደመ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ የቅሬታ እንቅስቃሴ የሌለው በሐረሪ ክልል ብቻ ነው፡፡ የብሔር/ብሔረሰብ መብቶች ከተከበሩ፣ ደም አፋሳሽ የእርስ በርስ ግጭት ለምን ይከሰታል? ዛሬ በትግራይ የቀድሞ ተጋዮች በታገሉባቸው በረሀዎች ሌሎች የትግራይ ወጣቶች መሣሪያ አንስተው እየታገሉ ናቸው፡፡ ለምን?

ሁለተኛው ለሰማዕተቱ መደሰት ምክንያት ኢትዮጵያ የዴሞክራሲያዊ አገር መሆንዋ ነው፡፡ «ሀገራችን የብሔር/ብሔረሰቦች መብቶች የተረጋገጡባት ዴሞክራሲያዊ ሀገር ሆናለች» ነው ያሉት? አቶ ሴኮቱሬ ፓርላማው 99.6 በመቶ በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ሥር በሆነበት፣ አስፈፃሚ አካል አለአግባብ ጡንቻውን አፈርጥሞ ሁሉን ተቆጣጣሪና አዛዥ በሆነበት፣ ፕሬስና ሲቪክ ማህበራት በአሳሪና አስፈሪ ሕጎች ተጠፍረው በተሽመደመዱበት፣ ሕዝቡ በፀረ-ሽብርተኝነት ሕግ ተጨብጦ በፍርሀት ድባብ ውስጥ በሚኖርበት ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ ነው የሚባል ሀገር ሊኖር አይችልም፡፡

ሦስተኛው ሰማዕታትን የሚያስደስተው ጉዳይ የሀገራችን « ከድህነት የመላቀቅ ተስፋ ይዛ በልማት ጎዳና ወደፊት እየገሰገሰች መሆንዋ ነው»፡፡ ይላሉ አቶ ሴኮቱሬ፡፡ ቁሳዊ ልማት ይታያል? መንግሥት የካፒታል አቅሙን እየገነባ ነው? በዚያውም የጥቂት ደጋፊዎቹን እያበለፀገ ነው፡፡ ጥቂት በሀብት ሲንሩ ብዙሃኑ እየደኸዩ ነው፡፡ በቀን ሦስት ጊዜ ትበላለህ የተባለ ሕዝብ በቀን አንድ ጊዜም መብላት እያቃተው ነው፡፡ ወደፊት መገስገስ እኮ በሕዝቡ ቁሳዊና መንፈሳዊ ህይወት ውስጥ በጎ ለውጥ ማምጣት አለበት፡፡ ያ የተዋሀደ ቁሳዊና መንፈሳዊ ለውጥ በሕዝቡ የእለት ተእለት ኑሮ እያየነው አይደለም፡፡ ከሌሎች አገሮች ጋር ስንነፃፀር የድህነት ተርታችን ሁሉ ጊዜ ወደ መጨረሻ ነው፡፡ በባሰ ድህነት የሚበልጡን አገሮች በጣም ጥቂት ናቸው፡፡ በቁጥር (ስታቲስቲክስ) እየገሰገስን የማንገሰግስ፣ እየሄድን የማንሄድ መሆናችን የዘመናችን እንቆቅልሽ ነው፡፡

አራተኛው ሰማዕታትን ያስደስታል የተባለው « የሀገራችን አርሶ አደሮች በልማት ውስጥ በሰፊው እየተሳተፉ ራሳቸውን ችለው ሀገራቸው ወደፊት እያራመዱ መሆናቸው» ነው፡፡ በቅድሚያ የሀገራችን አርሶ አደሮች ራሳቸውን ከቻሉ በየዓመቱ በሀብታም መንግሥታት ደጃፍ እየዞርን የምግብ ርዳታ የምንለምንባቸው በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ከየት የመጡ ናቸው? የሀገራችን አርሶ አደር፣ ቡና እና ጫት አብቃዩ ሳይሆን፣ በተለይ ተራው አራሹ ያለበትን ሁኔታ ዓለም ያውቀዋል፡፡ ብጣሽ የመሬት ይዞታው፣ የሚጠቀምበት ኋላቀር የአስተራረስ ዘዴ የታወቀ ነው፡፡ ያለበት የማዳበሪያ፣ የምርጥ ዘርና የፀረ-ተባይ ዋጋ ጫና ከየአቅጣጫው የሚመጣበት ማለቂያ የሌለው የገንዘብ መዋጮ ጫና የታወቀ ነው፡፡ አርሶ አደሩ በምን ሁኔታ ላይ እንዳለ ለመገንዘብ ከአዲስ አበባ ወጣ ብሎ ማየቱ ብቻ በቂ ነው፡፡ ለምሳሌ በሰሜን ኢትዮጵያ ሰውም ከብቱም በአብዛኛው በመጎዳቱ የሚረግጠውንና በዙሪያው ያለውን አፈር ይመስላል፡፡ ራሱን ለውጦ አገሩን የሚለውጥ አይመስልም፡፡ ከገጠር ወደ ከተማ የሚጎርፈው ወጣት ገበሬ ለምን ወደ ከተማ እንደሚፈልስ ሲጠየቅ በገጠር መኖር አልተቻለም ነው መልሱ፡፡ ይህም በተለያዩ ጥናቶች የተረጋገጠ ነው፡፡ ራሱን የቻለና አገሩን የሚለውጥ አርሶ አደር በአብዛኛው ከአካባቢው አይፈልስም፡፡ ሰማዕታቱ ቀና ሲሉ ያዩት ኢህአዴግ « የልማት ጀግኖች» እያለ ሜዳሊያ የሸለማቸውን ከሆነ ሌላ ታሪክ ነው፡፡ ምን ያህል እንደሆኑ እናውቃለን፡፡ ገበያውም ይናገራል፡፡ ራሱን ችሎ አገሩን እየለወጠ ያለ ገበሬ ካለ ምርቱ ከፍ ብሎ ሸማቹ ያውቅለት ነበር፡፡ የምግብ እህል ዋጋም ሰማይ ባልደረሰ ነበር፡፡

አምስተኛው ሰማዕታት የሚደሰቱበት የተባለ ምክንያት «በሀገራችን ዴሞክራሲ ሰፍኖ፣ ዜጎች የፈለጉትን አስተሳሰብ በነፃ የማራመድ መብት ተረጋግጦ፣ የተለያዩ ጋዜጦች በየመንገዱ የሚነበቡበት፣ ሃሳቦች በነፃነት የሚንሸራሸሩበት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተደራጅተው አለን የሚሉት ሃሳብ በነፃነት የሚስተናገድበት ሲስተም በመፈጠሩ» ነው፡፡

ከላይ የተመለከቱትንና ዘወትር የሚዘመርባቸው የኢህአዴግ «በረከቶች» ከዚህ በፊት ፈጭተን፣ አቡክተን፣ ጋግረን በልተናቸዋል ሆድ ጠብያላሉ ጉዳዮች ናቸው፡፡ አላጠገቡንም፡፡ ቢሆንም ከተነሱ ዘንዳ እስቲ በሩጫ እንመልከታቸው፡፡ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት መረጋገጥን በተመለከተ በወረቀት ላይ ከሆነ አዎ ተረጋግጥዋል፡፡ በተግባር ያለው ግን ሌላ ነገር ነው፡፡ አሳሪና አስፈሪ የሆኑት የፕሬስና የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጆች እየተጋገዙ የሕዝቡን በመብቱ የመተማመን መሠረት አናግተውታል፡፡ ዛሬ ምን ብንናገር እንደሚያስቀጣና እንደማያስቀጣ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፡፡ ምን በፀረ-ሽብርተኝነት እንደሚያስጠየቅ ወይም እንደማያስጠይቅ ለመለየት አስቸጋሪ ሆኗል፡፡ ሃሳብን በነፃ የመግለጽ መብታችን ተረጋግጧል ብለው የተናገሩ ዜጎች ንግግራቸው እንደተፈለገ እየተተረጎመ ለእስር ተዳርገዋል፡፡ ጉዳት ይደርስብናል ብለው የሰጉ ደግሞ አገር ጥለው ተሰደዋል፡፡

የተለየዩ ጋዜጦች በየመንገዱ መነበብ እንደ አንድ ትልቅ የዴሞክራሲ መግለጫ ተወስዷል፡፡ አባቶች « ዓባይን ያላየ ምንጭ ያመሰግናል» ብለዋል፡፡ ከአንድ ደርዘን ብዙ የማይበልጡ ነፍስ ያላቸው፣ ማለትም ፖለቲካውን፣ ኢኮኖሚውንና ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚዳስሱና የረባ ስርጭት ያላቸው ጋዜጦች በየመንገድ መነበብ በጣም ትንሽ ነገር ነው፡፡ እጅግ በጣም ትንሽ ነገር ነው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ወደ 90 ሚሊየን የሚጠጋ ሕዝብ በአላቸው ሀገሮች ሊኖርዋቸው የሚገባ የጋዜጦች ቁጥር በመቶዎች ቤት ውስጥ ነው መቆጠር ያለበት፡፡ በሀገራችን የጋዜጦች ቁጥርን በተመለከተ በ1980ዎቹ ከነበረው ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር እንኳን እጅግ በጣም ወደኋላ ሄደናል፡፡ ቅድመ ሳንሱር እንደቀረ በይፋ ተነግሯል፡፡ ሆኖም በብርሃንና

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

# መለስ ኢትዮጵያን እንዴት እየመራት ነው?

ሪቻርድ ዳዉደን

መለስ ዜናዊ ለውጭ እንግዶች ሲናገሩ በጣም የተዋጣላቸው ናቸው፡፡ ለሚያስተዳድሯቸው ኢትዮጵያውያን ሲናገሩ ግን እጅግ አስቸጋሪና ገታራ ናቸው፡፡

ባለፈው ጊዜ በካምፕ ዴቭድ የG-8 ሀገራት ስብሰባ ላይ ከሚሳተፉ 4 የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች አንዱ ነበሩ፡፡ እርዳታ ሰጪዎች መለስን ይወዷቸዋል፡፡ እራሳቸውም ብዙ ያነበቡ፤ ሀሳቦችን ሲገልፁ ቁጥሮችን የሚደረድሩና ትኩረት ማድረግ የሚችሉ ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ለብዙ መቶ ዘመናት የኖረች ሀገር እንደመሆኗ እርሷን ማስተዳደር ከብሮክራሲያዊ ስራ የዘለለ ልዩ ጥበብ የሚጠይቅ አይደለም፡፡ እርዳታው ደግሞ ልክ የወንዝ ያክል በዓመት ወደ 4 ቢያንስ ዶላር ይጎርፋል፡፡ በዚያ ላይ መለስ በሶሚሊያና በሱዳን በኩል ባሰማሯቸው ወታደሮቻቸው የአሜሪካ ዘብ ናቸው፡፡ ከቀድሞ አጋራቸውና የቀጠናው አታራማሽ ፕሬዝዳንት ኢሳያስ አፈወርቅ ጋር ባለበት የሚቀጥል ጠላትነት አሏቸው፡፡ አንድ የመለስ ሁኔታ የጨነቀው የአሜሪካ ዲፕሎማት ሰውዬው "የሙባረክ አባዜ" አለባቸው ብለውኛል፡፡ "ለሙባረክ የግብጽን ሚና በቀጠናው ምን እንደሆነ እንጂ ግብጽ ውስጥ ምን (አደገኛ ሁኔታ) እየተካሄደ እንደሆነ ፈጽሞ ልንነግራቸው አንችልም፤ በኢትዮጵያም(አቶ መለስ ዘንድም) ተመሳሳይ ነገር ነው ያለው፡፡

በምርጫ 1997 ዓ.ም ተቃዋሚዎች ዋና ከተማዋ አዲስ አበባን እንዲሁም በሀገር አቀፍ ደረጃ ማሸነፋቸውን ሲያውጁ መንግስት መሪዎቹን ከማሰሩም በላይ በሀገር ክህደት ነበር የከሰሳቸው፡፡ ግማሾቹ ታሰሩ፤ የቀሩት ሀገር ጥለዉ ተሰደዱ፡፡ አሁን ገዢው ፓርቲ ኢህአዴግ 99.6% ድምጽ በማሸነፍ የአንድ ፓርቲ ስርዓት በሀገሪቷ ዘርግቷል፡፡ ባለፈው ሁለት ሳምንት ከአቶ መለስ ጋር በነበረኝ ቃለ መጠይቅ አቶ መለስ በመላ ሀገሪቱ ካሉ መንደሮች ተቃዋሚዎች የተመረጡበትን አንዲት መንደር እንኳ እንደማያውቁ ነግረውኛል፡፡

አንዳንዶች ያልሰመረ አምባገነናዊ ልማታዊነት ነው ይሉታል፡፡ መንግስት የሚለውን ካደረክ ከመንግስት የመሬት የውሃና የአገልግሎት ድጋፍ ታገኛለህ፡፡ ካላደረክ ምንም ታጣለህ፡፡ በህገ መንግስቱ የተደነገጉት የፖለቲካ መብቶች በባለስልጣናት ትእዛዝ ሲጣሱ ይውላሉ፡፡ የሚዲያ ነፃነትማ አይነሳም፤ በቅርቡ በወጣው ህግ መሠረት አታሚ ህገ ወጥ ነው ብሎ ያሰባቸውን ይዘቶች ያለማተም መብቱ እንደሆነ ደንግጓል፡፡ የህትመት ሚዲያው ያበቃለት መሆኑ የሚገባችሁ በኢትዮጵያ ጋዜጣ ማተም የሚችለው ማሽን የተያዘው በመንግስት መሆኑን ስታውቁ ነው፡፡

በ1983 ዓ.ም ስልጣን በኃይል ከያዙ ጀምሮ የአቶ መለስ ትልቁ ስኬት በዝቅተኛ ግብር እንደዚሁም ከክፍያ ነጻ በሆነ መሬት የውጭ ባለሀብቶችን መሳባቸው ነው፡፡ የቻይና ሞዴል በመከተል ባለሀብቶችን በመሳብ ግብርናውንና ፋብሪካዎችን ለማልማት ይሞክራሉ፡፡ አቶ መለስ "ከዚህ በፊት በማርክሲዝም ፍቅር የነደዱ ናቸው በሚል እንተማ ነበር፤ አሁን ደግሞ የቤተሰብ ማንኪያ ለውጭ ባለሀብቶች በመሸጥ እንከሰሳለን፤ ማካካሻ መሆኑ ነው" ብለውኛል፡፡

መለስ ለአበባ እርሻና ለምግብ እህል ከ4 ሚሊዮን ሄክታር በላይ መሬት ለውጭና ለሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ስጥተዋል፡፡ የመብራት ሀይል እንዲያገኙም ግድብ እየገነቡ ነው፡፡ እስከ ዛሬ ከተሰሩ ግድቦችም ከአካባቢ ጋር ተስማሚ እንዲሁም ብዙ የውሃ ትነት የሌለበት ነው ይላሉ፡፡ ነገር ግን ዞሮ ዞሮ ነፃ ገበያ አሟልተው ኢይፈቅዱም፤ ባንክና ቴሌኮም በመንግስት ሞኖፖል ስር ናቸው፡፡ ሁሉም መሬት የመንግስት ነው፤ ይህ በዚህ እንደሚቀጥል መለስ አረጋግጠዋል፡፡

አቶ መለስ «እንከን የማይወጣለት ዲሞክራሲያዊ ስርዓት ገንብተናል? አልገነባንም፤ በእድገት ላይ ያለ ጉዳይ ነው፤ እግራችን የሚሮጠውን ያክል እየሮጠ ነው? አዎ፤ ይህ በአዲስ አበባ ብቻ አይደለም፤ በጣም ኪስ ነው የሚባሉ ቦታዎችም ጭምር ነው፡፡ ካለፉት መንግስታት በተቀራኒ እጅግ አስቸጋሪ ቀጠና ውስጥ የተረጋጋች ሀገር ፈጥረናል፡፡ አሰራራችን የትኛውንም መንደር ይዳስሳል፤ ይህ በኢትዮጵያ ታሪክ አልታየም፤ መንግስት ሩቅና አላስፈላጊ ነበር» በማለት ይናጋራሉ፡፡

አቶ መለስ ከምዕራብ በጎ አድራጊ ድርጅቶች ወቀሳ በተቃራኒ የፖሊሲያቸውን ትክክለኛነት በግትርነት ይከላከላሉ፡፡ እድገታችሁ ከአካባቢ ጋር የማይስማማና ሀገሬውን ከትውልድ ቀየው እንደአልባሌ ነገር (bullshit) በግድ የሚያፈናቅል ነው በሚል የኦክላንድ ተቋም ያወጣውን ሪፖርትም ሙሉ በሙሉ አይቀበሉም፡፡ አርብቶ አደሮች በአርብቶ አደር የሕይወት ዘዬ እንዲኖሩ ሊፈቀድላቸው እንደሚገባ ስነግራቸው ትክክል መሆኑን ቢያምኑም እንኳ አስቀድመው አፍቃሬ ምዕራብ እንደሆንኩ ነግረውኝ ነበር የጀመሩት፡፡

ፖለቲካውም ተመሳሳይ ነው፡፡ በ1983 ዓ.ም ስልጣንን በኃይል የተቆጣጠሩት መለስ ከአናሳ ብሔር እንደመገኘታቸው የመውጫ ቀዳዳ የሚሆናቸውን የትኛውም ብሔር (ብሔረሰብ) የራሱን ነፃነት እንዲያውጅ የሚያስችላቸውን ህግ በህገ መንግስቱ ደነገጉ፡፡ የፖለቲካ ችግር በተከሰተ ቁጥር የትኛውም ብሔር ኢትዮጵያዊነት ማቆም እንደሚችል ይነገራል፤ ነገር ግን በየትኛውም ሁኔታ በህዝብ ድምጽ ተግባራዊ የሚደረግ አይደለም፡፡

አሁን በጋምቤላ ያለው ሁኔታ ኢህአዴግን ምድጃ ላይ ጥዶታል፡፡ በጋምቤላ መሬት ሁሉ ለግብርና አልሚዎች ተሰጥቷል፡፡ ሰዎች ከመሬት በሃይል ስለመፈናቀላቸው አቶ መለስ አያምኑም፡፡ መሬታቸውን የለቀቁት በፍቃዳቸው መሆኑን ለማስረዳት "የጋምቤላ ህዝብ መሬት ባለበት ነው የሰፈረው፤ ደግሞም እርግጠኛ ሁን፤ ከንግዲህ የጋምቤላ ወጣቶች ለማረስ እንጂ ለጥበቃ ወደ እርሻ አይሄዱም" ነበር ያሉኝ፡፡

መለስ የሚመሩት ፈጣን የመንግስት ካፒታሊዝም ይሰራ ይሆን? በቅርቡ አዲስ አበባ በተደረገው የአለም ኢኮኖሚ ፎረም ስብሰባ ወቅት ትችት የመጣው አንደ ከዚህ ቀደሙ ከምዕራባውያን መያዶች አልነበረም፤ የኢትዮጵያ ዋነኛ አጋር ከሆነችው ቻይና ነው፡፡ የቻይና የኢንቨስትመንት ፎረም ተጠሪ የነበረው ጋዎ ዘይፐንግ "እኛ ያደረግነውን የግድ አታድርግ" በማለት አስጠንቅቋቸው ነበር፡፡ ጋዎ ዘይፐንግ "ሰብአዊ ልማትን ያላገናዘበ የኢኮኖሚ እድገት አያስፈልግም፤ እኛ ከአየር መዛባትና፤ የሃብት ኢ-ፍትሃዊ ክፍፍል የተነሳ እየተሰቃየን ነው፤ እናንተ ይህ ችግር ገና አልገጠማችሁም፤ በመሆኑም ያልተነካካ ነጭ ወረቀት በጃችሁ አለ፤ ከማጨማለቃችሁ በፊት ጥሩ ነገር ሳሉበት፡፡" በማለት ምክር ብጤም ጨምሯቸዋል፡፡

በዚህ አይነት ሁኔታ የአፍሪካ መሪን በአደባባይ የወቀሰ የቻይና ባለስልጣን አለ? የውጭ ባለሃብቶችም ደስተኞች አይደሉም፡፡ የኢትዮጵያን እድገት እየመሩ ቢሆንም አሁን ግን በሚገኘው ትርፍ ላይ ከመንግስት ሁሉን ፈላጊነት ጋር ግብግብ መግጠም ግድ ብሏቸዋል፡፡ የአበባ እርሻ ላይ የተሰማሩ ኩባኒያዎች

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ሐምሌ 2003 ዓ.ም ተመሰረተ፡ ፡ፍኖተ ነፃነት በአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት) ስር የሚታተም በፖለቲካዊ፣ በማህበራዊ፣ወቅታዊ ጉዳዮችና በመዝናኛ ላይ የሚያተኩር ጋዜጣ ነዉ፡፡

ጋዜጣችን ሚዛናዊና ነፃ ጋዜጣ ሆኖ ማገልገል መርሁ ነዉ፡፡ ማንኛዉም ሀሳብና አመለካከት የሚስተናገድበትና የሚንሸራሸርበት እንዲሆን እንሻለን፡ ፡ ሰፊ የሚዲያ ሽፋን አለዉ የሚባለዉ ኢህአዴግም በዚህ ሚዲያ አቋሙንና ፖሊሲዉን ለማግለፅ ቢፈልግ መድረኩ ክፍት ነዉ፡፡

ዋና አዘጋጅ፡-
ሰለሞን ስዩም
አድራሻ፡-
የካ ክ/ከተማ ወረዳ 1
የቤት ቁ.028
ስልክ ሞባይል፡- 09 26 81 46 81

አዘጋጆች፡-
ብዙአየሁ ወንድሙ
ስልክ ሞባይል፡- 09 22 11 17 62
ብስራት ወ/ሚካኤል
ስልክ ሞባይል 09 23 11 93 74

አርታኢ፡-
አንዳርጌ መስፍን
ስልክ ሞባይል 09 13 05 69 42


አምደኞች፡-ዶ/ር ኃይሉ አርአያ
ኢ/ር ዘለቀ ረዲ
ቀለሙ ሁነኛዉ
በለጠ ጎሹ
አንዷለም አራጌ
ግርማ ሞገስ
ደረጀ መላኩ
ወንድሙ ኢብሳ

ኮምፒዩተር ጽሁፍ፡-
ብርቱካን መንገሻ
ህትመት ክትትል፡-
ወንድወሰን ከንፈ

አከፋፋይ፡-
ነብዩ ሞገስ
አሳታሚዉ፡-አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ (አንድነት)
አድራሻ፡-አራዳ ክ/ ከተማ ወረዳ 07 የቤት ቁ. አዲስ

አታሚ፡- ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
አራዳ ክ/ ከተማ ቀበሌ 07 የቤት ቁ.984
የዝግጅት ክፍሉ ስልክ፡-01 11249659
ፖ.ሳ. ቁ. 4222
ኢሜይል fnotenetsanet@yahoo.com
ujdparty@gmail.com
andinet@ andinet.org
ፋክስ ቁጥር ፡-+251-111226288

# ርዕስ አንቀፅ




# ጥቅምት 23፣ መስከረም 2 እና ግንቦት 20

ኢትዮጵያ ሀገር ሆና ኖራለች፡፡ ለዚህ ምስክርነት የሚሰጡ ትርጉም ያላቸው ምሁራን ማንሳት ይቻላል፡፡ ከውጭዎቹ ሄኔሪ ክሲንገር፣ ሳሙኤል ሀቲንግተን፣ ዶናልድ ሌቪን፣ ሀሮልድ ማልከስ፣ ጆን አቤኒክ፣ ዶናልድ ክሩ ሜይ፣ ሴፉሩድ ፓውስዋንግን መጥቀስ ይቻላል፡፡ ከሀገር ውስጦቹ ምሁራን ተክለፃድቅ መኩሪ፣ ታደሰ ታምራት፣ መርዕድ ወልደ አረጋይ፣ ባህሩ ዘውዴንና ሽፈራው በቀለን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህና ሌሎች ያልተዘረዘሩ ብዙ ምሁራን ኢትዮጵያውያን በመንግሥት ስር የመተዳደር ልምዳቸው መንግሥት እንኳ ባይኖር ያለመታወክ የሚቆዩ ስርዓት ያዳበሩ ህዝቦች እንዳደረጋቸው ያወሳሉ፡፡ በተጨማሪም በነዚህ ሁሉ ሺህ ዓመታት ኢትዮጵያውያን እንደ ህዝብ ለቁጥር የሚያታክቱ መንግሥታትን እያሳለፉ ኖረዋል፡፡ በህዝብ አዕምሮም በታሪክ ማህደርም ቦታ የሌላቸው ብዙ መንግስታትና መሪዎችም በዚህ መሃል አልፈዋል፡፡


መንግሥታት እና መሪዎቻቸው እንደወራጅ ውሃ ሲያልፉ ‹የማያልፈው› ህዝብ ተመልክቷቸዋል፡፡ እነዚህ የሚያልፍ መሪዎች የሚያልፍ ሃሳቡን ሲጭንባት ተመልክቷል፡፡ ባብዛኛውም መሪዎቹ እነዚህን ሃሳብ ህዝባዊ በማድረጉ አልተሳካላቸውም፡፡ እስቲ የቅርቦቹን ሁለት እና የአሁኑን መንግሥታት ሁኔታ እናንሳ፡-

አፄ ኃይለ ሥላሴ “የተወለድኩበትን ሐምሌ 19 አክብሩ” አሉን፤ `አከበርንላቸውም`፡፡ “ዘውድ የጫንኩበትን ጥቅም 23ንም አክብሩ” አሉን፡ ፡ ደግመንም አከበረንላቸው፡፡ አፄ ኃይለ ሥላሴ አለፉ፤ የሐምሌ 19 እና የጥቅም 23 `በዓላትም` አለፉ፤ ተረሱም፡፡ ደግሞ ደርግ መጣ፤ “የፊውዳሉንና የዘውዱን ስርዓት የገረሰስኩበትን መስከረም ሁለትን አክብሩ” አለን፤ `አከበርንለትም`፡፡ ቆይቶ ደርግ አለፈ፤ መስከረም ሁለትም አብሮት አለፈ፤ ተረሳም፡፡ ኢህአዴግ ደግሞ መጣ፤ “ደርግን የገረሰስኩበትን ግንቦት 20 አክብሩ” አለን፤ እነሆ ‹እያከበርንለት› ነው፡፡ ኢህአዴግ ለጊዜው እንደ አፄውና እንደ ደርግ ስርዓት አላለፈም፡፡ ስለዚህ ግንቦት 20ን “እያከበርን” ነው፡፡

ነገር ግን ፍኖተ ነፃነት ከዚህ አዙሪት የመውጫ ቀዳዳው መፈተሽ እንዳለበት ታምናለች፡፡ እስካሁን ያየናቸው በዓላት ለገዥዎች `አከበርንላቸው` እንጂ የኛ አድርገን በኔነት አላከበርንም፡፡ በመሆኑም ዋናው መፍትሄ ገንዘብ እየከፈሉ አሊያም እያስፈራሩ ካሜራ ፊት አቁሞ የማያምኑትን እንዲያወድሱ ከማድረግ ዴሞክራሲያዊና ፍትሃዊ ስርዓት ገንብቶ መሪዎች ሲያልፉም ሲከበር የሚኖር በዓል መፍጠር ነው፡፡

**ጋዜጣችንን “ፍኖተ ነፃነት“ ብለናታል “ፍኖት“ ማለት መንገድ ማለት ሲሆን ከነፃነት ጋር ሲጣመር የነፃነት መንገድ ማለት ነው፡፡**

# አሳሳቢው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ሁኔታና የባንጁል ውሳኔ



መ/ር ደረጀ መላኩ

የአፍሪካ ኮሚሽን ወይም የአፍሪካ ሰብአዊና የህዝቦች መብት ኮሚሽን እ.ኤ.አ ከአፕሪል 18 ሜይ 2,2012 ባንጁል ጋምቢያ ላይ አድርጎ በነበረው ጉባኤ የአምባገነኑን የወያኔ ስርዓት የሰብአዊ መብት አያያዝ በእጅጉ ኰንኖት አልፏል መኰነን ብቻ አልነበረም ውሳኔም በማሳለፍ ነበር የ15 ቀናት ጉባኤውን የቋጨው፡፡

የአፍሪካ ሰብአዊና የህዝቦች መብት ኮሚሽን በአፍሪካ የሰብአዊ መብቶች በአምባገነን ገዢዎች እንዳይገፈፉ በእጅጉ የሚደክም ተቋም ሲሆን በአፍሪካ ቻርተር አንቀጽ 1 ላይ የሰፈረውን የመኖር መብት ሁሉም የአፍሪካ ሀገራት አገዛዞች እንዲያከብሩ ተማፅኖውን ከማሰማት ወደኋላ ያለበት ጊዜ የለም ማለት ይቻላል፡፡

ከዚህ ባሻገር አባል ሀገራት በአፍሪካ ቻርተር አንቀጽ 5,6,7 እና 9 የሰፈሩት አንቀጾች እንዲያከብሩ በጉባኤው ላይ መክሯል፡፡ በተለይ የማሰቃየት ተግባር እንዲቆም የሮቢን ደሴት መመሪያ (Robin island Guide lines) እና የፕሬስ ነፃነት በአፍሪካ እንዲከበሩ እንዲሁም ነፃና ገለልተኛ የፍትህ ስርዓት በአፍሪካ እውን እንዲሆኑ በ51ኛው የባንጁል ጉባኤው ላይ ካነሳቸው አበይት ቁም ነገሮች መካከል ዋና ዋናዎቹ ነበሩ፡፡

51ኛው የባንጁል ጉባኤ ከአስራ ሁለት ቀናት በላይ የየሀገሩን የሰብአዊ መብት አያያዝ በእጅጉ ከመረመረ በኋላ የእነ ሞሪሽስ፣ ጋና እና የመሳሰሉትን ሀገራት የሠብአዊ መብት ሁኔታ አመስግኗል፡፡ የአንዳንድ ሀገራት የሠብአዊ መብት አያያዝ ሁኔታ ደግሞ በጣም አሳሳቢ እንደሆነ ጠቅሷል፡፡ ከእነዚህ ሀገራት መካከል ኢትዮጵያ አንዷ እና ዋነኛዋ ነበረች፡፡

የኢትዮጵያን ህዝብ ወደ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እየዶሉት የሚገኙትና ላለፉት ሃያ አመታት በትከሻችን ላይ የተቀመጡት ገዢዎች የሰብአዊ መብት አያያዛቸው ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ ስለ መምጣቱ አፍሪካውያንን ሳይቀር እጅግ ማሳሰቡ የባንጁል ውሳኔ ምስክር ነው፡፡ በሌላ በኩል የሰብአዊ መብት አያያዝ ሪኰርዳችን ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ሁሉ ዝቅ ብሎ የመገኘቱ ሁኔታ በእውነቱ በእጅጉ ያሳምማል፡፡ ለማንኛውም 51ኛው የባንጁል ጋምቢያ የአፍሪካ ኮሚሽን “በኢትዮጵያ የሠብአዊ መብቶች ሁኔታ” በሚል ርእስ ያወጣውን መግለጫ አለፍ አለፍ አድርጌ ለመቃኘት እሞክራለሁ፡፡

ሀ. በጣም የሚያሳስበን (deeply concerned)

የባንጁል ጉባኤ በኢትዮጵያ አንዳንድ የእስር ቤቶች በተለይ በዝነኛው የማእከላዊ የወንጀል ምርመራ ቅጥር ጊቢ ውስጥ ያለው የእስረኞች አያያዝ በእጅጉ ያሣስባል አንዳንድ የፖለቲካ ሰዎች ይታሰራሉ፤ መታሰር ብቻ አይደለም የጭካኔ ተግባር ይፈፀምባቸዋል (ይደበደባሉ)፡፡

ለ. በተጨማሪ የሚያሳስበን (further concrned)

የፖለቲካ እስረኞች በገለልተኛ የመብት ተሟጋቾች፣ ወይም በህግ ባለሙያቸው አሊያም በአንዳንድ ቤተሰቦቻቸው በየጊዜው ሊጎበኙ ባለመቻላቸው እስረኞች ሊሰቃዩ ይችላሉ የሚለውን ጥርጣሬ ያጐላዋል ብለዋል የባንጁል ጉባኤ ታዳሚዎች፡፡

የሠብአዊ መብት ተሟጋቾች በሌላ እርስ የሚከተለውን በአፅንኦት ገልፀዋል፡፡

ሐ. በጣም የሚያሳስበን (deeply concerned) በሚል ርእስ ስር በኢትዮጵያ ያልታወቁ እስር ቤቶች (unofficial & ungazetted places of detention) እንደሚገኙ በጉባኤው ውሳኔ ተገልፆል፡፡ እንደ ባንጁሉ ጉባኤ ከሆነ በጦር ካምፖች በግል ህንፃዎች ውስጥ ታሳሪ ዜጎች ስቃይ ይቀበላሉ፡፡ ለምን ገመናዩ ወጣ ብለው ቡራከረዩ ይሉ ይሆን?

መ. እጅግ በጣም አሳሳቢ (Gravely alarmed)

በሠላማዊ የፖለቲካ ትግል ስልት ሥርዓቱን ለመለወጥ በግንባር ቀደም ተዋናይ የሆኑ ሠላማዊ ታጋዮችንና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብትን በመጠቀም ስርዓቱን የተቹ ጋዜጠኞችን በአሸባሪነት መወንጀል እጅግ በጣም አሳሳቢ መሆኑን ጉባኤው መክሯል፡፡

ከዚህ ባሻገር የኢትዮጵያ ጌቶች የሰብአዊ መብት አስከባሪዎች እንደ ልብ መንቀሳቀስ እንዳይችሉ በአዲሱ የበጎ አድራጐት ህግ አንቀው በመያዛቸው እና ጣልቃ በመግባታቸው እንዲሁም የሰብአዊ መብት ገፈፋ የደረሰባቸው ሰዎች ለሚመለከተው ክፍል እንዳያመለክቱ እንቅፋት በመሆናቸው በእጅጉ ተኰንነዋል፡፡

በመጨረሻም የባንጁሉ ጉባኤ ለኢትዮጵያ መንግስት በሚል ለገዢዎቻችን የተማፅኖ ጥሪ አቅርቧል፤ የተማፅኖ ጥሪዎቹ የሚከተሉት ነበሩ፡፡

ሀ) በአፍሪካ ቻርተር አንቀጽ 16 መሠረት በታወቁ እስር ቤቶች ወይም በሌላ ቦታ የሚገኙ ታሳሪዎች በገለልተኛ አጣሪዎች በቤተሰቦቻቸውና በህግ አማካሪዎቻቸው እንዲጎበኙ እንዲሁም በቂ የህክምና አገልግሎት ማግኘት እንዲችሉ ሁኔታዎች እንዲመቻቹ፡፡

ለ) ባልታወቁ እስር ቤቶች የሚገኙ ታሳሪዎች እውቅና ባላቸው ማረሚያ ቤት እንዲገቡና አስቸኳይ ፍትህ እንዲሰጣቸው

ሐ) የኢትዮጵያ መንግስት የሮቢን ደሴት መመሪያ ጨምሮ ስለ አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች እና የእስረኞችን አያያዝ በተመለከተ ለዳኞችና ለእስር ቤት አስተዳዳሪዎች ተከታታይ ስልጠና እንዲሰጥ መክሯል፡፡ ነፃነታቸውም እንዲጠበቅ በዚሁ አጋጣሚ ጠቁሟል፡፡

መ) አዲሱን የበጐ አድራጐት ድርጅቶች አሳሪ ህግ ከተባበሩት መንግስታት የሰብአዊ መብቶች ጥበቃ አንፃር መልሶ እንዲቃኘው

የኢትዮጵያን ህዝብ ወደ ድቅድቅ ጨለማ ውስጥ እየዶሉት የሚገኙትና ላለፉት ሃያ አመታት በትከሻችን ላይ የተቀመጡት ገዢዎች የሰብአዊ መብት አያያዛቸው ከድጡ ወደ ማጡ እየሆነ ስለ መምጣቱ አፍሪካውያንን ሳይቀር እጅግ ማሳሰቡ የባንጁል ውሳኔ ምስክር ነው፡፡ በሌላ በኩል የሰብአዊ መብት አያያዝ ሪኰርዳችን ከሌሎች የአፍሪካ ሀገራት ሁሉ ዝቅ ብሎ የመገኘቱ ሁኔታ በእውነቱ በእጅጉ ያሳምማል፡፡ ለማንኛውም 51ኛው የባንጁል ጋምቢያ የአፍሪካ ኮሚሽን “በኢትዮጵያ የሠብአዊ መብቶች ሁኔታ” በሚል ርእስ ያወጣውን መግለጫ አለፍ አለፍ አድርጌ ለመቃኘት እሞክራለሁ፡፡

ወደ ገፅ 7 ይዞራል....

## የጫት ንግድ መስፋፋቱ እያነጋገረ ነው

በኢትዮጵያ ባሉ ከተሞች የጫት ንግድ ከዕለት ወደዕለት እየተስፋፋ መምጣቱ እያነጋገረ ነው፡፡ በተለይ በሀገሪቱ ትላልቅ ከተሞች ውስጥ ባሉ የትምህርት ተቋማት እና የልጆች መዝናኛ ስፍራ አካባቢ ንግዱ እየተበራከተ እንዳለ ምንጮቻችን ጠቁመዋል፡፡

ስለጉዳዩ አዲስ አበባ ከተማን ተዘዋውረን የተመለከትን ሲሆን የጫት ንግድ በፊት ከተለመዱት ቦታዎች በተጨማሪ በተለያዩ አካባቢዎችም መስፋፋቱን ለማየት ችለናል፡፡

የጫት ነጋዴዎችንም ስለጉዳዩ መስፋፋት ምክንያቱ ምንድነው ላልናቸው ጥያቄ ሲመልሱ “የኬላዎች መነሳት እና መንግስት የጫት ንግድን በማበረታታቱ ነው” ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የንግድ ሚኒስቴር የጫት ኬላዎች መነሳትና አስፈላጊነትን አስመልክቶ የህዝብ ግንኙነት ባለሙያው አቶ አብዱራሂም “አላስፈላጊ እንግልትና ውጣ ውረድን ለማስቀረት አዎን ኬላዎች ተነስተዋል” ሲሉ ምላሽ ሰጥተውናል፡፡ አንዳንድ ያነጋገርናቸው የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በበኩላቸው መንግሥት የጫት ንግድን በከተሞች ላይ መስፋፋቱን ለምን እንደፈለ አልገባንም፤ ልጆቻችንም በቀላሉ ማግኘት በመቻላቸው የጫት ሱስ ሰለባ እየሆኑ ነው፣ መንግስት ትውልድን ከመታደግና ከማዳን ይልቅ በሱሶች እንዲጠመዱና ተስፋቢስ እንዲሆኑ እያደረገ ነውና ሊያስብበት ይገባል፡፡” ሲሉ ቅሬታቸውን ገልፀዋል፡፡

## የአቶ መለስ ምስል ከአደባባይ ተሰረቀ

በአቧሬ አድዋ አደባባይ ፊት ለፊት ተሰቅሎ የነበረው የጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ግዙፍ ምስል ባልታወቁ ሰዎች መሰረቁ ተገለፀ፡፡

በኢሳያስ ማስታወቂያ ታትሞ የተተከለው የአቶ መለስ ምስል “በዘመነ ትውልድ ያልተደፈረውን አባይ የደደፈረ ጀግና” የሚል መፈክር የያዘ እንደነበር የድርጅቱ ባለንብረት አቶ ኢሳያስ ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ተናግሯል፡፡

የአካባቢው ነዋሪዎች እንደ ገለፁት ምስሉ ተተክሎ የቆየው ለአምስት ቀናት ብቻ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ የምስሉን መጥፋት ግራ አጋቢ ያደረገው የአቶ መለስ ፎቶ በላዩ ላይ የታተመበት ከመሆኑ በተጨማሪ በቀን መሰረቁ ነው፡፡ በአዲስ አበባ የተለያዩ አካባቢዎች የአቶ መለስን ተክለ ስብዕና የሚገነቡ ምስሎች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ተበራክተዋል የሚሉት ነዋሪዎቹ በየትኛውም የአቶ መለስ ምስል ላይ ጉዳትም ሆነ ጥፋት ደርሶ እንደማያውቁ ተናግረዋል፡፡

አቶ ኢሳያስ ለምስሉ ከ35,000 (ሰላሣ አምስት ሺህ) ብር በላይ ማውጣቱን ገልፃሪል፡፡ አቶ ኢሳያስ አክሎም 28 ካሬ የሚሆነው ይህው ምስል በመጥፋቱ እንደተደናገጠ ለፍኖተ ነፃነት ተናግሯል፡፡

ይኸው የጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ምስል ከተሠቀለበት ቦታ ተገንጥሎ የተወሰደ ሲሆን በዘመናዊ ዲጂታል የህትመት መሣሪያ በኢሣያስ ማስታወቂያ ታትሞ በአቧሬ አድዋ አደባባይ ፊት ለፊት ተሰቅሎ የነበረ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

የኢሳያስ ማስታወቂያ ባለቤት ወጣት ኢሳያስ ለፍኖተ ነፃነት እንደተናገረው የምስሉ መጠን 7 ሜትር በ4 ሜትር መሆኑን በመግለፅና ስራውን ለእይታ ለማብቃትና አጠቃላይ የፍሬም ሥራውን በማካተት 35,000 (ሰላሣ አምስት ሺህ ብር) ወጭ እንደተረገበት ገልፃሪል፡፡

ይህ በእንዲህ እንዳለ የጠ/ሚኒስትሩ ምስል ግዙፍ ሆኖ ከፊት ለፊት አሁን በመገንባት ላይ ያለው የህዳሴው ግድብ በአንድ ላይ ሆኖ ከምስሉ ስር “በዘመነ ትውልድ ያልተደፈረውን አባይ የደፈረ ጀግና” የሚል ፅሑፍ እንደነበረው ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የነበቀለ ገርባ ክስ ላይ የመከላከያ ምስክር ሳይሰማ ቀረ

በፌደራሉ አቃቤ ህግ በ “ሽብርተኝነት” ክስ ተመስርቶባቸው ጉዳያቸው በፌደራል ከፍተኛ ፍ/ቤት ልደታ ምድብ 3ኛ ወንጀል እየታየ ያለው በነ አቶ በቀለ ገርባ ክስ ተከሳሾች የመከላከያ ምስክሮቻቸውን እያሰሙ እንደነበር መዘገባችን ይታወሳል፡፡

ባለፈው አርብ ግንቦት 17 ቀን 2004 ዓ.ም በዚሁ የክስ መዝገብ 2ኛ ተከሳሽ የሆኑት አቶ ኦልባና ሌሊሳ የመከላከያ ምስክር ለመስማት ፍ/ቤቱ ቀጠሮ ሰጥቶ ነበር፡፡

የኦህኮ /መድረክ ጽ/ቤት ኃላፊ የሆኑት አቶ ኦልባና ሌሊሳ በዕለቱ የመከላከያ ምስክሮቻቸውን ያቀረቡ ቢሆንም ሳይሰማ ቀርቷል፡፡ የመከላከያ ምስክሮቹ ቃል ያልተሰማበት ምክንያት ፍ/ቤቱ መከላከያ ምስክሮቹ እንዲመሰክሩ የተገለፀው ጭብጥ ከክሱ ጋር የተያያዘ አይደለም በሚል ውድቅ አድርጐታል፡፡ ይሁን እንጂ የምስክሮች ቃል እንደገና ከክሱ ጭብጥ ጋር የተያያዘ ሆኖ ተስተካክሎ እንዲቀርብ ፍ/ቤቱ ትዕዛዝ ሰጥቷል፡፡

ዛዜ



# ኪነ-ጥበብ ሰዎቻችን ፍርሃት ወለድ ኑዛዜ

## – "አርቲስቶቻችን" ምን ነካቸው?



ዳንኤል ተፈራ

የኪነ-ጥበብ ልሂቃኑ ዘርፈ ብዙ ሚና ላላት ኪነ-ጥበብ ወጥና የሚያስማማ፤ በአንድ ቃል ፍፅም የሚል ትርጓሜ መስጠት አልቻሉም፡፡ እንደ ውቅያኖስ ጥልቀት ያላትን፣ እንደ ሀይቅ ጠልቀው የማይጨርሷትን ኪነጥበብ እንደየ ቱባ ባህሉ በርካታ ትርጉም ከመስጠት ባለፈ ሰብሰብ አድርጐ "ኪነ-ጥበብ እኮ እንዲህ ናት?" ያለ ደፋር የለም፡፡ ኪነ-ጥበብ ለመራቀቅ የምትመች፤ ምጥቀታዊ የማህበረሰብ አንጡራ ሀብት ናት፡፡ የማይሰጧትና የማይነጥቋት ረቂቅ የህዝብ መሳሪያ፡፡

እንደ ኪነ-ጥበብ ባለሙያዎች ገለጣ የኪነ-ጥበብ መነሻ ተፈጥሮ ነው፡፡ ከተፈጥሮ ምንጭ የምትቀዳና ኩልል ብላ ወደ ህዝቡ የምትወርድ ንፁህ ውሃ ናት፡፡ ከተፈጥሮ ተወልዳ መልሳ ተፈጥሮን የምታስውብ፤ መገለጫዎቿ እውነትና ውበት የሆኑ፤ የሰው ልጅ ከተከሰተበት ጀምሮ ያፈራት፣ ያሳደጋት፣ ያጐለመሳት ግን የማትሞት፤ ለማንም መሣሪያ ሆና የማታገለግል፤ የማትወግን የህይወት ነፀብራቅ ናት፡፡ ስነ ህንፃው፣ ስዕሉ፣ ሙዚቃው፣ ቲያትሩ፣ እንጉርጉሮው፣ ፉከራው፣ ጨኸቱ፣ ለቅሶው፣ ረገዳው፣ ቀረርቶው፣ ድራማው፣ ሽለላው . . . ሁሉ ደግሞ መገለጫዎቿ ናቸው፡፡

ታዲያ ኪነ-ጥበብን ከህዝቡ ወስዶ ለህዝቡ መልሶ የሚያደርሰው የየዘርፉ ባለሙያ (የኪነ ጥበብ ሰው) "አርቲስት" ይባላል፡፡ አርቲስት የሚለው ቃል ራሱ አወዛጋቢ ቢሆንም፤ አብዛኞቹ ከመሬት ተነስተው አርቲስት የሚለውን ቃል እንደ ቢጃማ ማጥለቅ ቢወዱም፤ ለአነሳነው ርዕስ ይገልጥልናልና ቃሉን ለዚህ ፅሁፍ እንደ መግባቢያ በመጠቀም ተስማምተን እንቀጥል፡፡

የዚህ ፅሁፍ መነሻ ሀሳብ ሁለት ሳምንት ወደኋላ በሚወስደን የኪነ-ጥበብ ውይይት ላይ የተገኘ ነው፡፡ አዘጋጁ አንድነት ፓርቲ፡፡ ቦታው ደግሞ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ትያትር፡፡ ቀኑስ? አትሉኝም አዎ ግንቦት 12 ቀን 2004 ዓ.ም፡፡ በዚህ ውይይት ላይ ከታደሙት አንዱ ነበኩ፡፡ የኪ-ጥበብ መግነጢሳዊ ኃይል "እጅ ወደ ላይ!" ካስባለቻቸው አንዱ ነኝ፡፡ የኪነ-ጥበብ ባለሞያ ሳልሆን የኪነ-ጥበብ አድናቂ፡፡ እናም ደጋግሜ ብፅፍ ባልሰለቸሁ፡፡ ልክ እንደ ፖለቲካችን ሁሉ የዝምታ ድባብ የወደቀባት የቁልቁለት ጉዞውን አገባዳ ባፍጢሟ ልትደፋ ጥቂት የቀራት የሀገሬ ኪነጥበብ ያ ቱባነቷ ደብዝዞ፣ የህዝብ ሀብትነቷ ተዘንግቶ አንድ አካልን እንድታገለግል፣ እንዳትተነፍስና የፊጥኝ እንድትታሰር የተፈረደባት ወቅት ነውና፡፡ "ኪነ-ጥበብ በማህበረሰብ ውስጥ ያላት ሚና" የሚለው ርዕስ ልብ የሚያቆም ነበር፡፡

ለውይይት የትያትር መስዋዕት በሚሰዋበትና የኪነ-ጥበብ አዋይ አድባር በረበበበት የመድረክ ላይም ፀሐፊ ተውኔት፣ ገጣሚና ደራሲ አያልነህ ሙላቱ፣ ሰዓሊ እሸቱ ጥሩነህ ሰዓሊና ቀራፂ በቀለ መኮንን እና ከደራሲያን ማህበር ደግሞ ደራሲ አበረ አዳሙ ተሰይመዋል፡፡ አንጋፋው ፖለቲከኛ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ መድረኩን እየመሩት ነበር፡፡

በእርግጥም ግሩም የሚባል የኪነ-ጥበብን ትርጉምና ሚና በሰፊው የዘረዘረ የመወያያ ፅሁፍ በአያልነህ ሙላቱ ቀረበ፡፡ መልካም ይሄ ባልከፋ ነበር፡፡ ኸረ ጥሩም ነው፡፡ ግን በተዘጋጀው መድረክ ላይ ደፍሮ ኪነ-ጥበብ በዘመነ ኢህአዴግ ሚናዋ ምን እንደሆነ? ነፃነቷ እንደተገፈፈና አርቲስቱ ጠንካራ ሀገራዊ የሆኑ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ከማንሳት በመቆጠብ ተልካሻ በሆኑ የመንደር ውስጥ ቧልቶችና ወጐች እንደተሸጐጠ የሚናገር ደፋር ጠፋ፡፡ ነፃነት የሌላት ኪነ-ጥበብ ህመምተኛ ናት፡፡ ይሄን ህመሟን ማን ይድፈር፡፡ መድረሱ ላይ በድፍረት ከመናገር ይልቅ አንጋፋ የኪነ-ጥበብ ባለሞያዎቻችን ፍርሃት የወለደው ኑዛዜያቸውን አሰሙን፡፡

አራቱም እውቅ አርቲስቶች ከንግግራቸው መግቢያ በፊት አሰልቺና ርባና የሌለው ቃል አሰምተውናል "እኛ የማንም ተቃዋሚም ደጋፊም አይደለንም፤ ንፁህ የጥበብ ሰዎች ነን" የሚል፡፡ በእርግጥ የኪነ-ጥበብ ሰው "ወገንተኛ" ባይሆን ይመረጣል፡፡ ወገንተኛ መሆን ሰዋዊ ባህሪ ቢሆንም እነዚሁ እውቅ አርቲስቶች "እኛ የማንም ደጋፊ አይደለንም" የሚል ኑዛዜ ያለቦታው ሳይጠየቁ እንዲያሰሙ የገፋፋቸው አብይ ምክንያት በገዥው ፓርቲ ዘንድ ቂም ይያዝብናል ከሚል ተራ ስጋት በመነሳት እንደሆነ መገመት አይከብድም፡፡ ፖለቲከኛ ወይም የፖለቲካ አባል ደጋፊ መሆን አይጠበቅባቸውም፡፡ ኑዛዜው ግን ፈፅሞ የማያስፈልግ የአንጋፋ አርቲስቶችን ፍርሃትና ጥንቃቄ የሚያሳይ ነበር፡፡ እሪ በይ ኪነ-ጥበብ!

ታዲያ የመግቢያ ኑዛዜው አስደምሞን ሳያበቃ የደራሲያን ማህበርን ወክለው የተገኙት አቶ አበረ ከአንድነት ፓርቲ ኪነ-ጥበብ ሚና ላይ ውይይት ለማካሄድ ተሳታፊ እንደሆኑ ደብዳቤ ሲደርሳቸው ከፍተኛ ክርክርና ውዝግብ ነበር አሉ፡፡ ክርክራቸው ምን እንደነበረ ለመገመት ይቻላል፡፡ "ተቃዋሚ ባዘጋጀው የኪነ-ጥበብ መድረክ ላይ ብንገኝ ጌታችን ኢህአዴግ ምን ይላል? ኢህአዴግን ማስከፋት አይሆንብንምን? ሌላ ትርጉም ይሰጥብን ይሆን?" የመሳሰሉ ስጋቶችና ክርክሮች ይመስሉኛል፡፡ በመጨረሻም የደራሲያን ማህበር ከጉንጭ አልፋ ክርክር በኋላ ወሰነ፡፡ አቶ አበረ እንደነገሩን "እናንተ የዓለም ጨው ናችሁ፤ ጨው አልጫ ቢሆን በምን ይጣፍጣል!" በሚለው የመፅሐፍ ቅዱ ጥቅስ ተመርተን መጣን ብለውናል፡፡ ለጥቀውም "እኛ ሳንደግፍም ሳንቃወምም ነው መስራት የምንፈልገው" በማለት ከሰው ተፈጥሮአዊ ዑደት ውጭ የሆነ የመሀል መንገድ አሳይተውናል፡፡ በፖለቲካው እንደዚህ አይነቱ ጉዞ "መሀል ሰፋሪ" ያስብላል፡፡ የደራሲያን ማህበር የመሀል ሰፋሪነት ግን ወደ ገዥው ፓርቲ ያጋደለና "በመሞዳሞድ" ላይ የተመሰረቱ አካሄዶችን የመረጠ ይመስላል፡፡

ሌላው ከ "ፓናሊስቶቹ" አንደበት የሰማሁትና አራቱም የተስማሙበት ግን ለእኔ የሚያስማማና አከራካሪ የሆነውን ልጥቀስ፡፡ "ህዝቡ ፈርቷል፤ ዝምታ ወርሶታል፤ በሚያስፈራ ዝምታ ውስጥ ነው. . ." የሚል ነው፡፡ ይሄ ብዙ አያከራክርም፡፡ ህዝቡ ውስጥ ጥልቀት ያለው ዝምታ እያስተዋልን ነው፡፡ አርቲስቶቹ ቀጠሉና "የኪነ ጥበብ ባለሙያው ደግሞ ከህዝቡ ውስጥ የወጣ ስለሆነና የህዝቡ አካል ስለሆነ አብሮ ዝም ብሏል፡፡ ህዝቡ ኪነ-ጥበብን አላንቀሳቀሳትም" ብለውን እርፍ፡፡ እዚህ ላይ ወራጅ አለ፡፡ ከኪነ-ጥበብ ሚናዎች ዋንኛ የሚባለው እኮ ህዝብን ማንቃት ማደራጀትና ተሳታፊ እንዲሆን መገፋፋት ነው፡፡

እዚህ ላይ ኪነ-ጥበብ መሪ ነው ወይስ ተመሪ መሆን ያለባት? የሚለው ጥያቄ ይመጣል፡፡ ኪነ-ጥበብ መሪ እንጅ ፈፅሞ ተመሪ መሆን የለባትም፤ ባህሪዋም አይደለም፡፡ አሁን ግን ኪነ-ጥበብ በተቀደደላት አንዲት ቀጭን ቦይ እንድትፈስ ተፈርዶባታል፡፡ እሱም ፋይዳዋን ለልማት ብቻ ማድረግ የሚል ነው፡፡ በዚህ ቦይ እንዲፈሱ የተገደዱት የዘመናችን አርቲስቶችም እንደ ቀጭኗ ቦይ ሁሉ ዓይናቸው ጠበበና የማህበረሰቡን ሸክምና ችጋር ዘነጉት፡፡ የተቀየሰላቸውን ቦይም ተከትለው ፈሰሱ፡፡ ያኔ ህዝቡ ከእነሱ ብዙ ክንድ ራቀ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የሚነግሩት ህይወቱ ያልሆነውን ነውና፡፡

እስቲ የፊልሞቻችንን የታሪክ ይዘትና የሚያነሱትን ሀሳብ ትተን የሚሰሩበትን ቤት እንመልከት የእኛ አይደሉም፡፡ የሙዚቃ ክሊፖችስ እንዴት ናቸው? ቲያትሮችንስ? ከደራሲያን ማህበር የመጡት አቶ አበረ "መጽሐፍ አንባቢ የለም!" ሲሉ ይወቅሳሉ፡፡ ጥያቄው ፀሐፊስ አለ ወይ? የሚለው ነው፡፡ ማለቴ ተልካሻ ከሆኑ የጓዳ ውስጥ ታሪኮች ወጣ ብሎ የህይወትን ውበትና የተጫናትን ድብታ የሚበረብር ማለቴ ነው፡፡ አንባቢ ሞልቷል የዚህኛው ትውልድ እንኳ የፍራሃትን አጥር ሰብረው በመውጣት የህዝቡን ሀቅ የጠቆሙ ፀሐፊዎች መፅሐፎቻቸው እንደ ጉድ

ወደ ገፅ 9 ይዞራል....

# መስከረም 2 + ግንቦት 20 = መንግሥቱ ኃ/ማርያም + መለስ ዜናዊ = 38

ከመ/ር ቀለሙ ሁነኛው
kelemhun@yahoo.com

"ያለምንም ደም እንከኗ ይውደም
በፀና መንፈስ ኢትዮጵያ ትቅደም . . ."

በወታደራዊ ማርሽ ታጅቦ የሚያስተጋባ ዝማሬ! "ከጓድ መንግሥቱ ኃ/ማርያም ቆራጥ አመራር ጋር ወደፊት!" ግራ እጆች እስኪዝሉ የሚስተጋባ መፈክር፡፡ በመላው አገሪቱ ለአብዮቱ ማክበሪያ የተዘጋጁ "የአብዮት አደባባዮች" በብሔራዊ ባንዲራ፣ በመፈክርና የተለያዩ ህብረ ቀለማትን በሚፈነጥቁ የኤሌክትሪክ አምፑሎች የሚያሸበርቁበት መስከረም ሁለት ብሔራዊ በአልነቱ ከሥርዓቱ ጋር ከወደቀ እነሆ ዛሬ ግንቦት 20/2004 ዓ.ም ድፍን ሃያ አንድ አመቱ፡፡

በጣት የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች ወታደራዊውን ደርግ ነፍጥ አንግበው ለመታገል ደደቢት በረሀ ወረዱ፡፡ የአንድ እናት ልጆች ጎራ ለይተው የተገዳደሉበት ጦርነት በድል ተጠናቅቆ ህወሓት መራሽ ኢህአዴግ በተራው አገርን ለመምራት ከአራት ኪሎው ቤተ መንግሥት ከከተመ ግንቦት 20/2004 ዓ.ም ድፍን ሃያ አንድ አመቱ፡፡ 21 + ? + ? + ? = ? "ጃ ያስተሰርያል አዲስ መንግሥት እንጂ ለውጥ መቼ መጣ!?"

ዛሬ ግንቦት 20 ነው፡፡ ኢህአዴግ ደርግን አሸንፎ አገሪቱን መምራት ከጀመረ 21 ዓመት ሞላው፡፡ ለ17 ዓመታት ደም ባፈሰሰው ጦርነት በሁለቱም ወገን ህይወታቸው ለበረሀ አሸዋ ለገበሩ ኢትዮጵያውያን ወንድሞቻችንና እህቶቻችን ንባባችንን አቁመን በፍፁም አገራዊ ስሜት ውስጥ ሆነንና አይናችንን ከድነን የሕሊና ፀሎት እናድርግ፡፡

ለአያሌ ምዕተ ዓመታት በአገራችን ሥር ሰድዶ የቆየውን ንጉሳዊ አገዛዝ ገርስሶ ሥልጣኑን በጊዜያዊነት የተረከበው ጊዜያዊው ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ለህዝብ የገባውን ቃል በማጠፍ ራሱን ወደ ሲቪል ለውጦ መንበረ ሥልጣኑ ላይ ጉብ አለ፡፡ በወቅቱ ተቀናቃኝ የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎችን በወታደራዊ ክንዱ ጨፈላለቃቸው፡፡ "ቀይ ሽብር ይፋፋም" የሚል እኩይ መፈክር አንግቦ ምድሪቱን በወጣት ምሁራን ደም አቀላው፡፡ ወጣቱን ከእናቱ ጉያ እየነጠቀ በአደባባይ ረሸነ፡፡ የሶሻሊዝምን ርዕዮተ ዓለም አንግቦ ለ17 ዓመታት የአብዮት ነጋሪት ጎሰመ፡፡ መስከረም 2 ሕዝብ በአብዮት ጥበቃዎች ተገድዶ በነቂስ እየወጣ ከንጉሱ አገዛዝ ነፃ የወጣበትን የነፃነት ቀን ያለነፃነት ሲያከብር ከረመ፡፡ ሕዝቡ በየአካባቢው በሚገኙ የአብዮት አደባባዮች በኢሰማ፣ በከነማ፣ በመኢገማ፣ (አኢወማ) ስም እየተሰለፈ የአብዮት በአሉን በሆታና በእልልታ አጀበ፡፡

የደርግ የ17 ዓመታት የግፍና የስቃይ አገዛዝ ያንገፈገፋቸው አያሌ ምሁራን አገር ጥለው ተሰደዱ፤ ግማሹ በባሌ፣ ግማሹ በሞያሌ፣ ዝቅ ያለው በቦሌ፡፡ ኮሎኔል መንግሥቱ ኃ/ማርያም ስልጣናቸውን ሳያስነኩ ከአብዮቱ ጋር እኩል 17 ዓመት ሙሉ በጀግንነት ተዘከሩ፤ ከንቱ ውዳሴ፤ ፎቶ ግራፋቸው ከተራ የቀበሌ ቢሮ ጀምሮ ሲሰቀልና ሲመለከበት ተኖረ፡፡ ኮሎኔሉም አገሪቱን ከንጉሰ ነገስቱ አገዛዝ ሳይሆን ከአንበሳ መንጋጋ ብቻቸውን ታግለው መንጭቀው እንዳጸኗት ነገር ለ17 ዓመታት ተመለኩ፡፡ የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበር፣ የኢሰፓአኮ ሊቀመንበር፣ የኢህዲሪ ፕሬዝዳንት፣ የአብዮታዊ ጦር ጠቅላይ አዛዥ፣ የኢሠፓ ዋና ፀሐፊ አንዳችም አገራዊ ፋይዳ ባልታየበት የስም ስልጣን ተከበው ሕዝብን ለስቃይ ዳረጉ፡፡ በራቸውን ለጠረጼዛ ዙሪያ ድርድር የከረቸሙት ጓድ መንግስቱ ኃ/ማርያም የመስከረም 2 የአብዮት በዓል በተከበረ ቁጥር መስቀል አደባባይ (በቀድሞ ስሙ አብዮት አደባባይ) እየተገኙ በባዶ ሜዳ በሻዕቢያና በወያኔ ላይ ይፎክሩ ነበር፡፡ "አብዮት ልጇን ትበላለች" እያሉ በመቶ ሺህ የሚቆጠሩ ውድ ኢትዮጵያውያንን ቀርጥፈው በሉ፡፡ ለእርሳቸው የሥልጣን እድሜ ርዝማኔ አብዮት ልጇን ቀርጥፋ ብትበላም በህዝብ ይሁንታ እንጂ በሰው ደም የፋፋ መንግሥት የለምና ጓድ መንግሥቱና የ4 ኪሎው ቤተመንግስት ፍቅራቸው አካተመ፡፡ ከባለቤታቸው ከውባንቺ ቢሻው ይበልጥ የሚወዱትን ሥልጣን ሳይወዱ በግድ ለአቶ መለስ ዜናዊ አስረክበው ዙምባቡዌ ከከተሙ እነሆ ዛሬ ግንቦት 2004 ዓ.ም ድፍን ሃያ አንድ አመታቸው፡፡

ከጓድ መንግስቱ ወደ አቶ መለስ የዞረው ስልጣን እንደ "የነፃነት ቀን" ተቆጥሮ ግንቦት 20 መከበር ጀመረ፡፡ ከመስከረም 2 ወደ ግንቦት 20 ሽግግር ተደረገ፡፡ እርግጥ ነው የኢትዮጵያ ህዝብ ከወታደራዊው ደርግ አምባገነናዊ አገዛዝ ነፃ ወጥቷል፡፡ ይሁን እንጂ ብዙ የተባለለትን ዴሞክራሲ ግን እንደ ዳቦ መግመጥ አልቻለም፡፡ ገና ከማለደው ያለፉትን መንግስታት የታሪክ ቅርስ አፈራርሶ ከዜሮ መጀመርን ብቸኛ አማራጭ ያደረገው የአቶ መለስ መንግስት በብሄርና በቋንቋ የተመሰረተ ፖለቲካን በማንገብ አገሪቱን በዘር ከፋፈለ፡፡ ከጠቅላይ ግዛት ወደ ክ/ሀገር ከዚያም ወደ ክልል፡፡ "ሁሉም በየወገንህ ሲባል ርኮት ወደ. . ." ቁርበት እንዲሉ እድሜ ለኢህአዴግ ለኢትዮጵያዊነቱ እንጂ ለዘር ሀረጉ ግድ ያልነበረው ሁሉ ቁጭ ብሎ ዙሩን እየቆጠረ ጎራ ለየ፡፡ የ1987 ዓ.ም የዘመነ ኢህአዴግ ህገ መንግስትም በአንቀጽ 39 የሰፈረውን የመገንጣጠል ሀሳብ ሰንቆ ብቅ አለ፡፡ ከኤርትራ በኋላ በቀጣይ የሚገነጠለው ክልል ባይታወቅም ኢህአዴግ እሳካለ አንቀፁ የሚሻሻል አይመስልም፡፡

ወታደራዊው ደርግ ገና ከመነሻው ዴሞክራሲያዊ ባህሪይን ተላብሶ የመድበለ ፓርቲን ሥርዓት ለማስፈን ሞክሮ ነበር፡፡ በማርክሲዝም ፌደራሊዝም የፍልስፍና ፍቅር የተነደፉ በርካታ ወጣቶችንና ምሁራንን ያቀፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ አሸን ቢፈሉም እንደ አሸን ክንፍ ተራገፉ፡፡ ከኢሰፓ ውጭ ፓርቲ ላይታሰብ አዋጅ ተነገረ፡፡ የኢህአዴግ አካሄድም ከደርግ አልተሻለም፡፡ ባስልጣኑ ጅማሬ የሽግግር መንግስት የሰየመው ህወሓት/ኢህአዴግ በዘመነ ደርግ በትጥቅ ትግልና በስደት ላይ ለነበሩት ፓርቲዎች ጥሪ አቅርቦ ወደ ሀገር ቤት እንዲገቡ ማድረጉ ይታወቃል፡፡ ይሁን እንጂ ውለው ሳያድሩ በገቡበት መንገድ እንዲወጡ ተገደዱ፡፡ የግንቦት 20 ድል ለህወሓት መሪዎችና ለድል አጥቢያ ፓርቲዎች (ኦህዴድ፣ ደህዴን፣ ብአዴን፣ አብዴፓ . . .) እንጂ ለእነ ኦነግና ኦብነግ ለመሳሰሉት ፊቱን አዞረ፡፡ ኢህአዴግም ከሽግግር መንግስት ወደ ቋሚ መንግስትነት ተቀየረ፤ ወታደራዊው ደርግ የጦር ሰራዊት ዩኒፎርሙን ወደ ሰማያዊ ካኪ እንደቀየረ ሁሉ፡፡ አቶ መለስ ዜናዊም ከፕሬዝዳንትነት ወደ ጠቅላይ ሚኒስትርነት ተሸጋገሩ፡፡ ኮሎኔል መንግሥቱም ከጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ ሊቀመንበርነት ወደ ኢህዲሪ ፕሬዝዳንትነት፡፡ ስማቸው እንጂ

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

ነፃ አስተያየት

# መድረክ በመድረክ ላይ?



አንዳርጌ መስፍን

መድረክ የተቋቋመው በ2002 ምርጫ ዋዜማ ነው፡፡ በመጀመሪያ ሲቋቋም አባል ድርጅቶቹ ስምንት ነበሩ፡፡ ይሁን እንጂ ሁለቱ ድርጅቶች ብዙም ሳይርቁ ወዲያውኑ ጥለው ወጥተዋል፡፡ ቀሪዎቹ ስድስቱ ግን እያዘገሙም ቢሆን ልዩነቶቻቸውን አቻችለው እስካሁን ድረስ አብረው ቆይተዋል፡፡ የጎሪጥ በጥላቻ ከመተያየት ተላቀው በዚሁ ዳር መዝለቅ ከቻሉ የኢትዮጵያን ተራ የፖለቲካ ቁማር ጨዋታ ይሰብሩታል የሚል እምነትን በብዙዎች ዘንድ አሳድሯል፡፡ ግን ደግሞ የግንባሩ አለመመስረትና መጓተት አንዳንዶችን ማሳሰቡ አልቀረም፡፡

በዚህ 21 ዓመታት ውስጥ የምናስተውለው በሕዝብ ስም እየማሉና እየተገዘቱ የግል ኑሯቸውን ያመቻቹና ትክለሰውነታቸውን የገነቡ በመኖራቸው ጥርጣሬውና ሥጋቱ አግባብነት ያለው ነው፡፡

ሁለት ሊጣጣሙ የማይችሉ መርሆዎችን የሚያራምዱ ፓርቲዎች ማለትም ሕብረ ብሔራዊ መርህ አንግበው የተነሱና የብሔርተኝነት መርህ ይዘው የሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች "መጣጣም እንችላለን፤ እስከዛሬ ድረስ ያልሄድንበትን መንገድ እንሂድበት" ብለው ፊት ለፊት በመገናኘት በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተወያይተው ሰጥቶ የመቀበልን መርህ አክብረው መቆየታቸው በራሱ አንጋፋ ምሁሮቻችን በዚህ በኩል ሊመሰገኑ ይገባቸዋል፡፡ እስካሁን ድረስ በረጋና በሰከነ መልኩ መጓዛቸውም ብዙም አያስነቅፋቸውም፡፡ ይሁን እንጂ ግንባር ለመመስረት ከተሥማሙና ካፀደቁ በኋላ ግንባሩን እውን አለማድረጋቸው የግንባሩን መመስረት በጉጉት ለሚጠባበቁ ወገኖች ማሳሰቡና ቅር ማሰኘቱ እውነት ነው፡፡ በተለይም የመጓተቱ ምክንያት በግልፅ አለመታወቁና ድፍን ያለ በመሆኑ ለሥጋቱ ዋና ምንጭ ሆኗል፡፡

አንዳንዶች የሚሉት ደግሞ "መድረክ በጥምረትም ቢሆን እስካሁን ፀንቶ የቆየው ገዥውን ፓርቲ የመፎካከር ሥራ ባለመሥራቱ ነው" ይላሉ፡፡ አያይዘውም "መድረኩ ኢህአዴግን ቢፈታተነው ኖሮ አባላቱን እሥርን በማስገባት ውሻ እንደገባበት ዝንጀሮ ይበታትነው ነበር" በማለት ይተቻሉ፡፡ ይህም ሆኖ ኢህአዴግ መድረክን ወደ ሕዝቡ ቀርቦ እንዲወያይና እንዲነጋገር በሩን አልከፈተለትም፡፡ መድረክም እንዲከፈትለት አጥብቆ ሲያንኳኳ አላስተዋልንም፡፡

አንድ ስማቸው እንዲጠቀስ ያልፈለጉ አዛውንት በበኩላቸው ከላይ የተጠቀሰውን ሐሳብ ያጠናክሩታል፡፡ "መድረክ ሕዝብ ውስጥ ገብቶ ሥራ አልሠራም፡፡ መግለጫ በወንጭፍ ለማቀበል ይሞክራል" ሲሉ ይወቅሳሉ፡፡ ለፖለቲካው ጨዋታ ቅርበት አለን የሚሉ ወገኖች በበኩላቸው መድረክን በተለየ መልኩ ይወቅሱታል፡፡ "ወደ ግንባር ፈጥኖ አለመሸጋገሩ ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ጨዋታውን አልቻለበትም" ነው የሚሉት፡፡ እንደማስረጃ የሚያቀርቡትም፡- "ገዥው ፓርቲ ሕዝብን ንቆ ዜጎችን ከመኗሪያ ቀያቸው እያፈናቀለ በጎን ደግሞ የውጭ ቱጃሮችን በኢንቬስተር ስም ሲያሰፍር መድረክ ትንፍሽ አላለም፡፡ መግለጫ ሰጥቷል ቢባልም እንኳን የሕዝብን ቀልብ የሚስብ አይደለም፡፡ በመግለጫም ኢህአዴግን ከሥልጣኑ ማውረድ አይቻልም" በማለት አጥብቀው ይነቅፋሉ፡፡ እነዚህ ወገኖች ነቀፋቸውን በመቀጠል "ኢህአዴግ አውቆም ይሁን ሳያውቅ ለመድረክ ያቀበለውን አጀንዳ ባግባቡ ስላልተጠቀመበት መልሶ ነጥቆታል" በማለት በቁጭት ይናገራሉ፡፡ "የአዲስ አበባ ሕዝብ የሊዝ ፖሊሲውን አውግዞ በየአዳራሾቹ ጥሎ ሲወጣ መድረክ ይህንን እድል አልተጠቀመበትም፡፡ ሕዝብን ጠርቶ መሬት አንቀጥቅጥ የሆነ ሠላማዊ ሰልፍ ማድረግ ይችል ነበር፡፡ ፈቃድ ማግኘት አለማግኘት ሌላ ነገር ሆኖ እሱ ግን በበቂ ሁኔታ ሲንቀሳቀስ አልታየም" በማለት ይወቅሳሉ፡፡

በርግጥም እነዚህ ወገኖች እንደሚሉት የመድረክ ጉዞ የተለሳለሰና አዝጋሚ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የሚሰራቸው ሥራዎች ሁሉ የቀዘቀዙና ግልፅነት የጎደላቸው በመሆናቸው የሕዝብን ሁለንተናዊ ተሣትፎ ማግኘት አለመቻሉ በራሱ የሚያስወቅሰው ይሆናል፡፡ ሌላው ቀርቶ መምህራን በሕጋዊ መልኩ የደመወዝና የእርከን ጭማሪ አቅርበው ሳለ አልጋ እንደነቀነቁና ሥርዓት ለማፍረስ እንደተንቀሳቀሱ ተቆጥረው ከጠ/ሚንስትሩ ጀምሮ በተዋረድ ባሉ ባለሥልናት ሲዋከቡና ከሥራ ሲባረሩ መድረክ ትንፍሽ አለማለቱ ብዙዎችን ሳያስገርም አልቀረም፡፡ ለምን? እንዴት? ብሎ ከመግለጫ ባለፈ መልኩ መጠየቅ ነበረበት የሚሉ ጥቂቶች አይደሉም፡፡

አንድ የሕግ ባለሙያ የጥብቅና ፈቃዳቸውን የተነጠቁ በበኩላቸው "የፍትሕ በሀገሪቱ ውስጥ ጠፍቶ ዜጎች ከላያቸው ላይ ቤንዚን እያርከፈከፉ ራሳቸውን አቃጥለው ሲገሉ መድረክ ይህንን ሥርዓት ርቃኑን የሚያስቀርበት ትልቅ እድል ነበር፡፡ ግን አልተጠቀመበትም" በማለት በምሬት ይገልፃሉ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ ከመድረክ አባል ድርጅቶች መሀከል አንድነት በተቻለው አቅም ሁሉ ሲንቀሳቀስ ይስተዋላል፡፡ ይህም ሆኖ የፓርቲው ዋና ፀሐፊ አቶ አሥራት "ገና አልሠራንም" ይላሉ፡፡

እንግዲህ መድረክን በተመለከተ ለዝግጅታችን ክፍል የሚደርሱን አስተያየቶችና ጥያቄዎች ከሞላ ጎደል እስካሁን የጠቀስኳቸውን ይመስላሉ፡፡ ቀጥለን ደግሞ አመራሮችስ ምን ይላሉ? የግንባሩ አለመመሥረትስ ምክንቶቹ ምንድን ናቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ለማስቃኘት እንሞክራለን፡፡

## የግንባሩ መመሥረት ለምን ዘገየ?

ብዙ ጊዜ ለግንባሩ ፈጥኖ አለመመሥረት በምክንያት የሚጠቀሱት ከስድስት ፓርቲዎች መሀከል ሁለቱ ፓርቲዎች ማለትም በፕ/ር በየነ ጴጥሮ የሚመራው የኢትዮጵያ ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ (ኢሶዴፓ) እና በአቶ ጥላሁን እንደሻው የሚመራው የደቡብ ኢትዮጵያ ዴሞክራቲክ ሕብረት (ደኢዴሕ) ጠቅላላ ጉባኤ ጠርተው ማፅደቅ አለመቻላቸው ነው እየተባለ ይነገራል፡፡ ይህንኑ በተመለከተ የመጀመሪያውን ጥያቄ ያቀረብኩላቸው በፕ/ር በየነ ጴጥሮስ ነበር፡፡ የሚከተለውን አጭር መልስ ሰጥተውኛል፡-

"ግንባሩ እንዳይመሠረት እያቀዘቀዙትና እያጓተቱት ነው የሚባለው ነገር ትርፍ ነው፡፡ ችግራችንን የመድረክ አባል ድርጅቶች ያውቁታል፡፡ እኛ ጠቅላላ ጉባኤ ለማካሄድ አንድ ዓመት ይቀረናል፡፡ መድረክ ወደ ግንባር እንዲሸጋገር የተወሰነው ከዚያ ወዲህ በመሆኑ ለዚህ ተግባር በጀት ባለመያዛችን የፋይናንስ ችግር ስለገጠመን ነው፡፡ ያም ሆኖ አሁን በቅርቡ ገንዘብ በድጋፍ መልክ ያገኘን ስለሆነ ሰኔ ወር መጀመሪያ ላይ ጠቅላላ ጉባኤ ጠርተን እናፀድቃለን፡፡ ከዚያ በኋላ መድረኩ እውን ይሆናል" ብለዋል፡፡ ለአቶ ጥላሁን እንደሻው ያቀረብኩላቸው ጥያቄም ተመሳሳይ ነበር፡፡ እሳቸውም ሲመልሱ "ችግራችንን የመድረክ አባል ድርጅቶች ያውቁታል፡፡ እኛ ኤክስትራ (ተጨማሪ) በጀት ስለሌለን ነው፡፡ ያም ሆነ ይህ ሰኔ ወር መጀመሪያ አጋማሽ ላይ ጠቅላላ ጉባኤ ጠርተን እናፀድቃለን" ብለዋል፡፡ ቀጥዬ ያነጋገርኳቸው የኦፌዴንን ሊቀመንበር ዶ/ር ሞጋ ፍሪሣ ነበር፡፡ የመድረክ ግንባር እውን አለመሆን ችግሩ ምንድነው? ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የሰጡኝ መልስ፡-

"በመሀከላችን ምንም ዓይነት ሌላ ችግር አልተፈጠረብንም፡፡ ለጊዜው ሁለቱ ድርጅቶች የፋይናንስ ችግር ስለገጠማቸው ትንሽ እንታገሳቸው ብለን ነው፡፡ በሰኔ ወር መጀመሪያ ላይ ይሳካላቸዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን" ብለዋል፡፡

ለአንድነት ዋና ፀሐፊ ለአቶ አሥራት ጣሴ ያቀረብኩላቸው ጥያቄ "የመድረክ ግንባር ምስረታ አለመፋጠኑ አንድነትን አልጎዳውም ይላሉ?" የሚል ሲሆን የሰጡኝ መልስ፡-

ወደ ገፅ 12 ይዞራል....

# አሁንም ከ8 ዓመታት ...

ከ ገፅ 11 የዞረ....

ቤት እምነት የማይጣልባቸው ቁጥር አንድ ተቋሞች ናቸው ከተባሉ ወዲህም የህዝብ ስጋትና ፍርሃት ጨምሯል፡፡ ያለፈውን ምርጫም እንደ ትምህርት በመውሰድ ለቀጣይ ምርጫ ከወዲሁ መዘጋጀት ጊዜ የማይሰጠው ሥራ መሆን አለበት፡፡

በሁሉም ዘርፍ ያለው ሙስና የተጨመላለቀና የዘቀጠ ደረጃ በመድረሱ የሚሰማውና የሚታየው ነገር ሁሉ የሚዘገንን ሆኖአል፡፡ የሙስሊሞች፣ ኦርቶዶክሶች፣ ስፋሪዎች፣ ተፈናቃዮች፣ ነጋዴዎች፣ የግል ባለሀብቶች፣ መምህራኖች ወ.ዘ.ተ ጥያቄ ተሰብስበው ሲታዩ የሆነ ነገር ይሸታል፡፡ ኢህአዴግ ግን አሁንም የኛ ሌቦች፣ አሸባሪዎች፣ ጥቂቶች ወ.ዘ.ተ እያለ ስም እየለጠፈና አዳዲስ ተቀላቃዮችን ከወዲያ ወዲህ በመሰብሰብና በማገለባበጡ ሥራ ላይ ተጠምዶ ይታያል፡፡ ግን እስከ መቼ? ውሸትና ስንቅ እያደር መቅለሉን አለማወቅ ከታሪክ አለመማር ነው፡፡ ቀጣዩ ምርጫ እንዳለፈው አስጨናቂ እንዳይሆንም ለፓርቲዎች የተከለከለ ሕግ የፕሬስ፣ የመያድ (መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች) የፀረ ሽብር ህግን ጨምሮ ሰሞኑን ለማተሚያ ቤቶች የተሰጠው ቅድመ ምርመራ ሁሉ ቢፈተሹ ወደ ዚያው የሚወስዱ ይሆናሉ፡፡ ደግነቱ ግን አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ማንንም ሲያስጠልሉ በታሪክ ተመዝግበው አለመታወቃቸው ነው፡፡

ለገዢው ፓርቲ ተቀናቃኝ የሆኑ ተፎካካሪ ፓርቱዎች ለወደፊቱ ምርጫ ምን እያሰቡ እንደሆነ ሕዝቡ መረጃ ሊያገኝ ግድ ይላል፡፡ ከመሀከላቸው አዳራሽ ተከለከልን፣ አባላቶቻችን በአሸባሪነት ተጠርጥረው ተይዘውብናል ሌላም ሌላም ከሚሉት ጀምሮ አሁንም ስሙ በበጐ የማይነሣው ምርጫ ቦርድ ጣልቃ እየገባብን ነው ሲሉ ይደመጣሉ፡፡ በአንፃሩ ግን ስለመዋሀድ የምንሰማው ነገር የለንም፡፡ ፓርቲ ለሚመረጠው የኛ አብሮ መሥራቱ ጥቅሙ ምን ላይ ነው? የሚለውን ጥያቄ እያንዳንዱ ፓርቲ ከራሱ እሳቤ ማውጣት አለበት፡፡ ቅድሚያ ለህዝብ ጥቅ መቆም ያስፈልጋል፡፡ ከ1997 ዓ.ም ምርጫ በኋላ በተፈጠረው ድርጊት አዝኖ ያልሸሻቸውን ሕዝብ አለንልህ ሊሉት ይገባል፡፡

የሀገሩን ባንዲራ በህዝባዊ ሠልፍ ወቅት ለመያዝ ፈቃደኛ ያልነበረ ነገር ግን በተፎካካሪ ፓርቲ ጐራነቱ በሚያወርደው ወርቃማ ንግግር ህዝብ ሰማይ ጥግ ያደረሰው፣ እንዲሁም ትርፍና ኪሳራ አስልተው ከሚፎካከሩት ፓርቲ ጋር በሚሰጥር ይሞዳሞዱ የነበሩ፣ የምርጫ ብልጫ ያለውን ፓርቲ ስም የነጠቁ ወሮ በላዎችና ቀጣፊዎች ወዘተ በአጠቃላይ በህዝብ የሚነግዱ ሆኑ ሊያተርፉ ያስፈሰፉ ሁሉ ንስሐቸውን አውርደው ከእውነት ጋር እንዲጣቡ ጊዜ ያቀረበላቸው ጥያቄ ነው፡፡ በከንቱ የፈሰሰው የደሀ ደምና ዕንባ ሊታበስ ይገባል፡፡ በማህተም ሰጠኝ አትስጠኝ ከኢዴፓ ጀምሮ እስከ አሁኑ ሁለተኛው ቅንጅትና መኢአድ ድረስ የዘለቀው ተላላፊ የቀለም በሽታ መቆም አለበት፡፡ በየትርክምርኪው ጉዳይ ወህኒ ለመወርወር ከመመቻቸት ዘውር ብሎ መመልከት ያስፈልጋል፡፡ በተጨማሪም ለሚያከብራችሁና ለሚወዳችሁ ወገን ቅድሚያና ክብር ሰጡ፡፡ ደግሞም እኮ!!! ኢህአዴግ ከቁጥር ጋር ሲተናነቅ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ከማህተም ጋር መተናነቃችሁ አንድ ያደርጋችኋል፡፡ ምክንያቱም ሁለቱም በህዝብ ጆሮ የማይደመጡ ናቸውና፡፡ ለማንኛውም ግን ሁልግዜ ፀጋዬ ገ/መድህን አርአያ ". . . ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ . . ." ሲል ከአመታት በፊት ያስተላለፈውን ጠንካራ መልዕክት አስታውሱለት፡፡

# አሳሳቢው የኢትዮጵያ ...

ከ ገፅ 5 የዞረ....

ሠ) እ.ኤ.አ በ2008 እና 2009 የወጡት የሚዲያና የፀረ አሸባሪነት ህጎች ላይ የሠፈሩት አንዳንድ አንቀፆች ሀሳብን በነፃነት ለመግለጽ ደንቃራ በመሆናቸው እንዲሰረዙ ጥሪ አቅርቧል፡፡

## እንደመደምደሚያ

## በርከክ በርከክ አሉ አውሬ መስያቸው፣ ከሠው መፈጠሬን ማን በነገራቸው፡፡

እንዲሉ ይህ ታላቅ ህዝብ አስከፊ የሰብአዊ መብት ረገጣው ደርሶበታል የሙብት ገፈፋው በእናት ሀገራቸው የሚኖሩትን ኢትዮጵያውያን እና እንጀራ ፍለጋ አሊያም የሥርዓቱ ሰለባ ላለመሆን ባህር ተሻግረው የሄዱትንም ይጨምራል፡፡ በወታደራዊ መንግስትም ሆነ በጎሳ ፖለቲካ አቀንቃኞቹ ዘመን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ከሰብአዊ ሙብት አጣባበቅ አኳያ የአለም ጭራ ሆነናል ብል የተሳሳትኩ አይመስለኝም፤

በተለይ በዚህ ዘመን የደረስንበት የሰውነት ደረጃ አሳፋሪ እና አንገትን የሚያስደፋ መሰለኝ፡፡ ያለን ትልቅ ሀብት (መሬት) ለድንበር ዘለል ታላላቅ ኩባንያዎች እና ለኢትዮጵያ ጥሩ አመለካከት ለሌላቸው ባእድ ሀገራት እየተቸበቸበ ነው፡፡ በቅርቡ ደግሞ ለአለም የሰብአዊ ሙብት ጥበቃ ግንባር ቀደም ተሟጋች እኔ ነኝ የምትለው አሜሪካ ኩባንያዎች ጓዛቸውን ጠቅልለው ለመምጣት ድርድር ጀምረዋል፤ በሰብአዊ ሙብት አያያዝ ሪኰርዳቸው ከፋኛ የሚነቀፉትን ክቡር አቶ መለስ ዜናዊ በቡድን 8 ስብሰባ ላይ ከሚካፈሉ አራት የአፍሪካ ሀገራት መሪዎች አንዱ ነበሩ፡፡ ያሳዝናል፡፡ ግራም ነፈሰ ቀኝ በመሬት ቅርምቱ ምክንያት በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ (እንደ ምሁራን ትንተና ከሆነ በሚሊዮን ይቆጠራሉ) አስከፊ የሰብአዊ ሙብት ገፈፋ ገጥሟቸዋል፡፡ የስርዓቱ ሹምባሾችና በቀቀኖች ግን ዘውትር በፕሮፓጋንዳ ማሺነሪዎቻቸው አማካኝነት የኢትዮጵያ ህዝብ (ገበሬ) ማርና ወተት እንደሚዘንብለት ሲያላዝኑ ይሰማል፡፡ እውነታው ግን ይሄ አይደለም የኢትዮጵያ ህዝብ (በአብዛኛው) የሰቀቀን ኑሮ መግፋት ከጀመረ አመታትን አስቆጥሯል፡፡ እርግጥ ነው ማርና ወተት አይደለም በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠር ዶላር የዘነበላቸው ጥቂት የስርዓቱ ቃፊሮች እንዳሉ ይታወቃል፡፡ አይመስለኝም ሚሊዮኖች ከአፈርና በሣር በተሠሩ ጎጆዎች በሚኖሩበት ሀገር በመቶሺ የሚቆጠር ወገኔ መንገድ ዳር ድንጋይ ተንተርሶ በሚኖርበት ሀገር (ኑሮ ከተባለ) ጥቂት ባለ ጊዜዎች ሶስትና አራት ፎቅ ቤቶች እንደገነቡ የምንሠማባት ሀገር ሆናለች እማማ ኢትዮጵያ፡፡

በአጠቃላይ አርባ ጉጉም ሆነ ወላይታ ሶዶ፣ አሠቦት ገዳምም ሆነ አደባባይ ኢየሱስ፣ አሦሳም ሆነ ጉራ ፈርዳ ወዘተ የሚያሳዩት ነገር ቢኖር በኢትዮጵያ የሰብአዊ ሙብት አያያዝ በአስከፊ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ነው፡፡ ስለሆነም የአገዛዝ ስርዓቱ አለም አቀፍ የሰብአዊ ሙብት ጥበቃ ድርጅቶችና በሀገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ የሠብአዊ ሙብት ተቆርቋሪ ድርጅቶችን ውትወታና ጩኸት በቅን ልቦና ተመልክቶ እንዲታረም እማፀናለሁ፡፡ የግፉ ፅዋ ሞልቶ ከፈሰሰ አይበጅንም፡፡ ለኢትዮጵያም ሆነ በስርዓቱ ፊት አውራሪዎች (እሽኰሎሌዎቻቸው) ወይም ለህዝቡ የሚበጀው ጊዜው ሳይመሽ ወደ ህሊናችን መመለስ ይመስለኛል፡፡

# የቀበሌ ክበባት የማናቸው?



*ብዙአየሁ ወንድሙ*

ደርግ ሥልጣን እንደያዘ መጀመሪያ ከወሰዳቸው እርምጃዎች አንዱ የቀበሌ መስተዳድራዊ መዋቅር ማደራጀት ነበር፡፡ ህዝብን በአስተዳደራዊ መዋቅር በቅርብ ማግኘት የቻለበት አደረጃጀት ነው፡፡ ካድሬዎችን አሰልጥኖ ህዝብን ባልተለመደ ሁኔታ በቀላሉ ማንቀሳቀስ ችሎአል፡፡ ለረጂም ዓመታት የህዝብ ጥያቄ ሆነው የቆዩ ጥያቄዎችን ለመመለስ ሞክሯል፡፡ መሬት ለአራሹ፤ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤቶች አዋጅ፣ የወዛደሮች ጥያቄ ወዘተ መጥቀስ ይቻላል፡፡ ደርግ ሥልጣኑን ከተቆጣጠረ በቀይ ሽብር እና በጦርነት ምክንያት የተፈጠሩ አስከፊ ሁኔታዎች በተደጋጋሚ ለ20 ዓመታት የተነገረ ጉዳይ ስለሆነ ማስለቸት ይሆንብኛል፡፡ ግን አንድ የማይነሳ አብይ ጉዳይ አለ፡፡ ደርግ እንዴት ሆኖ ወደ ቀይ ሽብር ሄደ? በምን ምክንያት የከፋ ጦርነት ውስጥ ገባ? ደርግ ጥሎ ላለፈው ጠባሳ ተጠያቂው ደርግ ብቻ ነው? ወደ ርዕሴ ልመለስ፡፡

ደርግ ቀበሌን ሲያቋቁም አስተዳደራዊ መዋቅሩን ብቻ አልነበረም፡፡ ዝቅተኛው የህብረተሰብ አካል አገልግሎት የሚያገኝባቸውን ቀበሌ ክበባትንና የህብረት ሱቆችንም ጭምር ነው፡፡ እጅግ አነስተኛ በሆነ ትርፍ ህብረተሰቡን የሚያገለግሉ የቀበሌ ክበባት ተደራጁ፡፡ አንዳንዱ የቀበሌ ነዋሪ ገንዘብ አዋጥቶ ክበባትን አቋቋመ፡፡

በአዋጅ የተወረሱ ሰፋፊ ቤቶች ለመዝናኛ በነፃ ተሰጡ፡፡ ከአገር ውስጥ ገቢ ግብራና ልዩ ልዩ ክፍያዎች ነፃ ሆኑ፡፡ የንግድ ፍቃድ ሳያወጡ ህብረተሰቡን እንዲያገለግሉ ተደረገ፡፡ ጥሬ ዕቃዎችን በጂንአድ እንዲወስዱ ተፈቀደላቸው፡፡ መዝናኛው የቀበሌው ህዝብ በመሆኑ የቀበሌው ህዝብ እየተሰበሰበ የመዝናኛውን አመራሮች ይመርጣል፡፡ በየዓመቱ የመዝናኛ ክበቡን የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ይሰማል፡፡ ይገመግማል፤ ውሳኔ እና አመራር ይሰጥበታል፡፡ የመዝናኛ ክበቡ ዋና ዓላማ ከፍተኛ ሆቴል ሄደው መገልገል ለማይችለው የህብረተሰብ አካ አገልግሎት መስጠት ነበር፡፡

በቅርቡ እንደምንመለከተው ግን የቀበሌ ክበባት የማናቸው እንድንል ተገደናል፡፡ የቀበሌው ነዋሪ ያለ አዋጅ ንብረቱን እየተነጠቀ ነው፡፡ በአንዳንድ ቀበሌዎች የአደራ ቦርድ የሚባሉት የቀበሌው ነዋሪዎች አይደሉም፡፡ በቀበሌው ክበብ ከገቡ በኋላ ከመጡበት ቦታ ይዘውት እንደመጡት ንብረት ያዙበታል፡፡ በየቀበሌው የምንመለከተው የምግብና የመጠጥ ዋጋ በውድ ዋጋ ቤት ተከራይተው ተደራራቢ ክፍያ ለመንግስት ከሚከፍሉት ድርጅቶችና ግለሰቦች እኩል የዋጋ ተመን ያስከፍላሉ፡፡ ተገቢውን አገልግሎት አይሰጡም፡፡

በቅርቡ ቂርቆስ ክፍለ ከተማ ውስጥ መሻዕለኪያ አካባቢ በሚገኝ ቂ/ክ/ከ በቀድሞ አጠራሩ ቀበሌ 15 መዝናኛ ክበብ አንድ ትልቁ በደሌ ቢራ 14 ብር ሲሸጥ ከዚሁ ቀበሌ በግምት 300 ሜትር ላይ ያለው በቀድሞ ቀበሌ 32 መዝናኛ በ11 ብር ከመልካም መስተንግዶ ጋር ያስተናግዳል፡፡ በቀበሌ ህዝብ ንብረት እንዴት እንዲህ ታደርጋላችሁ ያልኩት አንድ ኃላፊ ይኽ ድሮ የቀረ አስተሳሰብ ነው፡፡ "ክበቡ አሁን የእኛ ነው" አለኝ፡፡ በየትኛው አዋጅ በማን ውሳኔ ወረሳችሁ ብዬ ብጠይቀው ከግልምጫ ውጪ መልስ አላገኘሁም፡፡

ከዚሁ ክፍለ ከተማ ሳንወጣ ቀበሌ 24 እና 23 ብንሄድ ከችግራቸው በተሻለ የምግብ ዋጋ የቀበሌውን ህዝብ ያገለገሉ፡፡ ቦሌ በቀድሞ ስሙ 1717 የሚባለው ራሱን ወደ ከፍተኛ ሆቴል ቀይሮ ለዝቅተኛ ህብረተሰብ በአነስተኛ ትርፍ ከሚለው መርህ አፈንግጧል፡፡ ኮተቤ፣ ሳሪስ፣ ፒያሳ ብትዘዋወሩ ተመሳሳይ ነገር ነው የምትመለከቱት፡፡ አብዛኛው ክበባት ምግብ ቤቱን፣ ሥጋ ቤቱን ከረንቡላ ቤቱን ወዘተ ለግለሰብ አከራየተውታል፡፡ የተከራየው ግለሰብ የተከራየበትን ዋጋ ለመንግስት ክፍያ "ለመንግሥት ሌቦች" የሚከፍለውን ሁሉ ደምሮ የዋጋ ተመን ያወጣል፡፡ በዚያ የዋጋ ተመን የቀበሌው ነዋሪ እንዲገለገል ይገደዳል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ነዋሪው መዝናኛ ክበቡን እንደተነጠቀ አምኖ የተቀበለ ይመስላል፡፡ ተሻዕሚዎች ያሻቸውን ቢያደረጉም ዝምታን ይመርጣሉ፡፡ ቢሸጡትም ቢለውጡትም አይበርደውም አይሞቀውም፡፡ በገንዘቤ ያቋቋምኩት ወይም በወላጆቼ ገንዘብ የተቋቋመ ነው፡፡ በንብረቴ እንዴት እንዲህ ታደርጋለህ የሚል መንፈስ አይታይም፡፡ አልፎ አልፎ ቢታይም ከቁጥር የሚገባ አይደለም፡፡

በቅርቡ መንግስት የተያያዘው የቀበሌ ክበባት ቦታን ለሀብታም መሸጥ ነው፡፡ ፊት በር በመልካም መስተንግዶ ይታወቅ የነበረው ተሸጦ ቤቱ ፈርሷል፡፡ ሥፍራው ታጥሮ ከተቀመጠ ዓመት አለፈው፡፡ በተለምዶ 22 ማዞሪያ ይባል የነበረው በቀድሞ አጠራር ቦሌ ክ/ከ ቀበሌ 07 መዝናኛ ከአካባቢው መዝኛዎች ሰፊና የተሻለ አገልግሎት የሚሰጥ እንደነበር ብዙዎች ይስማማሉ፡፡ ዛሬ ቦታው ተሸጦ ፈርሷል፡፡ እዚሁ አካባቢ ዘሪሁን ህንፃ ፊት ለፊት የሚገኘው ቀበሌ መዝናኛ ከፈረሰ ሁለት ዓመት ሞልቶታል፡፡ ሌሎች ቀበሌዎችን መጥቀስ ይቻላል፡፡ እነዚህ መዝናኛዎች ሁሉ በፈረሱ ቁጥር ቅሬታ ሲያቀርቡ የሚሰሙት የመዝናኛ ክበቡ ሠራተኞች ብቻ ናቸው፡፡ ሠራተኞቹ በእርግጥ ያሳዝናሉ፡፡ አንዳንዶቹ መዝናኛ ክበቡ ሲቋቋም የጀመሩ ናቸው፡፡ ዕድሜልካቸውን ከእጅ ወደ አፍ የኖሩ ናቸው፡፡ ዕድሜልካቸውን ከእጅ ወደ አፍ የኖሩ ናቸው፡፡ አፍላ ጉልበታቸውን ሁሉ የጨረሱት እዚሁ ቀበሌ መዝናኛ ላይ ነው፡፡ ዕድል የገጠማቸው "የመንግስት ሌቦች" ለአጭር ጊዜ በቀበሌው መዝናኛ ላይ እየተሾሙ ህይወታቸውን እየቀየሩ ሄደዋል፡፡ ሠራተኞቹ ግን ከእጅ ወደ አፍ ኑሮአቸውን ኖረዋል፡፡

ባለፈው ሳምንት 6 ኪሎ አንበሳ ግቢ በምስራቅ አቅጣጫ መግቢያው ፊት ለፊት የሚገኘው አራዳ ክ/ከ ቀበሌ 12 መዝናኛ ክበብ እንዲታሸግና እንዲፈርስ የወረዳ 6 አመራሮች ተገኝተው ነበር፡፡ በሥራቸው 500 ቤተሰብ አለን የሚሉት 83ቱ የመዝናኛ ክበቡ ሠራተኞች ዋይታ ፈጥረው ተመልክተናል፡፡ የአካባቢው ህብረተሰብም በገለልተኝነት ቆሞ ይመለከታቸዋል፡፡ 28 ዓመት በዚሁ መዝናኛ ክበብ አገልግያለሁ የ8 ቤተሰብ ኃላፊ ነኝ የሚሉ አንድ የዕድሜ ባለፀጋ አምርረው ሲያለቅሱ መቅረፀ ድምፃችንና ካሜራችን ላይ ገብተዋል፡፡ ወ/ሮ ሲያለቅሱ ይሉት የነበረው ጉልቤተ ባለቀበት ዘመን ልጆቼን ይዤ ለልመና ሊወጣ ነው፡፡ ምን ልሆን" እያሉ ሲጮሁ ቁጥራቸው ከ80 በላይ ሠራተኞች ወንድና ሴት ሳይሉ ያለቅሳሉ፡፡ ልበደንዳናዎቹ የወረዳ 6 አመራሮች ናቸው ደግሞ የፍኖተ ነፃነት ጋዜጠኞች እንዴት ያነጋግሯቸዋል ብላ ለማዋከብ ሞካከረዋል፡፡

ጽሑፉን ለማጠቃለል በህዝብ ገንዘብ የተቋቋሙት ክበባት ያለአዋጅ የተወረሱ ይመስላል፡፡ ከህዝባዊ አገልግሎትነት ውጪ እየሆኑ ናቸው፡፡ ህዝብ ንብረቱን መቆጣጠር ተስኖታል፡፡ በየደረጃው ያሉ ኃላፊዎች ህዝባዊነት ያጣ የህዝቡ መዝናኛ ክበባትን ከሌቦች መጠበቅ አለባቸው፡፡ የተደራጀ በርካታ ሠራተኛን እየበተኑ ያልተደራጀ ጥቂት ሠራተኛን ለሥራ ተደራጁ ማለቱ ተገቢ ሥራ ነውን? ለህዘብ ንብረት ለህዝብ መብት የሚቆም የሚከራከር የሚጠብቅ ሠራተኞች ያስፈልጉናል፡፡

# ህያው ፊልም ፌስቲቫል ተጠናቀቀ

## - ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ የምስጋና የምስክር ወረቀት ተሰጠው

ህያው ፕሮሞሽን እና ኢንተርቴመንት በኢትዮጵያ የኪነ-ጥበብ ስራ እየሰራ የሚገኝ ድርጅት ህያው ፊልም ፌስቲቫል ከግንቦት 6 እስከ 16 ሲካሄድ የቆየ ሲሆን 10 ያህል የተመረጡ የአማርኛ ፊልሞች ለተመልካች ቀርበዋል፡፡ በመዝጊያ ፕሮግራሙ ላይ በሀገራችን የፊልም አንድስታር ታሪክ አይረሴ ታሪካዊ ውለታ የዋሉ ታላቅ የኢትዮጵያዊ ባለሙያ ከተመልካችና ባለሙያ ከተሰጠ ድምፅ የኢትዮጵያ ፊልም ባለ ውለታነት አዋርድ የመጀመሪያው ባለ ቀለም ፊልም ጉማን የሰሩት ሚሼል ፒፓታኪስ አሸናፊ ሲሆኑ የመጀመሪያው ተዋናያኝ አርቲስት ደበበ እሸቱ፣ አርቲስት ሰላማዊት ገ/ስላሴ፣ አበበ ቀፀላ ሌሎችም ተሻላሚዎ ሆነዋል፡፡ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ፕሮግራሙ እንዲሳካ ድጋፍ በማድረጉ በኪነጥበብ ዘርፍ ለተሰማሩ ያለምንም ክፍያ በራሱ ወጪ እየተከታተለ የሚዲያ ሽፋን በመስጠቱ የምስክር ወረቀት ከማግኘቱም በላይ በኪነ ጥበብ ዘርፍ የሚሰሩት ከ20 በላይ ሚዲያዎችም የምስክር ወረቀት ከአዘጋጆቹ ሲቀበሉ ፌስቲቫሉ ቀጣይነት እንደሚኖረው አዘጋጆቹ ዮሐንስ ጉግሳና ሰለሞን ደርቤ ለዝግጅት ክፍላችን ሲገልፁ ሁልጊዜ በቅርብ ያለ ሰው ብቻ ማስታወስ ዋጋ የሌለው መሆኑንና ለዛሬ ፊልሞች መብዛት (መሠረት የሆኑ ሰው መሸለማቸው አስደሳች መሆኑን አክለው ተገልጻዕል፡፡

# ሣታፈቅረኝ የተሰኘ አዲስ ፊልም ተመረቀ

በአልማዝ ፊልም ፕሮዳክሽን መልቲ ሚዲያ የተዘጋጀው በደራሲ አልጊቱ ታምራት በዳይሬክተር ስንታየሁ ንጉሴ የተሰራው "ሳታፈቅረኝ" አዲስ ፊልም በአይነቱ ለየት ያለ ልብ አንጠልጣይ ፊልም ግንቦት 20 ቀን 2004 በአዲስ አበባና በክልል ከተሞች በግል ሲኒማ ቤቶች በድምቀት ተመረቀ፡፡ በዚሁ ፊልም ላይ ህይወቴ አበበ፣ አበባው መላኩ፣ ቤዘነ ግርማይ፣ አስራት ታደሰ፣ አልጊቱ ታምራት ሌሎችም ወጣትና አንጋፋ ተዋንያኖች ተውነውበታል፡፡ 1፡52 ደቂቃ በሚወስደው ፊልም ላይ አንድ ወጣት ሴት በስራ ፍለጋ ምክንያት የሚደርስባትን ውስብስብ የፈተናና ፍቅር ያሳያል፡፡ ፊልሙን ሰርቶ ለማጠናቀቅ 2 ዓመት ያህል ጊዜ ሲወስድ ከአራት መቶ ሰማንያ ሺህ ብር በላይ (480,000) ወጭ ወቶበታል፡፡ ፊልሙ ከሰኔ ወር ጀምሮ ለህዝብ እንደሚቀርብ ፕሮዲውሰሩ ማንደፍሮ መርሻ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፆል፡፡

# በአንድነት ፓርቲ ...

ከ ገፅ 1 የዞረ....

የአንድነት ፓርቲ ተከላካይ ጠበቃ የሆኑት አቶ ገበየሁ ይርዳው በበኩላቸው ክሱ ምንም ተያያዥነት እንደሌለው መከራከሪያቸውን ያቀረቡ ሲሆን ፍ/ቤቱም የክሱ ሂደት ግንኙነት እንዳለው ለመመርመር እንዲያስችለው የነ አንዱዓለም የክስ መዝገብ እንዲቀርብለት ለግንቦት 17 ቀን 2004 ዓ.ም ትዕዛዝ ሰጥቶ ነበር፡፡

የፌዴራሉ ከፍተኛ ፍ/ቤት በበኩሉ የነ አንዱዓለም አራጌ የክስ መዝገብ ዳኞች እጅ በምርመራ ላይ እንዳለና መላክ እንደማይችል በመጠቆም በምትኩ አቃቤ ህግ የመሰረተው ክስ ግን ሊቀርብ ችሏል፡፡ በዚህም መሰረት ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ ብይን ለመስጠት ለሰኔ 4 ቀን 2004 ዓ.ም ከረፋዱ 4፡00 ሰዓት ተለዋጭ ቀነ ቀጠሮ ሰጥቷል፡፡

## የአደባባይ ምስጢሮች

### መለስ ዜናዊና ቴምብሩ

ሰሞኑን በፌስ ቡክ የተሰራጨው የአደባባይ ምስጢራችን እነሆ፡-የኢትዮጵያ ጠ/ሚኒስቴር አቶ መለስ ዜናዊ የርሳቸዉ ፎቶ ያለበት የፖስታ ቴምብር ለማሳተም ፈለጉና ሰዎቻቸዉን ጠርተው አለም አቀፍ ደረጃውን የጠበቀ ቴምብር እንዲታተምልኝ እፈልጋለሁ ብለው ጥብቅ ትእዛዝ አስተላለፉ፡፡ ቴምብሩም እንደተፈለገው በጥሩ ሁኔታ ታትሞ አቶ መለስም ታትሞ እንዲሰራጭ ተደረገ፡፡ ቴምብሩ በተሰራጨ በጥቂት ቀናቶች በደንብ ማጣበቅ እንደማይችል አቶ መለስ ይሰሙ ጀመር፡፡ በሁኔታዉ እጅግ የተበሳጩት አቶ መለስ ይህንን ጉዳይ በአስቸኳይ አጣሩ ብለው ጥብቅ መመሪያ አስተላለፉ፡፡ አጣሪ ቡድኑም በተለያዩ ፖስታ ቤቶች ካጣሩ በኋላ ለአቶ መለስ ሪፖርት አቀረቡ፡፡ ሪፖርቱም እንዲህ የሚል ነበር፡-በተለያዩ ፖስታ ቤቶች ዙረን በደንብ አጣርተናል፡፡ በቴምብሩ ጥራት ላይ ምንም ችግር የለም፤ችግሩ ያለው አብዛኛዉ ሰዉ ቴምብሩን ለማጣበቅ ምራቁን የሚተፋው በተሳሳተ ጎን መሆኑ ነው!!




### ትዋል ትደር እንጂ አህያ የጅብ ናት

አበው ሲተርቱ የፈለገውን ያህል ጊዜ ቢቆይ ሊቀር የማይችለውን ነገር እንደማይሆን አድርገው ለሚያስቡ ሰዎች በምሳሌ ሲያስረዱ "ትዋል ትደር እንጂ አህያ የጅብ ናት" ይላሉ፡፡ እውነት ነው አህያ በህይወት እያለች ብትበላም የሚበላት ጅብ ነው፡፡ ረጂም ጊዜ ቆይታ ብትሞትም የሚበላት ጅብ ነው፡፡ ምክንያቱ ቤት ውስጥ ብትሞትም ጌታዋ አውጥቶ ለጅብ ይጥላታል፡፡ ጌታዋ ከጅብ ይጠብቃት ይንከባከባት የነበረው በህይወት እስካለች እስካገለገቺው ድረስ ብቻ ነው፡፡

በአቶ መለስ አስተዳደር ህዝብ 21 ዓመት አንብቷል፡፡ ህዝብ እንደ አንድ አገር ህዝብ ሳይሆን እንደባዕድ እንደጠላት እንዲባላ ተደርጓል፡፡ ዜጐች በነፃ ከቦታ ቦታ ተዘዋውረው እንዳይሰሩ ተደንግጓል፡፡ በይፋ አንተ አማራ ነህ፤ ኦሮሞ ነህ፤ አፏከ ነህ እዚህ መሥራት አትችልም እየተባለ ከሥራ ተባሯል፡፡ ከመኖሪያው ተፈናቅሏል፡፡ አገር ተቆርሷል፡፡ አገሪቱ ወደቧን አታለች፡፡ ጥቂት ሎሌዎች ከብረዋል፡፡ ጌታቸውን ከበው ይደሰኩራሉ፡፡ ህዝብ ግን ተርቦ፣ ታርዞ፣ ተዋርዶ ያያቸዋል፡፡ በቅርቡ በአቶ መለስ ላይ በዓለም አቀፍ አደባባይ የገጠማቸው ውርደት የአገር ውርደት ነው፡፡ ትምህርት ሊሆን ይገባል፡፡ እውነት ህዝብ ማሸነፉ የማይቀር ነው፡፡ ትዋል ትደር እንጂ አህያ የጅብ ናት፡፡ እንድንል ተገደናል፡፡

# መቼ ይሆን ለትውልድ የሚታሰበው?



ብስራት ወ/ሚካኤል
afrosonb@gmail.com

ቀን ቀንን እየወለደ ይነጉዳል፡፡ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ጉዳይ ባዕድ መሆን ከጀመሩ ይኸው ሰነባብተዋል፡፡ በተለይ ወጣቱ ትናንት ብቻ ሳይሆን ዛሬም መጠቀሚያ ከመሆን አላለፈም፡፡ ይሄ በገዥው ፓርቲ ብቻ ሳይሆን በተቃዋሚዎችም ተመሳሳይነት አለው፡፡ ነገር ግን በይበልጥ በዚህ ጉዳይ ዋናው ተጠያቂ ኢህአዴግ ነው፡፡ ምክንያቱም ተወደደም ተጠላ፣ ተመርጦም ይሁን አጨበርብሮ ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ ለሚፈጠሩ ችግሮች ሁሉ ግንባር ቀደም ተጠያቂ ነው፡፡ ምክንያቱም መምራትና ማስተዳደር እችላለሁ ብሎ ስልጣን ይዟልና፡፡

በተለይ ኢህአዴግ ከተቃዋሚዎች እጅግ በላቀ ወጣቱን መጠቀሚያ አድርጎታል፤ እያደረገውም ይገኛል ተብሎ በብዛት ይሰማል፡፡ ይህም በምርጫ ወቅት፣ በጦርነት ወቅት ለውጊያ፣ ለይስሙላ ድጋፍ ወቅት (ለተቃውሞ አይፈቀድም) ወጣቱ መጠቀሚያ ነው፡፡ ለምሳሌ የህወሓት አመራሮች እዚህ ለመድረስ ብዙ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ ኢትዮጵያውያን ወጣቶችን አስጨርሷል፤ በስማቸውም ነግዶ አትርፎበታል የሚል ወቀሳ ይቀርብበታል፡፡ የቀድሞ ኢህዴን የአሁኑ ብአዴንም እንዲሁ፡፡ ወጣቱ ግን ስቃዩና መከራው፣ ስደቱና ተስፋቢስነቱ ካለፉት የመንግስት ስርዓቶች በእጅጉ ልቆ ይገኛል፡፡ የሚገርመው ዛሬም ለሚፈልጉት ዓላማ በፈለጉት ቀን የወጣቱን ስነልቦና እና ስብዕና በጊዜያዊ ገንዘብ በመግዛት ይጠቀሙበትና እንደ አገዳ ልጣጭ ይተፉታል፡፡ የወጣቱ ስነልቦናዊም ሆነ አካላዊ መከራና ስቃይ ግን ቀጥሏል፡፡

ወጣቱም ቢሆን ራሱን ለሌሎች መጠቀሚያ አድርጎ አሳልፎ ሰጥቷል፡፡ ይህ እንዳይሆን ከፈለገ ራሱን መመልከት አለበት፡፡ የዚህች ሀገር የከፉ ቀን ደራሽ ነህ ይባልና የመብትና የጥቅም ጉዳይ ሲነሳ ግን ባዕድ ይሆናል፡፡ ኢትዮጵያዊ ወጣት ሁሉ የኢትዮጵያ ሙሉ ባለቤትና ባለመብት እንጂ ባዕድ እንዲሆን ሲደረግ ራሱ ወጣቱ ሊፈቅድ አይገባም፡፡

ነገር ግን ራሱን ለጊዜያዊ ቁሳዊ ጥቅም ስብዕናውን እንደ አሁኑ የሚሸጥ ከሆነ ሁሌም አካላዊና ስነልቦናዊ ባሪያ ይሆናል ማለት ነው፡፡ ይሄ ደግሞ ከሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ ውጭ ነው፡፡ ስለዚህ ወጣቱ በተለያየ መንገድ ስነልቦናው እንዲዳከም ሲደረግ "አይሆንም!" ማለት መልመድ አለበት፡፡

እስኪ ዛሬ ወጣቱ በተለያዩ ደባል ሱሶች ተጠምዶ የስነልቦና የበታችነት (አልችልም የሚለውን) እንዲያንፀባርቅ እንዴት እየተበረታታ እንዳለ በአጭሩ እንይ፡፡ ለዚህም ይረዳ ዘንድ የአዲስ አበባ ከተማን በተለይም ሳሪስን ለአብነት እናንሳ፡፡

ሳሪስ በቀድሞ የመዲናዋ ወረዳ 19 ስትሆን በአሁን ወቅት በንፋስ ስልክ ላፍቶ እና በአቃቂ ቃሊቲ ክፍለ ከተማ ውስጥ ትገኛለች፡፡ በዚህም በደቡብ ኢትዮጵያ በሶማሌ እና በኦሮሚያ ክልል በጋራ ከምትተዳደረዋ የሞያሌ ከተማ ጋር ያመሳስላታል፡፡

በአካባቢውም ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጡ የተለያዩ የግል የንግድ ተቋማት ይገኛሉ፡፡ የትምህርትና የጤናም እንዲሁ፡፡ ከሀገሪቱ የምስራቅና ደቡብ ምስራቅ አካባቢ የሚመጡ ምርቶች (የንግድ እቃዎች) እንዲሁም በተለይ ከወደብ (በአሁን ወቅት ባይኖረንም) የሚመጡ ዕቃዎች ሳሪስን ሳይሳለሙ ለአዲስ አበባም ሆነ ለሌላው የአብዛኛው የሀገራችን ህዝብ አይደርስም፡፡ በዚህ ሁሉ የሳሪስ ነዋሪ በድምቀቷ እንጂ በገቢ ተጠቃሚ ሳይሆን መጠቀሚያ ነው ይባላል፡፡

በተለይ የአካባቢው ወጣት ከመንግስት የሚያገኘው ድጋፍ በደባል ሱስ እንዲጠመድ የሚያበረታታና ነገ ጥገኛ የሆነ ትውልድ እንዲኖር በአዋጅ የተፈቀደ ይመስላል፡፡ ይሄ ባለማወቅ የሚፈፀም ነው ለማለት ግን ይከብዳል፡፡

ነገሩን ግልጽ ለማድረግ ያህል በአካባቢው አሁን በፋሽንነት ከሚታየው "የኮሚኒቲ ፖሊሲንግ" ጥርቅም ውጭ ሁለት ፖሊስ ጣቢያዎች ይገኛሉ፡፡ ከላይ ለመጥቀስ የሞከርኳቸው ክፍለ ከተሞች ቀበሌ (በአሁኑ ወረዳ) መስተዳደሮች እዛው አፍጠው አግጥጠው ይገኛሉ፡፡ እነኚህ መስተዳደሮች ለነዋሪዎች የመንግስትን ፕሮፓጋንዳ እንደ በቀቀን ከማስተጋባት የዘለለ አገልግሎት የሚሰጡ አይመስሉም፡፡

ለዚህም ምክንያት ያልኩትን ልጥቀስላችሁ፡፡ ስፍራው በአዲስ አበባ ትልቁ የጫት መጋዘንና ማከፋፈያ ያለው እዛው ሳሪስ ሲሆን በአሁን ሰዓት መርካቶ ካለው "አብዱ በረዳ" ይበልጣል፡፡ ጫት ማከፋፈያው ፊት ለፊት የንፋስ ስልክ ሳሪስ ፖሊስ ጣቢያ ሲገኝ ጫት በረንዳው ግን በአቃቂ ቃሊቲ ክ/ከተማ ውስጥ ነው የሚገኘው፡፡ ውስጥ ለውስጥ ከዋናው አስፓልት በቅርብ ርቀት ደግሞ የጫት መቃሚያና ሺሻ ቤቶች ይገኛሉ፡፡ እዛው መሀል መስኮት ከፈት ቢያደርጉ መመልከት የሚያስችል የክብሪት ቀፎ የሚመስለው የወረዳው መስተዳደር "ፎቅ" ይገኛል፡፡

እዛው አንድ የመንግስትና በርካታ የግል ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤትን ጨምሮ በዛ ያሉ የመጀሪያ ደረጃ ት/ቤቶች ይገኛሉ፡፡ የጭፈራ ቤቶች ብዛት ደግሞ የቀድሞ ካዛንችስን ያስንቃል፡፡ ከምሽቱ 3 ሰዓት ጀምሮ ከየጭፈራ እና ሆቴሎች ውጭ የወሲብ ደንበኞቻቸውን በጉጉት የሚጠብቁ በርካታ ወጣት እንስቶች ተደርድረው ያገኛሉ፡፡ እነኚህ እንስቶች አብዛኞቹ የአካባቢው ነዋሪ መሆናቸውንና የትምህርት ደረጃቸውም ከ6ኛ-10ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎች መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ከእነኚህ ሴቶች መካከል ብዙዎች ጫት ይቅማሉ፣ ያጨሳሉ፣ ሺሻም እንደሚጠቀሙ ያወጋሉ፡፡ በጐዳና ላይ ወሲብ ንግድ አማካኝነትም የሚፈሩት ኤች አይ ቪ/ ኤድስን ሳይሆን ያልተፈለገ እርግዝናን እንደሆነ በድፍረት ይናገራሉ፡፡ ለምሽት የፈረቃ የጐዳና ህይወት የዳረጋቸውም የቤተሰቦቻቸው የኑሮ መጐሳቆልና የትምህርት ቤት ወጪያቸውን ጨምሮ በቀን አንዴ የሚሹትን የዕለት ጉርስ ለመሙላት እንደሆነ ወጣት ፅጌረዳ እና ወይን እሸት (እንደነሱ ገለፃ) ከሆነ ይናገራሉ፡፡ በዚህ መልኩ ተመሳሳይ አስተያየት የሰጡ ብዙ ቢሆኑም በመቅረፀ ድምፅ መቀረፅንና ስማቸውን መንገር አይፈልጉም፡፡

ወጣት ጀሚላ ደግሞ ከላይ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆኖ ሌላም የተለየ ነገር አላት፡፡ እሷም በጐዳና ላይ ክብርንና ህይወትን ነግዳ ታድራለች፡፡ የዛሬን ለመብላት ነገን መርሳት ይመስል፡፡ በእርግጥ ስትታይ እውነትም ታምራለች፡፡ በዚህም በአካባቢው ሴተኛ አዳሪዎችን ለመጠጥ ንግዳቸው ማድመቂያ የሚያደርጉ ሁለት ባለ ሆቴሎች እነሱ ጋ እንድትሰራ ጠይቀዋት ፈቃደኛ ባለመሆኗ በስፍራው እንዳትታይ እንዳስጠነቀቋት አስታውሳለች፡፡ በተመሳሳይ መልኩ አዘውትራ በምትቆምበት አካባቢ ያለ ሆቴል ውስጥ የሚሰሩ ሴተኛ አዳሪዎችም "በገበያችን መጣሽ" በሚል እንደሚቀናቀኗት ታወጋለች፡፡ ነገር ግን ሳሪስን እንደምሳሌ እናንሳ እንጂ በተለያዩ የአዲስ አበባና የክልል ከተሞች

ወደ ገፅ 14 ይዞራል....

# "ከፖሊስ ዱላ ማን ያድነናል?"

መንገሻ ክሉ

## አንዳንድ ነገሮች

በዚህች ሀገር የሚኖሩ እውነተኛ ዜጐች ሁሉ እጅግ የሚያንገበግባቸውና የሚቆጨባቸው በርካታ ነገሮች አሉ፡፡ ጥቂት የምስራቅ አፍሪካ ሀገራትን በመዟዟር ያየው ጓደኛዬ በነዚህ ሀገራት ውስጥ ምንም ያህል የከፉ ጉዳት ቢደርስባቸው ተቆርቋሪና ተሟጋች መንግስት የሌላቸው ኢትዮጵያውያን ብቻ መሆናቸውን አጫውቶኛል፡፡ በአረብ ሀገራት እጅግ አሰቃቂ አደጋ ለሚደርስባቸው ውድ እህቶቻችን ሀዘኔታ የማይሠማቸው የፖለቲካ መሪዎቻችን ምንም ቁጭትና ቁራጥ ተቆርቋሪነት እንደሌለቸው ባየን ጊዜ ሁሉ ምነው እግዚአብሄር እንደንጉስ ዳዊት በፊቱ ቆሞ "ይህንን ግራና ቀኙን የማያውቅ ህዝብ ከምትቀጣ እኔን ግደለኝ" የሚል መሪ ቢሰጠን እያልን እንቆጫለን፡፡ አንጀታችን በጥልቅ ሐዘን እየተበላ ብቻ አንዳንድ ነገሮችን እያነሳን እንቆጭ ካልን

ከሠባት አመታት በፊት ባነበብኩት መረጃ አሜሪካን ሀገር ከሚኖሩ አፍሪካውያን በዕውቀት ሠራተኝነት / knowledge workers/ ኢትዮጵያውያን አንደኛ እንደነበሩ አስታውሳለሁ፡፡ እንደ ኢንጀነር ቅጣው እጅጉ ያሉ እንደ አንድ ሀገር ሊጠሩ የሚችሉ ሰዎች ለዚህች ሀገር ምንም ሳይፈይዱ ማለፋቸውን ስታስቡት እጅግ ያስቆጫል፡፡ በአንድ ወቅት ከአሜሪካ በያመቱ ወደ ሀገር ቤት በመምጣት ነፃ ህክምና ይሰጡ ከነበሩ ዶክተሮች አንዱ ወንድማችን በኛ ቴሌቪዥን እንዲህ ብሎ ነበር፡፡ "ኢትዮጵያ በውጭ ሀገራት በሁሉም ዘርፍ ያሏት ምሁራንና ባለሀብቶች ቅንጅት ፈጥረው ለሀገራቸው በዘላቂነት ቢሰሩ ይህች ሀገር ከአውሮፓውያን የስልጣኔ ዕድገት ደረጃ ላይ ለመድረስ ሃያ አመታት ብቻ ይበቋታል" ነበር የለው፡፡ ከዛሬ ሰባት አመታት በፊት ማለት ነው፡፡ ታዲያ ዛሬ ላይ ሆናችሁ ዶክተሩ ያለውን ስታስቡ ትቆጫላችሁ፡፡ ከሀገር ሁለንተናዊ ተሃድሶና ዕድገት ይልቅ ለፖለቲካ ስልጣናቸው የሚጋደሉ መሪዎቻችን ይህንን ሊያደርጉ አይችሉምና፡፡

በአፋር ክልል ብቻ ያለን ዕምቅ ተፈጥሮአዊ ሀብት መላውን አፍሪካ በአውሮፓውያን የኑሮ ደረጃ ልክ ለአርባ ዓመታት ሊያኖራቸው እንደሚችል ስትሰሙና ሁኔታ ስታዩ ኢትዮጵያ ለታረስ ከሚችለው መሬቷ 5% በላይ ማረስ ባለመቻሉ ለአብዛኛው ዜጋ እንጀራ መብላት ጭንቅ ሆኖበት ስታዩ ትቆጫላችሁ፡፡

ደርግ ስልጣን ላይ በቆየባቸው ዓመታት ለጦርነቱ በየቀኑ ያወጣ የነበረው ወጪ በአስራ ሰባት ዓመታት ሲሰላ ያወጣው ወጭ በቀጥታ ለኢኮኖሚው ዕድገት ውሎ ቢሆን ኖሮ ዛሬ ኢትዮጵያ አንድ አውሮፓዊ ሀገር ባለበት የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃ ላይ መገኘት ትችል እንደነበር ስትሰሙ ቁጭት ያንገበግባችኋል፡፡ ወያኔና ሻዕቢያስ ለዚያ ሁሉ ሀብትና ጊዜ ውድመት ምክንያት ሆነው ሲያልቁ ለዚህች ሀገር ከድህነት ሌላ ምን አመጡለት?

## "የዜግነት ክብር ናፈቀን"

ከላይ የጠቀስኳቸውን አንዳንድ ቁጭቶቻችንን እግረ መንገድ አነሳሁ እንጂ መነሻዬማ ሌላ ቁጭት ነበር፡፡ አንድ ዜጋ ጥፋት ይገኝበትም አይገኝበትም ጉዳዩ በህግ ሳይዳኝ በፖሊስ ዱላ ቦክስና ከስክስ ጫማ ተደብድቦ ከአንገቱ በላይ ጃርት የበላው ዱባ መስሎ ስታዩት ልባችሁ በሐዘን ይደማና መቼ ነው ለዜጐች ክብር ያለው መንግስት የሚኖረን ብላችሁ ትቆጫላችሁ፡፡ ባለቤቱ የናቀው በቅሎ አህያ ነው ይሉታል፤ እንደሚባለው የሀገሬው መሪ የናቀውና ያላከበረው ህዝብ አንድ ፖሊስ እንዴት ሊያከብረው ይችላል? እርግጥ ነው ከሸምቅ ውጊያ ወጥቶ ስልጣን በያዘ መንግስት የተፈራና የተከበረ ህዝብ የለም፡፡

ግንቦት ሰባት ምሽት ላይ ነው 1997 አይደለም፡፡ 2004 ዓ.ም መገናኛ ድልድዩ አቅራቢያ ሰው እየጠበቅሁ ሳለሁ ድንገት ጩኸት በረከተና ጠጋ አልኩ፡፡ አንድ እድሜው ሠላሳ የሚሆነው ወጣት በሦስት ፖሊሶች ሲደበደብ ባይ እንዲህ አይነት ነገር በየቀኑ ማየት የተለመደ ቢሆንም አንጀቴ ተላወሰ፡፡ የተሰበሰብ ነው ሁላችንም "ምን አጥፍቶ ነው እንዲህ የሚወገረው?" ብለን አልጠየቅንም፤ ምክንያቱም የትኛውም ጥፋት እንዲህ እንደማያስወግር እናውቃለንና፡፡ ወጣቱ በአካባቢው የመንገድ ንግድ ላይ ተገኝቶ እንደሆነና የሚሸጣቸው ልብሶች ተጠቅልለው እንዲሁም ሁለት ከርሱ ጋር የነበሩ ህፃናት ልጆቹም አጠገባችን በቆመው የፖሊስ መኪና ላይ ተጭነው አየን፤ በቦታው የነበረውን ሰው ይበልጥ ያሣዘነው ደግሞ ህፃናት ልጆቹ እያዩት በፖሊሶቹ ያን ያህል መጠፍጠፉና መንገላታቱ ነበር፡፡ ወጣቱ ፖሊሶች ወደ መኪና ሊጭኑት ቢታገሉም እሱ ግን ከመኪናው ጐማ ስር በመግባት "መኪናውን ንዱትና ግደሉኝ ምን አድርግ ነው የምትሉኝ? እሺ ምን ሠርቼ ልብላ? በቃ ግደሉኝና ገላግሉኝ" ሲል ፖሊሶቹ ያለምንም ርህራሄ መደብደባቸውን ቀጠሉ፡፡ ይሄኔ በቦታው የነበረው ሰው "አትደብድቡት አትደብድቡት" ማለቱን ሲገፋበት ወጣቱን በኃይል የፖሊስ መኪናው ላይ ጭነውት ሄዱ፡፡ እኔ ግን ቀጠሮዬን ረስቼ በቁጭት ተንገበገብኩ፤ ህዝብ እንጂ ገዢ መደብ የሣንቲም ቁራጭ እንደማይከፍላቸው የማያስተውሉት፡፡ ፖሊሶቻችን እስከመቼ ነው ልጅ አዋቂ የተማረ ያልተማረ ሳይሉ መቀጥቀጣቸውን የሚቀጥሉት? ብዬ ስቆጭና ከፖሊሶቻችን ወፍራም ዱላና ጡጫ እንደማናመልጥ አሰብኩና ከፖሊስ ዱላ ማን ያድነናል? እያልኩ መንገዱን ቀጠልኩ፡፡ ከቀጠሮዬ ጉዳይ ይልቅ ይህ ጥያቄ ከብዶብኝ፡፡

# ኪነ-ጥበብ ...

ከ ገፅ 6 የዞረ....

ተነበውላቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል እንደ ምሳሌ ይስማዕከ ወርቁ፣ ተመስገን ደሳለኝ፣ በዕውቀቱ ስዩም መፅሐፎቻቸው በሸሚያ ከሚነበቡላቸው ወጣት ደራሲያን መካከል ናቸው፡፡

ከወዲያኛዎችም ቢሆን እነ ሀዲስ አለማየሁ፣ በዓሉ ግርማ፣ ዘርይሁን ብርሃኑና አቤ ጉበኛ የመሳሰሉ በጨለማ ዘመን ብርሃን ፈንጣቂ ስራዎችን ያበረከቱ አንፃባራቂ ኮከቦች ናቸው፡፡ እና የራስን ፍርሃት፣ አጥርቶ የማየት ችግር በህዝብ ማላከክ ብዙ ርቀት አያስኬድም፡፡

አርቲስቱ ህዝቡ ውስጥ ዘልቆ በመግባት ደስታውን፣ ሀዘኑን፣ ጥጋቡን፣ ችግሩን፣ ሰርጉን፣ ልቅሶውን፣ ፖለቲካውን፣ ወጉን ፈልፍሎ በማምጣት መልሶ ለህዝቡ መስጠት የኪነ-ጥበብ ባለሞያው ድርሻ ነው፡፡

የኪነ-ጥበብ ባለሞያው የህዝብን አንቀሳቃሽነት ሚናውን መወጣት ይገባዋል፡፡ ይሄን ማድረግ የሚችለው ግን አርቲስት ነኝ የሚለውን ስም አጥብቆ የሚወደው የሀገሬ ከያኒ፣ ዘፋኝ፣ ሰዓሊ፣ ቀራፂ፣ እስክስታ ወራጅ፣ ቲያትረኛ ሁሉ በመጀመሪያ የራሱን ነፃነት ሲያውጅ ነው፡፡ ነፃነት ከሌለውና ነፃነቱን አሳልፎ ከሰጠ የኪነ-ጥበብ ሰው ምን ይጠበቃል? ራሱን "ጐመን በጤና" በሚል ተረት ያጠረ አርቲስት የህዝቡን ፍላጐት እንዴት ያውቃል? ከየትስ ያመጣዋል?

ውድቀቱ ይሄው ነው፡፡ ውድቀቱ አሁን እያየነው ያለነው ነው፡፡ ዘፈን በሌለበት እስክስታ መውረድ፡፡ አርቲስቱ ወደራሱ መመልከት እንዳለበት ይሰማኛል፡፡ የቆመበት ድንጋይ ትክክል መሆኑን ማረጋገጥም የራሱ ድርሻ ነው፡፡ በፍርሃት መጋረጃ ተሸፍኖ ወደ ህዝብ መጠቆም ተገቢም፣ ትክክልም አይደለም፡፡

እንደ ማጠቃለያም አንድ የፈረንጅ ተረት ልጠቀም፡፡ "The proof of the pudy is in the eating" ገንፎው ጥሩ ነው የሚባለው ጥርግ ተደርጐ ሲበላ ነው፡፡ አርቲስቶች ሆይ የምታቀርቡትን ምግብ ጥርግ አድርገን እንድንበላላችሁ አጣፋጥችሁ ስሩት፡፡

# ተመስገን! እሱስ ቢሆን ከማን መጣ?

ብስራት ወ/ሚካኤል
afrosonb@gmail.com

መቼም እናንተ እህ! ... ኳላችሁ ብዙ ታወራላችሁ። በእርግጥ አንዱ ዓላማችን እናንተ በነፃነት የተሰማችሁን እንድትናገሩና ላቅ ካለም ሰላማዊ ሰልፍ በመውጣት ሀሳባችሁን እንድትገልፁ ነው፡፡ ይህንንም ቢሆን በዝረራ ምርጫ ባሸንፍንበት 2002 ዓ.ም ወቅትና በህዳሴ (ሚሊኒየም) ግድብ ጅማሮ ብስራት ተሰልፋችሁ የለ? እና ሌላ ምን ፈለጋችሁ? ወይ እናንተ ዴሞክራሲ እኮ ያልቃል፤ ቆጥበን መጠቀም ካልቻልን አደጋ አለው፡፡ ገባችሁ?

እኛ ድላችን በትግላችን፤ ትግላችን ለኑሮአችንና ለራሳችን። ይሞታል ታዲያ! ያው ታውቁ የለ? የሞትነውም እኛ ያለነውም እኛ፤ አንድዬ(እናንተን አላልኩም፤ምን አግብቷችሁ) ከፈቀደ የምንኖረውም እኛ ምን ታመጣላችሁ? እኛ በዱር በገደሉ ስንቆስል ስንደማ ምድረ ቦዘኔ እና ዋልጌ ሁላ በየከተማው የጣፈጠ እየበላሽ ታውደለድይ አልነበር? ዛሬ እኛ ስልጣን ላይ ስንወጣ አይናችሁ ደም ይለብሳል፡፡ ምን ይሁን ብላችሁ ነው እንዲህ በቅናት እርር ድብን የምትሉት?

ቆይማ! እኛ በረሃ ለበረሃ ከላይ ታች በተለይ ከደደቢት እስከ ናቅፋ ከዚህ ባስ ሲልም ሱዳን የተንከራተትነው ስንት ዓመት እንደሆነ ይገባችኋል? ok! 17 ዓመት፡፡ ስልጣን ከያዝን ገና 21 ዓመት ይኸው ትናንት ደፈንን፡፡ ልብ በሉ፤ የታገልነው በበረሃ መሆኑን እንዳትረሱ፡፡ ይህንንም ገና አወራርደን አልጨረስንም፡፡ ምክንያቱም ያው የበረሃን ነገር ታውቁት የለ?

ወይ ጉድ! ዙሪያ ጥምጥም ሄድኩ እኮ! ምነው እቴ! እኛ ይህን "ጣፋጭ" ስልጣን የያዝነው 17 ዓመት በረሃ ቆይተን ስለሆነ በሁለት ተባዝቶ 34 ዓመት እስኪሞላን ስልጣን አንለቅም! አይገባችሁም እንዴ? ታዲያ ገና መች አወራረድን? ገና እኮ 21ኛ ዓመታችንን ነው ያከበርነው፡፡ስለዚህ ታገሱን አቦ!

እንደውም እውነቱን እናውራ ካልን በጣት ከሚቆጠሩት ውጭ "ተቃዋሚ" ነን የሚሉት አጠገባቸው ፊኛ ሲፈነዳና አይጥ ኮሽ ካደረገች ይደናበራሉ፡፡ አንዳንዴ በኑሮ ውድነት ምክንያት እሚያስቅ ነገር ስናጣ "ተቃዋሚዎችን" ምንም ሳያደርጉ ዋ! ካልናቸው ውሃ ውስጥ የገባች አይጥ ይመስላሉ፡፡ አንዳንዴ መግቢያ ጉዳጓድ ሁሉ ይጠፋቸዋል፡፡ ግን እኮ ያሉት አዲስ አበባ ውስጥ ነው፡፡ ቂ.ቂ.ቂ....፡፡ ታዲያ እነኚህ ናቸው እኛን የሚተቹና ራሳቸውን ነፃ ሳያውጡ ስለህዝብ ነፃነት ለመከራከር የሚዳዳቸው? ሰማህ ጎበዝ! እኛ ቢያንስ ህዝቡን ነፃ ባናወጣም ራሳችንን ነፃ አውጥተን በምቾት እየኖርን ነው፡፡ ገባህ?

ነፃነት ዝም ብሎ በስጦታ የሚገኝ ይመስል ቢሮ ቁጭ ብሎ ፖተሊካ እንጂ ፖለቲካ የለም፡፡ የማንም ፈሪ ሁላ! አዳሜ ገና ለገና እታሰራለሁ ብሎ በቢሮ የሚያጉረመርም ሁሉ ፖለቲከኛ ነኝ ይላል፡፡

አቦ! አሁን በዓላችንን እናከብርበት አትነጅሱን! ነጃሳ ሁላ! አንዳንድ አሽሟጣጮች በግንቦት 20 የድል በዓላችን ይቀናሉ፡፡ አቤት ቅናት፣ አቤት ... አቤት፡፡ የእኛ ሲሆን አይናቸው ይቀላል ወይ ሀበሻ! ምነው ያኔ ንጉሱ ጥቅምት 23 በዓለ ንግስናቸውን ልደት ደግሰው ያከብሩ አልነበረም? እሳቸውን ሲቃወሙ የነበሩት ደርጎችስ መስከረም 2 ቀንን አብዮታዊ በዓላቸውን ያከብሩ አልነበር እንዴ?

እኛስ ከማን እናንሳለን? ቅጥል በሉ! እንጂ ደግሰን በደማቅ ሥነ-ሥርዓጥ በዓላችን አክብረናል፡፡ ለማድመቂያማ እድሜ ለኢ-ቴቪ ምን ተስኖት፡፡ በተለይ ለበዓላችን ድምቀት ደፋ ቀና ላሉት ልማታዊ ጋዜጠኞች አንድ ሙሉ ልብስና ሌላ ሽልማት እናበረክትላችኋለን፡፡ ይገባችኋልና የእኛ በቀቀኖች፡፡

በተለይ አንዳንድ ወረኞች እኛ ለዜጎቻችን ያበረከትነውን አስተዋፅዖ ወደ ጎን በመተው ስለምናከብረው በዓል ይናገራሉ፡፡ ትዝ ይላችኋል! ባለፈው ቅዳሜ ግንቦት 20 በዓላችንን ምክንያት በማድረግ የአዲስ አበባ የኢህአዴግ ሴቶች ሊግ በግዙፉ ስታዲዮም 35ሺህ ሰዎች የባህል ልብስ ለብሰው እንዲገኙ ጋብዘዋል፡፡ በርግጥ እኔም ተጠርቼ ነበር፤ ነገር ግን "የባህል ልብስ ለብሳችሁ" የሚለው ቅድመ ሁኔታ ስላልተመቸኝ ቀረሁ፤ ውይ በሞትኩት! ቅጣት ይኖረው ይሆን? አደራ መቅረቴን እንዳትናገሩ፡፡

ምክንያቱም ያቺ ጉርሻ ትቀርብኛለቻ! ጎሽ የኔ እመቤት! የቡና ጠጡ እና ---- ሴቶች ማህበር እንኳን ለዚህ አበቃችሁ፤ ወላድ በድባብ ትሂድ፡፡ ግን የወንዶች፣ የወጣቶች፣ የህፃናትና የአዛውንቶች ሊግ በተመሳሳይ መልኩ ባለማክበራቸው ቅር ብሎኛል፡፡ ገንዘብ ከሆነ ያው ታውቁ የለ? ችግር የለብንም! ዕድሜ ለፀሐዩ መንግሥጣችንና ለ5 ዓመቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ፡፡ ድሮስ ምን ጎድሎባችሁ?

ለማንኛውም ሰሞኑን ግለሂስ ታወርዳላችሁ እሺ! አለበለዚያ በኪራይ ሰብሳቢነት ማህተም መሸኛ እንሰጣችኋለን፡፡ ደግሞ ያለምግብና ውሃ ግንቦት 20 ይላሉ፤ አንዳንድ ፀረ ልማት ኃይሎች አጼ ኃይለ ሥላሴ እና ደርግ ልደታቸውን ሲያከብሩ ዜጎች የሚበሉት አጥተው ነበር ይላሉ፡፡ ይሄ ሁሉ የሆነው እኮ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰሞኑን ከፍቷቸው እንደድሮ ባለመገኘታቸው ነው፡፡ቻሉት እሺ!

ሰሞኑን ደግሞ እኛ ግንቦት 20 በዓለ ልደታችንን ስናከብር በተለይ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ውሃ አጥተው ጀርካን ተሸክመው ሲራወጡ ለምግብ ዘይት ግዥ የሚሄዱ ይመስላል ይላሉ፡፡ ይህንንም አስመልክቶ ውሃ ለግንቦት 20 ክብረ በዓለ ሄዳ ነው እያሉ ያማሉ፤ እሷ ግን ለጊዜው የ2 ዓመት ፈቃድ ሞልታ እረፍት ላይ ነበረች፡፡ የምግብ ዋጋ መወደዱንም ከእኛ በዓል ጋር የሚያያዙት አሉ፡፡ አሁንስ ፈረደብን ውይ! ሌላ ስራ የላቸውም እንዴ! የግድ ለወረኞች ምን እናድርግ? በየቦታው የሚያማ አይጠፋም፡፡

ቆይ! አሁን ነፃነት አጥተናል፣ ኑሮ ተወዷል፣ተራብን፣ውሃ ጠፍቷል፣ መጠለያ አጣን፣ መብታችንን ተነፈግን፣ ታሰርን፣ ተደበደብን፣. . . ይላሉ፡፡ ይሄም ቢሆን የልማታዊ መንግስታችን ውጤት ነው፡፡ እሱስ ቢሆን ከማን መጣ! ተመስገን ነው፡፡ መቼም እናንተ ተመስገን አታውቁም፡፡ አሁንስ በዛ! ጉበዝ፡፡ Anyways ሰሞኑን የድጋፍ ሰልፋችሁን ቀጥሉበትና ለተቃውሞ ግን ጊዜ ስጡን፡፡ ምክንያቱም ልክ እንደ ዴሞክራሲያችን የተቃውሞ ሰልፍም ቢሆን ብዙ ጊዜ የሚጠይቅና በሂደት የሚስተካከል ይሆናል፡፡ በርግጥ በ1997 ዓ.ም በስህተት ፈቅደን ነበር፤ አሁን ግን ያው እንደምታውቁት ነው፡፡

ለማንኛውም በ2005 ዓ.ም የሞት ሽረት የሆነው የአዲስ አበባ ምርጫችን ስላለ ቢከፋችሁም ዝም በሉ፡፡ ካሸነፍን በባቡር ትሄዳላችሁ፣ ኮንደሚኒየም ያለኮንደም ይሰጣችኋል፡፡ ባንችል እንኳ በስዕልም ቢሆን እናቀርብላችኋለን እሺ! እስከዚያው ችግራችሁን ዋጡና ኢቴቪን ተመልከቱ፡፡

# የኢህአዴግ ፖለቲካና የህግ ባለሙያዎች ዝምታ

ታደሰ ፍስሃ

ጉዳዩ እንኳን በውስጤ መክረር ከጀመረ ሰንብቷል፡፡ አሁን ግን ፀረ ኢህአዴግ ስለሆነው ወይም ስለሚመስለው የነቃ ኢትዮጵያዊ ሳስብ ብሽቅ ከሚያደርጉኝ አያሌ ነገሮች ውስጥ ይሄ አንዱ እንደሆነ ነው፡፡ በዚህ የመከራ ሂወት ያልተበረዘች ትርፍራፊ ዕውቀት ካለችኝ እሷን አንጠፍጥፌ ፖለቲካንና የህዝብን ጉዳይ በአፍጢሙ ደፍተው በየጓደቻው ስለተደበቁ የህግ ባለሙያዎቻችን መፃፍ ካሰብኩ በጣም እረዥም ጊዜዬ ነው፡፡

ያዘገየኝ እና ሀሳቤን በቶሎ እዳልገልጽ ያደረገኝ የሰው አፍ ፍራቻ ጭምር ነው፡፡ በኢትዮጵያ ፖለቲካ ወይም የፕሬስ ሥራ ውስጥ አንድ መጥፎ ደዌ ይኸው ነው፡፡ ሁልጊዜም ህዝቡም ወይም የምንጽፍለት ወገን የሚያስገፈልገውንና የሚያስደስተውን ብቻ መፃፍ ይዘወተራል፡፡ እውነት ቢሆን እንኳን ህዝብን የሚያስቆጣ ወይም የሚያስኮርፍና የሚያስተች ከሆነ ለመጻፍና ለመናገር እንሸሻለን፡፡ ብቻ በጣፈጠና በበጎ አደራደር ለዚያውም ለህግ ባለሙያዎች ሀሳብን ማቅረብ እንደፈተና ነው፡፡ እነሱም ይሆኑ ሌሎች እኔ ተተኪ ፖለቲከኛ ለመሆን የምውተረተረውን ወጣት ብድግ ብለው በሚጽፏቸው መልሶች አፈር ድሜ ቢያስግጡኝ በምን አቅሜ ልሸከመው? ነገ እዚህ ህዝብ ፊት በየትኛው ወኔዬ ልናገር ነው? የኛ ሀገር ቁልምም ፖለቲካ እንኳንስ ለኔ ቢጤው ለአዋቂዎቹም ያስቸገረ ቢሆንም ልሞክረው፡፡

እራሱ ቆስሎ ጥቂት ፖለቲከኞቻችንና ጋዜጠኞችን ያቆሰለውን የቆሰለ ፖለቲካችንን ለማከምና የሞተ ፖለቲካችን ነብስ ለመዝራት የኢህአዴግን ጠንቅቆ ማወቅ ግድ ስለሆነ የህግ ባለሙያዎች ተሳትፎ ወሳኝ ነው፡፡ ከኢህአዴግ ጋር በምንገጥማቸው ማናቸውም የፖለቲካ ግብግብ ከእቁብተኞች (ከመንደር ምሬት) የፖለቲካ ስሞታ ወቶ ወደ አደባባይና መድረክ በመግባት የኢህአዴግን አዋጆች እያብጠረጠሩ የሚተቹ መንግስት ለጭቆና በሚጠቀምባቸው ህግ መሰል መሳሪያዎች ላይ ደግሞ እየተከታተለ የሚያረክስ አደጋዎችን አስቀድሞ በመተንበይ ወገንን የሚታደግ የህግ ባለሙያ እዚች ሀገር ያስፈልጋታል፡፡

ህግ በባህሪው እንኳን "ለዚህ ተራ ህዝብ" ወይም ላልተማረ ቀርቶ ለህግ ባለሙያዎች አጨቃጫቂ፣ አነታራኪ በአተረጓጎም ወይም በአቀባበል የማያስማማ ነው፡፡ ህጉ የህግ አውጪውን ልቦና ግምት እንድንመረምር ግድ የሚል የሀገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ እንድናስታውስ የባለጉዳዮችን ጥያቄና ፍላጎት ከግምት እድንናስገባ የሚያስገድድ ብዙ ምርምር ብዙ ንባብ የሚጠይቅ አሻሚ አንዳንዴም መልስ የለሽ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ አንፃር በሀገሪቱ ላይ የሚወጡትን ህጎች የሚመረምሩና የሚያስፈፅሙ ባግባቡ መተርጎማቸውን አጣርተው የሚተቹ ለህዝብ ሰላም እና ነፃነት የሚመቹ መሆናቸውንና ጨቋኝና አፋኝ እንዳልሆኑ የሚያጠኑና የዜጐችን መብት ማስከበራቸውን የሚከታተሉ በቂ የሕግ ባለሙያዎች በፖለቲካው መስክ መሰማራት ይኖርባቸዋል ብዬ አምናለሁ፡፡ ካለበለዚያ ግን ህገ መንግስቱን ተከትሎ የምርጫ የሽብርተኛ የሙስናና ሌሎችም ፖለቲካና ኢኮኖሚያዊ ህግጋትም የመንግስት አዋጆችና ደንቦችን የማውጣትና የማስፈፀም የመተርጎም ጉዳይ አቶ ኃ/ማርያምና አቶ መለስ ይለማመዱባቸው የሚሉ ነው የሚመስለው (Lafayette) የተሰኘ የመካከለኛው ክፍለ ዘመን የፈረንሳይ ፀሐይ "አምባገነኖች አገዛዛቸው ዴሞክራሳዊ እንዲመስል በሌሎች ዘንድ ዴሞክራሲያዊ የሚያስመስሉ ተግባራትን ይፈጽማሉ" ሲል መፃፌ አምባገነኖች የሚያደርጉትን ህጉ እንዲፈቅድላቸው እንዲደረግ የማይፈልጉትን ህጉ እንዲከላከል በማስቀመጥ እንጂ ዝም ብለው በደፈናው የሰውን መብት ላይ ጉብ አይሉም ማለቱ ነው፡፡ ደርግም ሆነ ኢህአዴግ አምባገነንነትንና ግፍን ፈፀሙ ስንል ለሚፈፅሟቸው የአምባገነንነትና ኢ-ሰባዊ ተግባራት የተፃፈም ያልተፃፈ ህግጋትን ወይም አዋጆችን መሠረት አድርገው በመጥቀስ የመገናኛ ብዙሃን እየለፈለፉ እና ምክንያት ለማስመሰል እየጣሩ ስርዓታቸው ህግ ናቸው ብለው እንደ ሚያምኑባቸው በመመራት እንጂ እንዲያው ከመሬት እየተነሱ አይደለም፡፡ በመሠረቱ ደርግም ይሁን ኢህአዴግ መንግስት ሆንን ሲሉ ለዓለምም ይሁን ለእኛ መንግስት በሚያስመስል ህግጋትና ስርዓት ውስጥ በእኛ ወይም ከእኛ በወጡ "የውስጥ አርበኞች" ታጅበው እያለፉ እንጂ ብድግ እያሉ በባዶ ሜዳ አልነገሱብንም፡፡ ስለዚህ የተከረቸመውን የኢህአዴግ ፖለቲካ በርጋግዶ የሚገባ ህጉን ፈቶ የሚገባጥሙ ጠንካራ የህግ ባለሙያዎች ወይም ጠበቃዎች ከሌሉን የኢህአዴግን ቆስሎ ያቆሰለ የፖለቲካን መርዝ የሚያረክስ "የኢህአዴግን ትእቢትና ጡንቻ" ያፈረጠመውን ዝምታችንን የሚሰባብሩ አንደበታቸው የሰላ የሕግ ባለሙያዎች በብዛትና በጥራት ወደ ፖለቲካው መድረክ በመምጣት ኢህአዴግ ጋዜጠኞች የከሰስ እለት ብቻ ሳይሆን እራሳቸው ቀድመው ሕዝብና ፓሪቲያችን ተጎዳ ብለው ኢህአዴግን "በኢህአዴግ ፍርድ ቤት" ሙግት የሚገጥሙ የሕግ ባለሙያዎች ካልኖሩን ብዙ ርቀት መጓዝ አይቻልም፡፡ የኢህአዴግን የተሰበረ ፖለቲካ የሚጠግን የህግ ወጌሻ በለሌለበት ሀገር የሚሊዮኖች ሕይወት እንደተሰበረና እንደተቀጠፈ ሕይወታችንን እንገፋለን በእርግጥ የኢትዮጵያ አብዮት እስካሁን ግቡን እንዳልመታ ይልቅስ ብዙዎች የሞቱበት አብዮት በስተመጨረሻ እንደ ኢህአዴግ ያሉ ጉዶችን እንዳመጣብን ተደጋግሞ ይነጋራል፡፡ ከመወለዴ በፊት ስለነበረው ስለቀድሞ ጊዜ የፖለቲካ ትግል እና ስለቀድሞ የፖለቲካ ተዋንያኖች በዚህ ጽሁፍ ብዙ ማንሳት አልፈልግም እነሱ መራራ ትዝታ ይኖራቸዋልና፡፡ በተለይ ኢህአዴግ ስልጣን ከያዘ ወዲህ ስላለው ስናገር በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ተቃዋሚው ሃይል በምርጫ አሸንፎ በኢህአዴግ እፍረት የድል ባለቤት ባይሆንም ጠንካራ የሚባል ፉክክር አድርገው በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ቢያገኝም የስልጣን ባለቤት ላለመሆናቸው እንደምክንያት የሚነሳው

ወደ ገፅ 15 ይዞራል....

# አሁንም ከ8 ዓመታት በኋላ ማረፊያ ያጣው ተባበሩ ወይም ተሰባበሩ!!

ብሩክ ከበደ

ፓርቲ የሚለውን በአንድ ፕሮግራም ስር የሚሰባሰቡ ወይም የተሰባሰቡ ሰዎች የሚመሠርቱትን ቡድን ለተራው ህዝብ ሳይቀር በማስተዋወቅ በኩል የ1966 ዓ.ም ህዝባዊው አብዮት ቀዳሚውን ሥፍራ ይይዛል፡፡ በዚህ አብዮት ማግስት ሠራተኛውን፣ ምሁሩን ወታደሩን፣ ተማሪውን እንወክላለን የሚሉ በርካታ ፖለቲካ ፓርቲዎች እንደ አሸንፈልተው የነበረ ቢሆንም ሁሉንም በኃይል ደፍጥጦ አንድ ወጥ ግዙፍ የሠራተኛ ፓርቲ ከሰሜን ኮሪያና ሩሲያ በተደረገ ሁለገብ ዕርዳታ በመፍጠሩ በኩል ደርግ (ኢሰፓ) ተሳክቶለታል፡፡

በተለይ በሥነ ምግባርና ዕውቀት የታሸ ትውልድ ለመጥፋቱ መንስኤ የሆኑት ኢሕአፓ፣ መኢሶን ወዘተ የሚሰኙ ፖለቲካ ፓርቲዎች በዛ ትውልድ መንፈስ ያስቀመጡት አሉታዊ ስሜት እንዲህ በቀላሉ የሚሻር አይደለም፡፡ ይህም በመሆኑ መስከረም 2 የአብዮት፣ ሚያዚያ 23 የወዝ (ላብ) አደር፣ ማርች 8 የሴቶች ቀን ፓርቲው (ኢሠፓ) መደበኛና አስቸኳይ እንዲሁም ብሔራዊ ሸንጎ አባላት የሚያካሄዱትን ስብሰባ ጨምሮ የፓርቲው መሪ ኮ/መንግስቱ ኃ/ማርያም በሬዲዮና ቴሌቪዥን ረጅም ንግግራቸውን ሲያቀርቡ፤ በየአደባባዩ በሚሰቀሉ ባነሮች፤ በየግድግዳው በሚፃፉ ጥቅሶችና መፈክሮች ፓርቲው ይህን አድርጐ፤ ይህን አስቦ የሚሉት ቃላቶች በስፋት ስለሚደጋገሙ ህዝብ ከመሠላቸቱም በላይ ፓርቲ የሚለውን ቃል ማድመጥ የማይፈልግበት ደረጃ ላይ ደርሶ እንደነበር የቅርብ ጊዜ ክስተት ነው፡፡

ይህው በተለያዩ የሀገሪቷ ክፍሎች የሚኖሩና በአንድ የሀገሪቷ ባንዲራ ሥር ተሰባስበው በተለያየ ሙያ፣ ዕውቀት፣ ሀይማኖት፣ ዕድሜ ወዘተ የሚገኙ አባላቶቹን በዘር፣ ቋንቋ፣ እምነት አቧድኖና ለያይቶ ያልያዘው ኢሰፓ በኢትዮጵያ ቁልፍ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ሶሻላዊ ለውጦችን በማምጣት በኩል ሁነኛውን ሚና ተጫውቷል፡፡ ከአርባ ምንጭ ጨርቃ ጨርቅ እስከ ኮምቦልቻ ጨርቃ ጨርቅ፣ ሐረር ቢራ እስከ አሠላ ብቅል ፋብሪካ፣ ከሙገር ስሚንቶ እስከ እብነበረድ ማምረቻ፣ ከመከላከያ ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እስከ ናትፋ (ናዝሬት ትራክተር ፋብሪካ) ጨምሮ ሀሴብ፣ የጀልባ ማምረቻና እሸት የተባይ መርጪያ አውሮፕላን፣ ከግልገል ጊቤ እስከ ጭስ አባይ የኤሌትሪክ ኃይል ማመንጫ፣ ከሠፋፊ የመንግስት እርሻ እስከ የውትድርናና ትምህርት ማሰልጠኛ ተቋም፣ ባለ 50 ብር የወር ደሞዝተኛን የግል ቤት ባለቤት ከማድረግ ጀምሮ እስከ ተሳኩ የሠፈራ መንደሮች፣ ከጦር ሜዳ ቁስለኞች መንከባከቢያ እስከ ወላጅ አልባ ህፃናት ማሳደጊያ አምባ ከነፍስ ወከፍ መሣሪያ እስከ ታንክ መድፍና ሚሳይል ማምረቻ ከዘመናዊ የመስኖ ዝርጋታዎች እስከ ተለያዩ ግድቦች ከሶስቲክስ ሶዳ እስከ ተባይ ማጥፊያ ኬሚካል ጨምሮ በሂደት ላይ የነበር የማዳበሪያ ፋብሪካ እሳቤ ከሀገር አቀፍ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ እስከ ዩኒቨርስቲ ትምህርት በነፃ ወ.ዘ.ተ በመገንባት ለሀገሪቷ ሲቪልና መከላከያ ኢንዱስትሪዎች ግንባታ የበኩሉን አኩሪ የላቀ ሥራ መሥራቱን ማንም የሚክደው አይደለም፡፡ በየመስካቸውም አኩሪ ስራ ለሰሩ ዜጎች የተለያዩ ሜዳሊያዎች ሽልማቶችና ኒሻኖችን በመስጠት ለሥራቸው እውቅናና አገራዊ ክብር በመስጠትም ኢሰፓ ተሳክቶለታል፡፡ ለዚህም የተሻሻለ ምርጥ የቡና ዘርን በማግኘት ከኮነሬሉ እጅ የዲኤክስ መኪና ቁልፍ የተረከቡት ዶ/ር መስፍን አማህ ጨምሮ ሌሎች ዜጎችም ምሽክሮች ናቸው፡፡ እዚህ ላይ ግን አንድ ነገር ልብ ማለት ያስፈልጋል ደርግ ቀ.ኃ.ሥ ለዘመናዊቷ ኢትዮጵያ እድገት የበኩላቸውን ያደረጉ መሆናቸውን ማስታወስም ሆነ ማንሣት ባለመፈለጉ የእሱም ዕጣ ፈንታ እንደሳቸው የተዘጋ ቢሆን የሚገርም አይሆንም፡፡ ለምንቢሉ ሁሉም የእጁን ነውና የሚያገኘው፡፡

ሕዝባችን በዴሞክራት ሀገር እዳሉት የህዝብ ፓርቲዎች በተቃራኒ መልኩ ልቡንና መንፈሱን ሳይሰጥ ጭርሱንም ከእምነቱ ያቆራረጠውን ቅጥ የለሹን የፓርቲ አሠራርና አተረጓጐም እንደጠላና እንደተማረረ ኢህአዴግ ደርግን (ኢሠፓ) በጦር ኃይል አሸንፎ (ህዝብን ሳይሆን አመራሩን መሆኑን በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል) ስልጣኑን በጨበጠ በወር ከአንድ ቀኑ ታሪክ ራሱን ደገመ እንደሚባለው ሆነና እንደ አሸን የፈሉ የተለያየ መጠሪያ ያነገቡ ፓርቲዎች ኤርትራን ያላካተተች የወደፊቷ ኢትዮጵያን ዕጣ ፈንታ እንወስናለን ሲሉ ተሰባሰቡ፡፡ እስከ ዛሬ የነበረውን የአገሪቷ ታሪክና መሪዎቿም ለነፃነትና አንድነት ያደረጉትን ተጋድሎ ኮንነው ከተመሠረች መቶ አመቷ ነው ያሏትን የአቢሲኒያም ድር ያስተዳድራል ያሉትን ቻርተር አፀደቁ፡፡ በተለያየ ቂም፣ ስልጣን ፈላጊነት፣ ዘር፣ ቋንቋና ሀይማኖት የተቧደኑት ፓርቲዎችም አብዛኞቹ በውሸትና ፈጠራ ወሬ የተሞሉ በመሆናቸው ከራርመው እንወክልሀለን ለሚሉት ሕዝብ ጠንቅ የሆኑ ጉዳዮችን እንዳያዩ አይናቸውና ህሊናቸው የተጋረደ በመሆኑ የፐ/አሥራት ወ/የሰን እውቀትና እውነት መቀበል አቅቷቸው ከ70 ሺህ በላይ የወገን ደም ፈሶ እንዲቀር ምክንያት ሆኖአል፡፡ እውነት በሆነው የምድር የስበት ኃይል ውሸት አሸንፎ ስለማያውቅ ከራርሞ ከፓርቲዎቹ ሰዎች መሀል ግማሹ ሲታሰር፣ ግማሹ ሲከስም፣ ግማሹ ሲሰደድ ግማሹ በጥቅም ሲያዝ ግማሹ በጥቅም ሲያዝ ፓርቲዎቹ እንደ አጀማመራቸው አከሳሰማቸው ሳያምር ቀረ፡፡

የዚህ ጽሁፍ አቅራቢም በሐረር በተለያዩ አካባቢዎች አንድ ፓርቲ ፈፀመው ከተባለው አረመኔያዊ ድርጊት መሀል አንዱን በቴሌቪዥን መስኮት ቀርቦ መልክቱን ያስታውሳል፡፡ ተጎጂው ግለሰቡ ከእርሻና ኢንዱስትሪ ልማት ባንክ 6 ሚሊዮን ብር ተበድረው አዲስ ቤት ሠርተውና በተጨማሪም የለውዝ እርሻ ለማስፋፋት ተዘጋጅተው በነበረበት ወቅት የልጆቻቸው እናትን ጨምሮ ዘጠኝ ልጆቻቸው በታጣቂዎች መጨፍጨፋቸውን ገልፀው ይህም የመለስ ዜናዊ (ስም ጠርተው) አስተዳደር ያመጣው የያጐሣ ፖለቲካ መዘዝ የተናገሩትን ኢቴቪ በወቅቱ እንዳለ አስተላልፎታል፡፡ ነገሩ በጊዜው ደግሞ ለዴሞክራሲ መሆኑ ነበር፡፡ የሚያሳዝነው ግን የእኒህን ግለሰብ ታሪክ ከ20 አመት በኋላ ለአኬልዳማ ዝግጅቱ እንደ ግብአት የተጠቀመበት ኢቲቪ ቆራርጦ አቅርቦታል፡፡ (እኒህን ግለሰብ ፍትህ ጋዜጣ ዝግጅቱ ከተላለፈ በኋላ ያስታወሳቸው ቢሆንም ለተጨማሪ መረጃ እንዲሆን ከልማት ባንክ ገንዘብ ለቤት መሥሪያና ለእርሻ ማስፋፊያ መበደራቸውን፡፡ በተጨማሪም ጋራ ሙለታ አውራጃ ኩርፋ ጨሌ ወረዳ ነዋሪ የነበሩ አቶ ታዬ (ያባታቸው ስም ለዚህ ጽሁፍ ያልደረሰ) በሚያሽከረክሩት ፔጆ መኪና ውስጥ ከአመት ልጃቸውና እና ባለቤታቸው ጋር በጥይት ተገለዋል አክልበታለሁ፡፡)

ለኢህአዴግ መንግስትም ይህን መሠልና ሌሎች በርካታ ዴሞክራሲያዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ የህግ የበላይነት ጥያቄዎች በህዝቡ ዘንድ ከዕለት ወደ ዕለት እየተነሱ በመምጣታቸው የተለያዩ ፓርቲዎች እንዲመሠረቱ ምክንያት ሆነ፡፡ ፓርቲዎቹም በተናጥል እየተፍጨረጨሩ ባሉበት ሁኔታ ታሪካዊ የ1997 ዓ.ም ምርጫ እየተቃረበ መጣ፡፡

በዚህ ሀገራዊና ክልላዊ ምርጫ በሀገራችን ታሪክ ቀዳሚ የሆነውም የፓርቲዎች ውህደት ተፈጠረ፡፡ አገር ቤት ካለው ገበሬ ጀምሮ አሜሪካ እስካለው የጠፍር ሳይንቲስት ድረስ ገዥውን ፓርቲ በምርጫ ሳጥን በቃኸን ሊለው በህብረት ተሰለፈ፡፡ ኮረንቲና ፖለቲካ በሩቁ ነው ሲል የነበረው አደርባዩ ምሁርና ተራው ዜጋ በገሐድና በስውር በቅስቀሳ ተጠመደ፡፡ በአንድ ፓርቲ ጥላ ሥር የተሰባሰቡት ፓርቲዎች ወደ ምርጫ ገብተው ተፎካካሪዎቻቸውን በማይታመን የነጥብ ልዩነት ዘረሩ፡፡ በዚህም የተደናገጠው ገዥ ፓርቲ ክፉኛ ተደናገጠ፡፡ በቀጣይነትም በፓርቲዎች አይታመንም ይባል የነበረው ምርጫ ቦርድን ጨምሮ የተለያዩ እጆችና መንፈሶች በህዝቡ መነሳሳትና አንድነት ላይ በረዶ አስቀመጡበት፡፡ በምትኩም ሞት፣ እሥር፣ ስደት፣ አካለ ጐዶሎ መሆን፣ በሥነ ልቡና መታወክ፣ ከሥራ መባረር የመሳሰሉት እኩይ ሂደቶች ቦታውን ተቆጣጠሩት፡፡ ይኸ ሁሉ አስደሳችና አሳዛኝ ክስተቶች የተፈራረቁት ፓርቲዎች በአንድ ላይ ባመጡት ውጤት ሲሆን አደጋውም የሰላማዊ ትግል አንዱ አደጋ መሆኑንም እግረ መንገዱን ያሳየ ነበር፡፡ ሕዝብ አሁንም ከበፊቱ የባሰ በርካታ ጥያቄዎችን አንግቦ ፍትሀዊና ዴሞክራሲያዊ ምርጫ እየጠበቀ ነው፡፡ የህዝብ ደጀኖች ናቸው ተብለው የሚታመንባቸው ፖሊስና ፍ/

ወደ ገፅ 7 ይዞራል....

# ፕሬስ

ኢህአዴግ ወደ ስልጣን እንዲወጣ ከወሰዳቸው አበረታች እርምጃዎች ውስጥ የፕሬስና ሀሳብ የመግለፅ መብትን "መፍቀዱ" ነው፡፡ መንግስት ይህ መብት ህገ መንግስታዊ እንዲሆን ቢያደርግም በተግባር ግን አፋኝ እርምጃዎችን ከጅምሩ ነፃ ፕሬስ እንዳይዳብር እንቅፋት ሆኗል፡፡ የአንድ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መረገጫ የሆነው የፕሬስና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በኢትዮጵያ አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ መንግስት ላይ ትችት የሚያቀርቡ ጋዜጠኞች እና ሀሳባቸውን በይፋ የሚገልፁ ፖለቲከኞች መታሰር፤ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የአደባባይ ምሁራንን አርቋል፡፡ ሀሳባቸው የሚገልፁ ጋዜጠኞችና ተቺዎች ከእስር ጋር ተፋጠው ለመስራት ተገደዋል፡፡ ኢህአዴግ ያወጣቸው የፕሬስና የፀረ ሽብር አዋጆች ኢትዮጵያውያን ሀሳባቸውን በፕሬስ ውጤቶች እንዳይገልፁ የሚጠፍር ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን እንዳያገኙ አግዷል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲያብብ በሚረዱት የፕሬስ ውጤቶች አለማደግ ብሎም መመናመን የድህረ ግንቦት 20 ኪሳራ ሌላው ማሳያ ነው፡፡ በተለይም በቅርቡ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በኩል ቅድመ ምርመራን ለመጀመር እንቅስቃሴ መጀመሩ ከላይ ያየናቸው የድህረ ግንቦት 20 ኪሳራዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሀገሪቱ የመድብለ ፓርቲ ስርዓቱ እንዲከስም አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ በ2002 ምርጫ 99.6 በመቶ በሆነ ውጤት ፓርላማውን የተቆጣጠረው የአቶ መለስ መንግስት አውራ ፓርቲ መሆኑን በመግለጽ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ተንኮታኩቶ ጠቅላይ አምባገነን ስርዓት መደላደሉን አብስሯል፡፡ ግንቦት 20 አቶ መለስን በኢትዮጵያ አንግሷል፡፡ በሀገሪቱ ላይ ብቸኛው አድራጊና ፈጣሪ አቶ መለስ ናቸው፡፡ ሙገሳቸውም ሆነ ወቀሳቸው ድጋፋቸውም ሆነ ተቃውሟቸው እንደ እግዜር ቃል ይታያል፡፡ ለግንቦት ሃያ የተከፈለው መስዋዕትነት አቶ መለስን የሀገሪቱን ቁንጮ ከማድረግ ያለፈ ውጤት ያመጣ አይመስልም፡፡ የድህረ ግንቦት 20 ኪሳራዎች የኢትዮጵያ ህዝብ ከህወሓት ኢህአዴግ ነፃ የሚወጣው የድል ቀን እንዲጠብቅ ሳያስገድዱት አልቀረም፡፡



# በነዳጅ ፍለጋው ሥራ ዙሪያ አቶ መለስ የሰጡት ፍንጭ



ጥላሁን ባልቻ

ግንቦት 5 ቀን 2004 ዓ.ም ዘመድ ሰርግ ላይ ለመገኘት አዲስ አበባ በቅ ብዬ ነበር፡፡ ብቻዬን ስለነበርኩ ጊዜ ያሳልፍልኛል ብዬ ሪፖርተር ጋዜጣ ሲመጣ ገዛሁ፡፡ ርዕሰ አንቀጹን አስቀድሜ አነበብኩ፡፡ ከመጨረሻዎቹ አራት ፓራግራፎች በቀር ሐተታው ተስማምቶኛል፡፡ በመቀጠል ያነበብኩት በሽፋን ገጹ ላይ "የአፍሪካ መሪዎች በሙስና ለመዘፈቃቸው የውጪ ኢንቨስተሮች ተጠያቂዎች ናቸው" የሚለውን አቶ መለስ ዜናዊ ጥቅስ ሥር የቀረበውን ሐተታ ነው፡፡ ጽሑፉን ጨርሼ አነበብኩት፡፡ አዲስ ዜና ይዟል፡፡

ከጽሁፉ ትኩረቴን የሳበውንና የዚህ ማስታወሻ ሰበብ ስለሆነኝ ጉዳይ የበኩሌን ትንሽ ለማለት ፈልጌ ማታውኑ መምነጫጨር ጀመርኩ፡፡ ሪፖርተር ሲጽፍ . . ." ይህ በዚህ እንዳለ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ እስከ ዛሬ ድረስ ነዳጅ ለማውጣት ሲደረግ የነበረው የመጨረሻው የነዳጅ ፍለጋ ሥራ በያዝነው ዓመት መጨረሻ ወይም በሚቀጥለው ዓመት መጀመሪያ ውጤታማ ሊሆን እንደሚችል ጠቆሙ" ይላል፡፡ በመቀጠልም፣ "የሳውዝ ዌስት ኢነርጂ መሥራች ሊቀመንበርና ሥራ አስፈፃሚ አቶ ቴዎድሮስ አሸናፊ የውጤቱ የምሥራች አብሳሪ እንደሚሆኑ አያይዘው ገልጻዋል፡፡ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ይህን ያሉ ባሳለፍነው ሳምንት በአዲስ አበባ በተዘጋጀው የዓለም ኢኮኖሚ ፎረም ላይ ለመሳተፍ ከመጡና ከፎረሙ በፊት በተካሄደው በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ፎረም ላይ ለተሳተፉ ከ400 በላይ ለሚሆኑ የዓለም አቀፍ ኩባንያና የአገር ውስጥ ድርጅቶች ሥራ አስፈፃሚዎች በኢትዮጵያ ሰፊ የኢንቨስትመንት ዕድል እንዳለ ባብራሩበት ወቅት ነው" በማለት ሪፖርተር በቅጽ 17 ቁጥር 36/1256 ግንቦት 5 ቀን 2004 ዓ.ም የታተመው አስነብቧል፡፡ ሪፖርተርን ለዜናው አመሰግናለሁ፡፡

አቶ ቴዎድሮስ ይኼው ሳውዝ ዌስት ኢነርጂ የተባለው ኩባንያቸው መቼ ነዳጅ መፈለግ እንደ ጀመረ ባይገለጽም በጋምቤላ፣ በጅማ ዙሪያና በኦጋዴን በሦስት አካባቢዎች የነዳጅ ፍለጋ ሥራ በማካሄድ ላይ ይገኛል ሲሉ በሪፖርተር አማካኝነት አብሰረውናል፡፡ በሦስቱ አካባቢዎች ሦስት የፍለጋ ቡድኖች (crew) አሰማርተዋል ማለት ነው ወይስ ተራ በተራ? ግልጽ ቢደረግ ጥሩ ይሆን ነበር፡፡

ሌላው ግልጽ ያልሆነው ነገር አቶ መለስና እኚህ ግለሰብ ስለአንድ የተገኘ የነዳጅ ክምችት ነው ሊነግሩን የሚፈልጉት ወይስ በየፊናቸው ስለተለያዩ ግኝቶች? ለማናቸውም እንዳፋቸው ያድርግልን ከማለት በቀር የምለው አይኖርም፡፡

እስቲ ለጊዜው ይህን ጉዳይ በእንጥልጥል እንተወውና ስለ ነዳጅ ፍለጋ ሥራ ምንም ግንዛቤ ለሌላቸው ወገኖቼ ትንሽ ወደኋላ ዘለል ብዬ ፍንጭ ልስጥ፡፡

የተፈጥሮ ነዳጅን ፈልጎ ለማግኘትና ለማልማት ግዙፍ የፋይናንስ አቅምን ይጠይቃል፡፡ የነዳጅ ፍለጋ ሥራ ውጤታማ የመሆን እድሉ 10% ነው ስለሚባል ትርፍ ሥራ የፈታ ገንዘብ ያላቸው ትላልቅ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ናቸው ሥራው ላይ ደፍረው የሚሳተፉት፡፡ ከዚሁ ከአክሳሪነቱ ባህሪው የተነሳ የቱንም ያህል ሀብታም ቢሆኑ መንግሥታት ደፍረው ወደዚህ ሥራ አይገቡም፡፡

የነዳጅ ፍለጋ የሚካሄድባቸው አካባቢዎች በሦስት ይከፈላሉ፡፡

ሀ. ምንም ዓይነት የነዳጅ ፍለጋ ሥራ ተሞክሮባቸው የማያውቅ

ለ. የገፀ ምድርና የከርሰ ምድር ጥናት የተካሄደባቸው

ሐ. የቁፋሮ ሥራ የተካሄደባቸውና የነዳጅ ምልክት የታየባቸው የነዳጅ ኩባንያዎችን ትኩረት ለመሳብ የቦታው ዓይነት ወሳኝነት አለው፡፡ የነዳጅ ኩባንያዎቹም በሦስት ይከፈላሉ፡-

i. ግዙፍ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች

ii. መካከለኛ ዓለም አቀፍ ኩባንያዎች

iii. ትናንሽ በቤተሰብ ወይም በጓደኞሞች የሚቋቋሙ ኩባንያዎች ዓለም አቀፍ የነዳጅ ፍለጋ ሥራዎችን የሚሠሩት በተራ ቁጥር i እና ii የተመለከቱት ኩባንያዎች ሲሆኑ የካፒታላቸው መጠንና የሰው ኃይላቸው ይለያያል፡፡ ትናንሾቹ ኩባንያዎች በኮንትራት ለተወሰነ ጊዜ የሚያሠሩ ናቸው፡፡ መረጃ በማጠናቀር ለትልልቆቹ ኩባንያዎች በመሸጥ ገንዘብ ያገኛሉ፡፡ ደላሎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

## ነዳጅ የት ነው የሚፈለገው?

የተፈጥሮ ነዳጅ ጋዝም ይሁን ዘይት ወይም የሁለቱም ድብልቅ ሊፈጠር የሚችለው በአብላጫው ባህር ሸሽ አካባቢ የተለያዩ ዝቅጠተ አለቶች (sedimentary rocks) ተነባብረው በሚገኙበት ሁኔታ ነው፡፡ ለነዳጅ መገኘት ሦስት ነገሮች ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡

1ኛ ነዳጅ አመንጪ አለት (source rock)

2ኛ ማጠራቀሚያ አለት (reservoir rock)

3ኛ ገዳቢ ወይም ቆብ አለት (cap rock)

ነዳጅ አመንጪ አለት ውስጥ ያሉት ቅሬተ አካላት በጊዜ ብዛት በከፍተኛ ጭነትና በሚፈጠረው ሙቀት ወደ ነዳጅነት ይለወጣሉ፡፡ ነዳጁ ለመውጣት ወደ ላይ ይመጣል፡፡ መጠራቀሚያ ስፖንጅ መሰል ቀዳዳዎች ውስጥ ይጠራቀማል፡፡ ከመጠራቀሚያው አናት ላይ የነዳጅ ገዳቢ አለት (cap rock) ንጣፍ ከሌለ ነዳጁ ያመልጣል፡፡ ገዳቢ

ወደ ገፅ 13 ይዞራል....

# መድረክ ...

ከ ገፅ 7 የዞረ....

"መድረክ ፈጥኖ ወደ ግንባር አለመሸጋገሩ አንድነትን ብቻ ሳይሆን ሁሉም የመድረክ አባል ድርጅቶች አባላትና ሕዝቡም ጭምር ቅር ብሎታል ብዬ አስባለሁ፡፡ ይሁን እንጂ መድረክ ወደ ግንባር ማደጉ በራሱ የምንም ችግር መፍቻ ይሆናል ብዬ አላስብም፡፡ ወደድንም ጠላንም ዛሬ እዚህ ግባ የሚባል ሥራ እየሠራን አይደለንም፡፡ ይህንን ሀቅ ማመን አለብን፡፡ የሰብዓዊና የዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ እየተጣሱ ናቸው፡፡ በሕዝብ መካከል የጋራ መግባባት እንዲፈጠር ለማድረግ አልተቻለም፡፡ እነዚህንና ሌሎችም ብዙ የመታገያ አጀንዳዎች እያሉ ብዙ መሥራት አልቻልንም፡፡ ሀገር መስቀልኛ መንገድ ላይ ነው ያለችው፡፡ ሥልጣን ላይ ያለው መንግሥት ፍትሕንና መልካም አስተዳደርን ማስፈን ባለመቻሉ አብዛኛው ሕዝብ በድህነት እየማቀቀ ነው፡፡ ጥቂቶች ደግሞ የሚበለጽጉበት ሥርዓት እየተንሰራፋ ነው፡፡ ይህ በመሆኑም ኢህአዴግ በሕዝቡ ዘንድ ተቀባነትና አመኔታ እያጣ ነው፡፡ ዛሬ ጊዜው የሚጠይቀው ከግንባርም ታልፎ ወደ ውህደት መሸጋገርን ነው፡፡ ርግጥ ነው የመድረክ ግንባር ምስረታ አዝግሟል፡፡ ይሁን እንጂ ጥምረትም ይሁን ግንባር ዛሬም ቢሆን ትልቁ የመታገያ መሣሪያችን መድረክ ነው፡፡ መድረክ የወደ ፊቷ ኢትዮጵያ ጠንካራና የበለፀገች ሀገር እንድትሆን የማዕዘን ድንጋይ ነው፡፡ በመሆኑም መድረክ በቅርብ ጊዜ ግንባሩን እውን እንደሚያደርግ ሙሉ እምነቴ ነው" በማለት ዘርዘር አድርገው መልሰዋል፡፡

ወደ ዶ/ር መረራ ጉዲና ለተመሳሳይ ጥያቄ ደውዬ ስልካቸው ይጠራል ማንሳት ባለመቻላቸው ሀሳባቸውን ማካተት አልቻልኩም፡፡ እንዲሁም ለአቶ ገብሩ አሥራት ደውየላቸው ከተገናኘን በኋላ ጥያቄውን ሳናነሳባቸው በሥራ የተጠመዱ በመሆናቸው በዚያን ሰዓት እንደማይመልሱልኝ ስለገለጹልኝ እኔም በሥራ የተጠመድኩ በመሆኔ ዳግም አልደወልኩላቸውም፡፡

እንግዲህ የስድስቱን የመድረክ አባል ድርጅቶች ከፍተኛ አመራሮች አነጋግሬ እንደተረዳሁት ከሆነ የሁለቱ ድርጅቶች የገንዘብ ችግር ሲገጥማቸው በስተቀር ሌላ ችግር በመሀከላቸው እንደሌለ ሁሉም አረጋግጠዋል፡፡ ግንባሩም በቅርብ ጊዜ እንደሚመሠረት ተስፋቸውን ገልፀዋል፡፡ የመድረክ ጉዳይ በዚህ ሁኔታ ላይ እያለ መድረክ በመድረክ ላይ ለመመሥረት ሽርጉድ የሚሉ እንዳሉ ሰማን፡፡ ሰንደቅ ጋዜጣም የዚህን ምስጢር አስነብቦናል፡፡

## ለመሆኑ መድረክ በመድረክ ላይ መፍጠር ለምን አስፈለገ?

በዚህ 21 ዓመታት ውስጥ ብዙ የፖለቲካ አክሮባቶችን አይተናል፡፡ ፓርቲ አፍርሶ ፓርቲ መመሥረት፣ ካንዱ ፓርቲ ወጥቶ ወደ ሌላው መሄድ የተለመደ ነው፡፡ ካንዱ ፀንቶ መታገል የሚታሰብ አይደለም፡፡ ሌላው ምርጫ በመጣ ቁጥር ጥምረት፣ ሕብረትና ቅንጅት በጥድፊያ መመሥረትና ምርጫው ካለፈ በኋላ ደግሞ ተወንጃጅሎ ሕብረቱን ወይንም ቅንጅቱን አፍርሶ መበታተን ነው፡፡ አንድ የፖለቲካ ተንታኝ ኀልማሣ ስጋቱን እንዲህ በማለት ይገልፃል፡-

"ኢህአዴግን ለመገዳደር ታስቦ ከሆነ ጥሩ ነው፡፡ ግን አይመስለኝም፡፡ አራት ሠባራ ወንበሮችን ካንድ ድህነኛ ወንበር ጋር አደጋግፈው ቢያቆሟቸው ደህነኛውን ይዘውት በመውደቅ ይሠባበራሉ" በማለት ሥጋቱን ይገልፃል፡፡ ለመሆኑ የትኞቹ ፓርቲዎች ናቸው አዲሱን መድረክ የሚፈጥሩት?

6ቱ የመድረክ አባል ድርጅቶችና ሌሎች ሁለት ፓርቲዎች ናቸው፡፡ እነሱም መኢአድና አዲስ የተቋቋመው ሠማያዊ ፓርቲ የተባለው ነው፡፡ ከዚህ ላይ አንድ የሚያስደንቅ ነገር መጥቀስ የግድ ይላል፡፡ ይኸውም፡- መኢአድ ከአንድነት ጋር ለመዋሀድ ብዙ ጊዜ ጥረት አድርጓል፡፡ በተለይ በመጨረሻው ለድርድሩ መቋረጥ በምክንያትነት የሚጠቀሰው "አንድነት ከመድረክ መውጣት አለበት" የሚል ቅድመ ሁኔታ በማስቀመጡ ነበር፡፡ ስለ መኢአድ ሌላም ትዝብት መጨመር ይቻላል፡፡

ከምርጫ 2002 በፊት እንዲሁ መኢአድ ከአንድነት ጋር ለመዋሀድ መቀራረብ ይጀመራል፡፡ ይህ ወቅት ደግሞ አንድነት ከመድረክ ጋር ጥምረት ለመፍጠር በሂደት ላይ ነበር፡፡ በመሆኑም መኢአድ አንድነትን ከመድረክ ጋር የጀመረውን ግንኙነት እንዲያቋርጥ ጠየቀ፡፡ አንድነት አልሞከርም አለ፡፡ በዚህ እልህ የገቡት ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ግጥም አድርገው ፈርመው ከጠ/ሚንስትር መለስና ከልደቱ አያሌው ጋር በሚያስደንቅ ሁኔታ በሻምፓኝ ተራጩ፡፡

የዚህ አዲሱ ጥምረት አስተባባሪ ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ናቸው፡፡ ዶ/ር ያዕቆብ ኃይማርያም የሕግ ምሁር ናቸው፡፡ በአገር አቀፍ ብቻም ሳይሆን በዓለም አቀፍ ደረጃም እውቅናን ያተረፉ ምሁር ናቸው፡፡ ብቃቱም ሆነ ቀናነቱ አላቸው፡፡ የሳቸው ችግር የጀመሩትን ከዳር ማዝለቅ አይችሉም እያሉ በቅርብ የሚያውቋቸው ይተቿቸዋል፡፡ ለመድረክ መፈጠር ትልቁን ሚና ከተጫወቱት ምሁራን መካከል አንዱ እሳቸው ነበሩ፡፡ ዳሩ ግን ከፍፃሜ ሳያደርሱት ከአንድነት ሾልከው ወጡ፡፡ ከወጡ በኋላ ደግሞ አርፈው አልተቀመጡም፡፡ ራሳቸውን አስረጅተው "ወጣቱ ወጣቱ፣ ለወጣቱ ቦታ መልቀቅ" አለብን እያሉ ወተወቱ፡፡ በዚህም ብዙ ነቀፋ ደረሰባቸው፡፡ ቆይተውም ብርቱካን ስትፈታ በፊት የተናገሩትን በመርሳት ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ሊናገሩ የማይገባቸውን በመናገራቸው አሁንም ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠማቸው፡፡ ዛሬ ደግሞ 8 ፓርቲዎችን ለማጣመር ወይንም ሌላ አዲስ መድረክ ለማቋቋም እየባከኑ መሆናቸውን ስንሰማ ገርሞናል፡፡ ለመሆኑ ዶ/ር ያዕቆብ 8ቱን ፓርቲዎች ለማቀራረብ ሲነሱ እሳቸው የየትኛው ፓርቲ አባል ሆነው ነው? ይህ በግልጽ መታወቅ አለበት፡፡ በርግጥ የማንም ፓርቲ አባል ሳይሆኑ ወይንም ላንዱ ሣይወግኑ ባገር ፍቅር ስሜት ማደራደር ይችላሉ፡፡ በዚህም ቢመሰገኑ እንጂ አይነቀፉም፡፡ አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉ የአንድነት ፓርቲ አባል ሥጋታቸውን እንደሚከተለው ይገልፃሉ፡-

"የዶ/ሩ የአሁኑ አመጣጡ አልጣመኝም፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ እናት ፓርቲውን አንድነትን ለምን ጥሎ ወጣ?" በማለት ይጠይቁና "ምናልባት የመድረክን ወደ ግንባር መሸጋገር ለማደናቀፍ የተሴረ ሴራ እንዳይኖር?" በማለት ሥጋታቸውን በጥያቄ ይደመድማሉ፡፡ ሌላው አስተያየት ሰጭ፡-

"ጥምረቱ ይሁን ቢባል እንኳን መኢአድ በመጀመሪያ ደረጃ የራሱን ችግር ይፍታ፡፡ ሰማያዊ ፓርቲም በመጀመሪያ ከብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የእውቅና ሠርቲፊኬት ያግኝ" በማለት አስተያየታቸውን ይሠጣሉ፡፡

ሌላው አሥገራሚ ነገር ደግሞ ሠንደቅ ጋዜጣ እንዳስነበበን ከሆነ አዲስ ለሚፈጠረው ጥምረት ፕሬዚዳንት እንደሚሆኑ ለኢ/ር ኃይሉ ሻወል ቃል የተገባላቸው መሆኑን ነው፡፡ የዚህን እውነተኛነት ለማረጋገጥ ወደ ኢ/ር ኃይሉ ሻወል ደውዬ አግኝቻቸው ራሴን አስተዋውቄ ጥያቄውን ሳነሳላቸው ከመቅፅበት ራሳቸውን ቀይረው "አሁን እንቅልፍ ላይ ናቸው፡፡ ወደ ቢሮ ቢደውሉ ይሻላል" የሚል መልስ ሰጡኝ፡፡ ገረመኝ፡፡ ካልታመሙ በስተቀር የደውልኩበት ሰዓት ከቀኑ 4 ሰዓት ነው፡፡

እንደተባለው ለፅሐፊያቸው ደውዬ ስጠይቀው "ምንም የማውቀው ነገር የለም" የሚል መልስ ሰጠኝ፡፡ ይህንኑ ጥያቄ ይዤ ወደ ሰንደቅ ጋዜጣ ዝግጅት ክፍል ደውዬ፡- "ምንጩን ከየት አገኛችሁት? ይኽ ነገር እውነት ነው ወይ?" ብዬ ላቀረብኩላቸው ጥያቄ የሰጡኝ መልስ "እውነት ነው" የሚል ነው፡፡ በመጨረሻም ይህንን ምስጢር ያውቃሉ ወደ ተባሉ ሰው ደውለን ስለ እውነትነቱ ስንጠይቃቸው፡- "የጥምረቱ ሂደት በጥሩ ሁኔታ እየተካሄደ ነው፡፡ ነገር ግን ድምዳሜ ላይ ባለመደረሱ አሁን ውጤቱን መግለጽ አይቻልም፡፡ የሊቀመንበርነቱን ቦታ ለኢ/ር ኃይሉ ሻወል ለመስጠት ቃል ተገብቶላቸዋል የተባለው ግን የፈጠራ ወሬ ነው፡፡ ጋዜጠኞች ከየት እንዳገኙት አላውቅም፡፡ እየተሠራ ያለው መዋቅር ስብሳቢ፣ ፀሐፊ የሚል የለውም" ብለዋል፡፡

እንግዲህ አዲስ ሊፈጠር የታሰበው የ8 ፓርቲዎች ጥምረት ይህንን ይመስላል፡፡ ዝርዝር ውስጥ ለመግባት ግን አልፈለኩም፡፡ ግንዛቤን ለማስጨበጥ ከበቂ በላይ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ የመድረክ አባል ድርጅቶች ምሁራን ምን ይላሉ? ለማንኛውም አበው "እባብ ያየ በልጥ ደነገጠ" ይላሉና በጥምረት ስም መድረክ በመድረክ ላይ ለማፈናጠጥ ከመቸኮል ይታሰብበት እንላለን፡፡

# ወ/ሮ አዜብ መስፍን መሬት መውሰዳቸውን ያጋለጠው ሠራተኛ ታሰረ

በቅርቡ በቡራዩ ከተማ በከንቲባ ኩማ ደመቅሳ በተመራው ሙሰኞችን የማጋለጥ ስብሰባ ላይ "ወ/ሮ አዜብ መስፍን ያለ አግባብ በወንድማቸው ስም መሬት ወስደዋል" ብሎ ያጋለጠው የማዘጋጃ ቤቱ ሠራተኛ መታሰር በከተማው መነጋገሪያ መሆኑን በአካባቢው ያነጋገርናቸው የከተማው ነዋሪዎች ለሪፖርተራችን ገለፁ፡፡ ነዋሪዎች እንደሚሉት "መድረኩ የተዘጋጀው በቡራዩ አካባቢ የመሬት ቅርምት ተፈጽሟል፤ በመንግስትና በህዝብ መሬት ግለሰቦች አላግባብ በልጽገዋል፤ ከፍተኛ ሙስና ተፈጽሟል ተብሎ ነበር" ይላሉ፡፡

ሆኖም ግን ይላሉ ምንጮቻችን "የመድረክ አመራሩ ተሰብስበው በአካባቢው ኃላፊዎችና ከቁጥር በማይገቡ ሙሰኞች ላይ ብቻ ጣቱን እንዲቀስር እንዲያጋልጥ ግፊት ይደረግ ነበር፡፡ ይህንን የተገነዘበው አቶ ኃይሉ ንጉሴ የተባለው የማዘጋጃ ቤቱ የፋይናንስ ሠራተኛ ተነስቶ ትኩረቱን ለምን በትንንሾቹ ብቻ ታደርጋላችሁ፡፡ ሙስናን በቁርጠኝነት የምትታገሉ ከሆነ ወደ ላይም አትመለከቱም፡፡ በዚህ በከተማችን ወ/ሮ አዜብ መስፍን በወንድማቸው ስም መሬት ወስደዋል፡፡ ለምን አይጣራም? ለምን እሳቸውም አይጠየቁም" ብሎ ተናግሯል፡፡ በወቅቱ ስብሰባውን የሚመሩት ከንቲባ ኩማ ደመቅሳ "ጥቆማው አንድና አንድ ነው፡፡ ጥቆማው በማስረጃ መረጋገጥ አለበት፡፡ ዝም ብሎ መጠቆም አይደለም፡፡" እያሉ ጥቆማውን ለማጣጣልና ለማንቋሸሽም ሞክረዋል፡፡ ይህ ሲገርመን በቅርቡ ጠቋሚውን በሙስና ትፈለጋለህ ተብሎ ታስሯል፡፡ መንግስት በተለይ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ሙስናን ለመዋጋት ያለውን ቁርጠኝነትና ጥያቄ ውስጥ የሚከት ከመሆኑም በላይ በመንግስት ላይ ያለን እምነት እየተሸረሸረ ነው፡፡" ሲሉ ሥጋታቸውን ገልፀዋል፡፡

አቶ ኃይሉ ንጉሴ በገፈርሳ ቡራዩ ውስጥ ሊቀመንበር ሆኖ ያገለገለ ሲሆን በአሁኑ ወቅት በቡራዩ ማዘጋጃ ቤት የፋይናንስ ሠራተኛ ነበር ወ/ሮ አዜብ መስፍን በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ያለአግባብ ከፍተኛ ሀብት አፍርተዋል ተብሎ ከሚታሙት ግለሰቦች ውስጥ አንዷ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

# አቶ መለስ በደቡብ አፍሪካ ሊያደርጉት የነበረው ንግግር በተቃውሞ ተሰረዘ

አቶ መለስ ዜናዊ በደቡብ አፍሪካ ሊያደርጉት የነበረው ንግግር በኢትዮጵውያን ተቃውሞ መሰረዙን ከደቡብ አፍሪካ የደረሰን መረጃ አመለከተ

አቶ መለስ በደቡብ አፍሪካ ግንቦት 16 ቀን 2004ዓ.ም ታቦ ምቤኪ ሊደርሺፕ ኢንስቲትዩት በተዘጋጀ ጉባኤ ላይ ንግግር እንደሚያደርጉ ተቋሙ አስቀድሞ ያሳወቀ ቢሆንም፣ በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ የኢትዮጵያ ማህበረሰብ አባላት እና የሲቪክ ማህበረሰብ አባላት ግንቦት 15 ቀን 2004 ዓ.ም ባደረጉት የተቃውሞ ሰልፍ ምክንያት አቶ መለስ ሊያቀርቡት የነበረው ንግግር መሰረዙን በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ምንጮቻችን አስታውቀዋል፡፡

ምንጮቻችን እንደገለፁት ተቋሙ የአቶ መለስን ተክለ ስብዕና የሚያጐሉ መረጃዎችን እና የህይወት ታሪካቸውን ጭምር በማስታወቂያዎች ላይ በመለጠፍ ለፕሮግራሙ ዝግጅት አድርጐ ነበር፡፡ በማስታወቂያው እንደተገለፀው አቶ መለስ "በአዲሱ የአለም ስርዓት የአፍሪካ ፈተናዎችና እድሎች" በሚል ርዕስ ንግግር ካቀረቡ በኋላ ለእሳቸውና ለታቦ ምቤኪ ከተሳታፊዎች ጥያቄ እንደሚቀርብ አስቀድሞ ተገልፆ ነበር፡፡

ይሁን እንጂ በደቡብ አፍሪካ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንና የሲቪክ ማህበራት ለተቋሙ ባቀረቡት ተቃውሞ፣ የተቋሙ ስራ አስፈፃሚዎች አቶ መለስ ሊያቀርቡት የነበረውን ንግግር መሰረዛቸው ታውቋል፡፡ ምንጮቻችን እንደገለፁት መንግስትን በመተቸት የሚታወቀው አርቲስት ታማኝ በየነ በቅርቡ በደቡብ አፍሪካ ቆይታ ማድረጉንና ከኢትዮጵያ ማህበረሰብ ጋር ስኬታማ ውይይት አድርጐ እንደነበር አስታውሰው ከተቃውሞ ሰልፉ ጋር በተገናኘ አርቲስቱ አስተዋፅኦ ሳይኖረው እንዳልቀረ ጠቁመዋል፡፡ በተቋሙ ውስጥ የስራ አስፈፃሚነት ድርሻ ያላቸው ታዋቂው ምሁር ፕሮፌሰር ማሞ ሙጨም የአቶ መለስ ንግግር እንዲሰረዝ ትልቅ ጥረት ሳያደርጉ እንዳልቀሩ ከስፍራው የደረሱን መረጃዎች አመልክተዋል፡፡

ፍኖተ ነፃነት ስለጉዳዩ ለማጣራት የመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት ም/ኃላፊ አቶ ሽመልስ ከማልን ብትጠይቅም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ቃል አቀባይ የሆኑት አምባሳደር ዲና ሙፍቲም በጉዳዩ ላይ በቂ መረጃ እንደሌላቸው ለፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ተናግረዋል፡፡

አቶ መለስ ዜናዊ በተለያዩ አለም አቀፍ ስብሰባዎች ላይ የሚያደርጓቸውን ንግግሮችና ተሳትፎዎች በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን በተደጋጋሚ ይቃወሙ እንደነበርና፤ በቅርቡም በአሜሪካ ቡድን 8 ጉባኤ ላይ በርካታ ኢትዮጵያውያን ተቃውሟቸውን ማሰማታቸው እና ጋዜጠኛ አበበ ገላው ንግግራቸውን "አቶ መለስ አምባገነን ናቸው" በሚል ማቋረጡ ይታወሳል፡፡

# በነዳጅ ፍለጋው ሥራ ...

ከ ገፅ 12 የዞረ....

አለት ከላይ ካለ ግን ነዳጁ በማጠራቀሚያው አለት ውስጥ ተገድቦ ይቀመጣል፡፡ የዚህ መሰሉ የነዳጅ ኬሬ አብዛኛውን ጊዜ ከ2000 እስከ 3000 ሜትር ጥልቀት ላይ ይገኛል፡፡

በዚህ ጥልቀት የሚገኝን የነዳጅ ኩሬ ፈልጐ ለማግኘት፡-

- ሳይንሳዊ አስተሳሰብ (ዘይት የሚገኘው ሰዎች አእምሮ ውስጥ ነው የሚል አባባል አለ)
- የነዳጅ ፍለጋ ዘዴ ክህሎት
- ዘመናዊ ቴክኖሎጂን መጠቀም
- በቂ ገንዘብ
- ዕድል ተሟልተው መገኘት አለባቸው፡፡

የኢትዮጵያ የነዳጅ አለኝታ

ነዳጅ የሚፈጠረው ዝቅጠተ አለቶች ተነባብረው በሚገኙበት አካባቢ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በዝቅጠቱ አለቶች የተሸፈኑ ረባዳ ስፍራዎች (basins) የሚገኙት በስፋት በደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ኦጋዴን እና በምዕራብ ጋምቤላና መተማ፣ ዓባይ ሸለቆና መቀሌ አካባቢ ሲሆን በስምጥ ሸለቆም ይገኛል፡፡

በኦጋዴን ነዳጅ ሊፈለግበት የሚችል ስፍራ 250,000 ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት ሲኖረው ጋምቤላ 26,000 ካሬ ኪሎ ሜትር ይደርሳል፡፡ በኢ.ዘ.አ በ1937 ዓ.ም ሲንክሌር የተባለ አሜሪካዊ ኩባንያ በአገሪቷ በሙሉ ነዳጅ ለመፈለግ የሚያስችለው ጥያቄ አቅርቦ ስለ ተፈቀደለት ሥራ ጀመረ፡፡ ትንሽ ቆይቶ ሙሉ ትኩረቱን ወደ ኦጋዴን በማዞር ጥልቀታቸው 3000 ሜትር የሆኑ ሁለት ጉድጓዶች ቆፍሮ በሁለተኛው ጉድጓድ የዘይት ምልክት ሊያገኝ ችሏል፡፡ ሲንክሌር ለቆ ሲወጣ ኤልቨራት የተባለ የጀርመን ኩባንያ በ1950 ኦጋዴን የፍለጋ ሥራ ጀመረ፡፡

ይኼኛውም ኩባንያ ቴክኒካዊ መረጃዎችን ከሰበሰበና ከገመገመ በኋላ በ1955 ዓ.ም ጥልቀቱ 3395 ሜትር የሆነ ጉድጓድ ቆፍሮ ነዳጅ ሳያገኝ ቀረ፡፡ ኩባንያው ቀጣይ ሁለተኛ ጉድጓድ ቆፍሮ ነዳጅ ቢያጣም ከእሱ በፊት የሠሩት ኩባንያዎች በቆፈሩአቸው ጉድጓዶች ያልታወቀ የድንጋይ ንጣፍ በመብሳቱ መረጃነቱ ለጂኦሎጂ ዕውቀቱ ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደረገ ነበር፡፡ የጠበቀውን ውጤት ባለማግኘቱ በ1959 ዓ.ም ጠቅልሎ ከአገር ወጣ፡፡

ሐምሌ 1961 ዓ.ም ቴኔኮ የተባለ አሜሪካዊ የነዳጅ ኩባንያ የጀርመኑን ኩባንያ ይዞታ የነበረውን ያካተተ በጣም ሰፊ የፍለጋ ክልል በኦጋዴን ያዘ፡፡

ከእሱ የቀደሙት ሁለቱ ኩባንያዎች ሲንክሌርና ኤልቨራት የሰበሰቡትን የጂኦሎጂና ጂኦፊዚክስ (gravity, magnetic, seismic) መረጃዎችን በቢሮ ውስጥ ከገመገመ በኋላ የራሱን ተጨማሪ አዲስ መረጃ አክሎ በ1964 ዓ.ም ጥልቀቱ 3487 ሜትር የሆነ ጉድጓድ ቆፍሮ የዘይትና ጋዝ ምልክት ለማግኘት ችሏል፡፡ ሁለተኛውን ጉድጓድ 2200 ሜትር ድረስ ቆፍሮ አሁንም የዘይትና ጋዝ ምልክት አገኘ፡፡

ቴኔኮ ጥናቱን በመቀጠል በ1965 ዓ.ም ካሉብ 1 የተሰኘውን ጉድጓድ እስከ 4000 ሜትር ጥልቀት ቆፈረ፡፡ ይህ ጉድጓድ በሁለት (በተለያየ ጥልቀት) አሸዋማ የድንጋይ ንጣፎች ውስጥ ከፍተኛ የጋዝ ክምችት መሆኑ ነው፡፡ በዚህ የተበረታታው ቴኔኮ በዚሁ ጉድጓድ ትይዩ ላይ 4ተኛውን ጉድጓድ እስከ 3910 ሜትር ቆፈረ፡፡ በማከታተል 5ኛ ጉድጓድ እስከ 3445 ሜትር 6ና ጉድጓድ እስከ 4270 ሜትር ቢቆፍርም አጥጋቢ ውጤት አላገኘም፡፡

በ1966 ዓ.ም በኢትዮጵያ አብዮት በተቀጣጠለበት ዓመት 7ኛ ጉድጓድ ሂላላ-1 የተባለውን ቆፍሮ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥሩ የሚባል የዘይት ምልክት አገኘ፡፡ ቴኔኮ የያዘው የፍለጋ ክልል በጣም ሰፊ በመሆኑ አለፍ አለፍ እያለ ነበር የከፍተኛ ቁፋሮ የሚያካሄደው፡፡ በዚሁ መሠረት ከመሀል ኦጋዴን ወደ ምዕራቡ ጫፍ የባሌ ክፍታ ግርጌ 8ኛውን ገርቢ-1 ብሎ የሰየመውን ጉድጓድ ቆፍሮ ምንም ሳይገኝ ቀረ፡፡

ቴኔኮ የቁፋሮ ሥራውን ለጊዜው አቁሞ የሠራውን ሥራ መገምገም ጀመረ፡፡ በዚሁ መሠረት በ1967 ዓ.ም ካሉብ ላይ ያገኘውን ጋዝ አምርቶ ለገበያ ለማቅረብ የአዋጪነት ጥናት ማድረግ ጀመረ፡፡ ጥናቱ ያመለከተው በዘመኑ የነበረው የነዳጅ ጋዝ ዋጋ ዝቅተኛነት የተገኘው ክምችት አነስተኛነት፣ ከካሉብ እስከ አሰብ ወደብ የሚዘረጋው ቧንቧ ከፍተኛ ወጪን ግምት ውስጥ በማስገባት በዚያን ጊዜ ጋዙን ማልማት አዋጪ ያለመሆኑን ነበር፡፡

ቴኔኮ ሥራውን ለመቀጠል የሚያስችለው አጠቃላይ የሥራ ግምገማ ለማድረግ የአንድ ዓመት ፈቃድ እንዲሰጠው መንግሥትን ጠይቆ ፈቃድ ስለተከለከለ ኩባንያው የካሉብ ጋዝን ትቶ ጓዙን ጠቅልሎ በ1968 ዓ.ም ከአገር ወጣ፡፡

በኢትዮጵያ የነዳጅ ፍለጋ ታሪክ እንደ ቴኔኮ ግዙፍ ሥራ የሠራ ኩባንያ እስከ ዛሬ አልታየም፡፡ በተከታታይ 8 ጥልቅ ጉድጓዶችን የቆፈረው ቴኔኮ ብቻ ነው፡፡ ለመጀመሪያ ጊዜም ሳይሰሚክ (seismic) የከርስ ምድር መረጃ ስብሰባን አሁን በሚታወቀው የተሻሻለ መልኩ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀመው ቴኔኮ ነበር፡፡

ቴኔኮ በኢትዮጵያ የነዳጅ ፍለጋ ጥረት ከፍተኛ ተስፋ የፈነጠቀ የጊዜ ጉዳይ እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ነዳጅ ዘይትና ተጨማሪ ጋዝ መገኘቱ አይቀሬ እንደሆነ ያሳየ ባለውለታ ድርጅት ነው፡፡ ነዳጅ ፈላጊ ኩባንያዎች በፍለጋ ሥራቸው ወቅት የሰበሰቡትን የጂኦሎጂ የጂኦፊዚክስ የጂኦኬሚስትሪ እና ናሙናዎችን ለመንግሥት በመተላለፋቸው ሌሎች መሰል ኩባንያዎችን መሳቢያ (ማማለያ) ጠቃሚ የፕሮሞሽን ግብአቶች ናቸው፡፡

የካሉብ ርጥብ ጋዜ የቤንዚን፣ ቡታጋዝ፣ ነጭ ጋዝና ናፍጣ ድብልቅ ሲሆን የመጠኑ ግምትም 68 ቢሊዮን ኩብ ሜትር ይገመታል፡፡ ከጋዙ ኤሌክትሪክ ሊመነጭ ይችላል፡፡ የካሉብ ጋዝ ለ40 ዓመታት ተቀብሮ ያለ ጥቅም ተቀምጧል፡፡ የልማት ሥራው ከ20 ዓመት በፊት ቢጀመርም ዛሬም ዳር አልደረሰም፡፡

የአቶ መለስና የአቶ ቴዎድሮስ "ድንገቴ ብሥራት" በየትኛው የአገሪቷ አካባቢ እንደተከሰተ እንኳን ፍንጭ አልሰጠም፡፡ በቂ ሥራ ከተሰራ ኢትዮጵያ ውስጥ የነዳጅ መገኘቱ ዕድል በጣም ከፍተኛ ነው፡፡

ምሥራቅ ኦጋዴንን ብንመለከት ከሳዑዲ አረቢያና ከየመን የነዳጅ መስኮች ጋር ተመሳሳይ ጂኦሎጂካዊ ገጽታዎች ይታያሉ፡፡ ከጋምቤላ ሰሜን ምዕራብ ሱዳን ውስጥ በቅርብ ርቀት ነዳጅ እየተመረተ ነው፡፡

በዩጋንዳ ባለፈው ዓመት ነዳጅ ተገኝቷል፡፡ በሰሜን ኬኒያ በቅርቡ የተገኘው ነዳጅ ደቡብ ሱዳን ከተገኘው ክምችት ጋር በተያያዘ መስመር ላይ የሚገኝ በመሆኑ በመሀላቸው ያለው ጋምቤላም ተመሳሳይ የጂኦሎጂ ሁኔታ ስላለው በጋምቤላ የነዳጅ መገኘት የጊዜ ጉዳ ብቻ ነው፡፡

25,000 ካሬ ኪሎ ሜትር የቆዳ ስፋት ያለው የኦጋዴን ሴዲሜንተሪ ረባዳ ውስጥ እስካሁን የተቆፈሩ የፍተሻ በ20 በታች ነው፡፡ ምንም ሥራ አልተሰራም ማለት ይቻላል፡፡ በ20 ጉድጓዶች ነዳጅ ለማግኘት መሞከር በትልቅ ባሕር ውሰጥ የወደቀች መርፌ እንደመፈለግ ይቆጠራል፡፡ መርፌዋን ፈልጐ ለማግኘት የተቀራረበ ፍለጋ በበቂ ዘመናዊ የመፈለጊያ መሣሪያ የተደገፈ ግብረ ኃይል ማስማራት ይጠይቃል፡፡ ይህ ጥረት ደግሞ ብዙ ገንዘብ ማስወጣቱ ጥያቄ አበረታች ናቸው፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የነዳጅ ይገኛልን ፍንጭ ከደሀና ጐስቋላ ሕዝባቸው ሰውረው ለጥቂት በኢኮኖሚ ፎረሙ ላይ ለመገኘት ለመጡ የውጪ አገር ታዳሚዎች ቅድሚያ መረጃውን ማብሰራቸው እኛ ኢትዮጵያውያን ቅድሚያ ባለማግኘታችን ቅሬታም ብዥታም ፈጥሮብኛል፡፡

አቶ መለስ ቢያውቁትም ፎረሙ ላይ የተገኙት በእኛ ስም ነው፡፡ በኢትዮጵያ ስም ነው፡፡ "ኩንትራቱን" የሰጣቸው ሕዝብ ኮንትራቱን ሊስብ ይችላልና ሕዝብን ማክበር ብስለት ነው፡፡

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር

# የጠ/ሚኒስትር መለስ ጀሮና የአበበ ገላው ድምፅ

ከይመር እንግዳ

የአሜሪካው ፕሬዘዳንት ባራክ አባማ በአማሪካን ካምፕ ዴቪድ ሬገን ማዕከል ባዘጋጁት በምግብ ዋስትና ላይ የሚመከረው የቡድን ስምንት አለም አቀፍ ስብሰባ ላይ ለመካፈል ተገኝተው የነበሩት ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ድንገተኛ ተቃውሞ እንደገጠማቸው ፍኖተ ነፃነት ዘግባ ነበር፡፡ ከዚያው ክስተት ጋር በተያያዘ ይህችን አጭር መጣጥፍ ለማቅረብ ወሰንኩ፡፡

ግንቦት 10/2004 ዓ.ም ጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በ21 ዓመት የስልጣን ዘመናቸው ሊሰሙ የማይፈልጉትን ድምፅ ለመስማት ተገደዋል፡፡ አበበ ገላው የተናገራቸው የብሶት ድምፆች ለ21 ዓመታት በኢትዮጵያ ተፀንሰው በ80 ሚሊዮን ህዝብ ልቦና ውስጥ የነበሩና ጆሮ አጥተው የሰሚ ያለህ የሚሉ ኡኡታዎች በካምፕ ዴቪድ ሬገን ማዕከል በዓለም አቀፍ ጋዜጠኞች ማህበር አባል በሆነው ጋዜጠኛ አበበ ገላው አማካኝነት ለጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ጆሮዎች በሚገባ ደርሰዋል፡፡ አይ አሜሪካ "እንጀራ ይውጣልሽ!" የ200 ዓመት የታሪክ ባለቤት ለታላቅ እህትሽ የ5000 ዓመት የታሪክ ባለቤት በገዛ አገሯ አልሰማም ብትል የትንሽ ትልቅ ሆነሽ ጆሮዎቿ እንዲሰሙ አደረግሽ፡፡ ጎሽ! በመጀመሪያ ልጅሽ በጆርጅ ዋሽንግተን ስም ምስጋና ይድረስሽ፤ እውነተኛ ዴሞክራሲሽን መሠረት ጥሎልሽ አልፏልና፡፡

"ለእኔ ትልቅ ቀን ነው" ብሏል አቤ፡፡ እውነት ነው አቤ፤ ላንተ ትልቅ ቀን ነው፡፡ በጠመንጃ አፈሙዝ ታፍኖ ላለ ህዝብም ልዩ ቀን ነው፡፡ ከታሪክ ተወቃሽነት እራስህን ነፃ አውጥተሃልና ነፃነት! ነፃነት! ነፃነት! ስትል፡፡

ክቡር ጠ/ሚኒስትር ወደ አገሮት ሲመለሱ ለአንድ ጋዜጠኛ የሰጡትን ጆሮ ለ80 ሚሊየን የኢትዮጵያ ህዝብ እንደማይነፍጉት ባለሙሉ ተስፋ ነኝ፡፡ ትምህርት አግኝተዋልና፡፡ ምክንያቱም የግለሰቡ ጩኸቶች ከእሱ በፊት እዚሁ ሲጮኹ (ጠብቆ ይነበብ) ጆሮ ተሰጧቸው ቢሆን ኖሮ በሰው አገር ሊያስተላልፉ የነበረውን መልዕክት አቁመው ጆሮዎትን ለመስጠት ባልተገደዱ ነበር፡፡ አሁንም እላለሁ በአገሪቱ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ የምግብ እጥረት፣ የመልካም አስተዳደር እጦት፣ ድህነት፣ በነፃነት ሠርቶ ሃብት ማፍራት አለመቻል፤ የዜጎች ከመኖሪያ ቀያቸው መፈናቀል፣ የሃይማኖት ውጥን ቅጦች፣ የሙስና አዘቅት እንዲሁም ገደብ የለሽ የዜጎች ስደት እነኚህ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ መንግስት ከዜጎች ይልቅ ለውጭ ባለሀብቶች ክብርና የእርሻ መሬቶች በገፍ የመስጠት አባዜ፣ ሥራ አጥነትና የመሳሰሉት ህልቆ መሣፍርት የህዝብ ሰቆቃዎች በአገሪቱ ከጫፍ እስከ ጫፍ ተንሰራፍተዋል፡፡ እስኪ ካዛንችስ ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ አካባቢ ከተለያዩ የአገራችን ክፍሎች እየመጡ ወደ ተለያዩ የአረብ አገራት ለስደት የተኮለኮሉ እንቡጥ እህቶቻችንን ረጃጅም ሰልፎች ይመልከቷቸው፡፡ እነዚህ እንግዲህ በየቀኑ የምናያቸው የዘወትር ክስተቶች ናቸው፡፡ ፍርድ ተጓደለ፣ ስደት ተበራከተ፣ ዳቦ ስም ብቻ ሆኗል፡፡ ለእኛም ቀና ብለው ጆሮዎትን ይስጡን፡፡ በእርግጥ እርስዎ ስልጣን ከያዙ አሜሪካ አራት ፕሬዘዳንቶች አይታለች (ጆርጅ ኤች ደብሊው ቡሽ፣ ቢል ክሊንተን፣ ጆርጅ ደብሊው ቡሽ እና ባራክ አባማ ናቸው) ኢትዮጵያ ግን መለስ ዜናዊን መለስ ዜናዊ ብቻ ናቸው፡፡

ዙፋኖትንም ቆም ብለው ይቃኙ! ምናልባትም ነቀዝ በልቶት ሊሆን ይችላልና በአዲስ ይቀይሩት ወንበሩን፡፡ በመጨረሻም በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የእርሶን ጆሮዎች የሚፈልጉ የብሶት ድምፆች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ አጋጣሚውን አጥተው ሊሆን ይችላልና፡፡ ስለዚህ የህዝቦችን የሰቆቃ ድምጾች ለመስማት በካምፕ ዴቪድ ሬገን ማዕከል እንዳደረጉት በድንጋጤ ሳይሆን ረጋ ብለው በሰከነና በማስተዋል መንፈስ ጆሮዎትን ቀና ያድርጉ እነሆም የነፃነት ናፋቂ ድምፆች በደጅዎ ቀርባለችና አቤት ይበሏት፡፡ ፈውስንም ያገኛሉና፡፡

ለማንኛውም መልስዎን በተግባር እጠብቃለሁ እስከዚያው ቸር እንሰንብት፡፡

# ሰማዕታቱ ቀና ...

ከ ገፅ 3 የዞረ.....

ሠላም ማተሚያ ድርጅት ጓሮ ተደብቆ የመጣው ሳንሱር በጋዜጦች ላይ አደገኛ ጥላ አጥልቷል፡፡ ብርሃንና ሠላም ማተሚያ ድርጅት ያዘጋጀው ሳንሱርን ያዘለና አሳታሚዎች እንዲፈርሙት የቀረበ ውል ሥራ ላይ ከዋለ በአሁኑ ጊዜ ጭል ጭል የሚሉት የነፃው ፕሬስ ጋዜጦች ጭራሹን ይጠፋሉ፡፡ የዜጎች በነፃነተ ሃሳብን የመግለጽና የሕዝቡም መረጃ የማግኘት መብት ያበቃላቸዋል፡፡ ሰማዕታቱ ዳግም ቢነሱ በየመንገዱ ጋዜጦች ሲነበቡ አያዩም፡፡

በኢትዮጵያ ውስጥ የ68 ፓርቲዎች መርመስመስ ለአጭር ጊዜ ቀና ያሉ ሰማዕተትን ያስደስት ይሆናል፡፡ ነገር ግን የእነዚህ ፓርቲዎች መኖር ዴሞክራሲ እንዳላመጣ እናውቃለን፡፡ የብዙ ፓርቲዎች መኖር የዴሞክራሲ መግለጫ ሊመስል ይችላል፡፡ ብልህነትን ግን አያሳይም፡፡ የዳበረ ዴሞክራሲ ያላቸው ብልህ አገሮች የፓርቲዎቻቸውን ቁጥር በተቻለ መጠን እስከ ሁለት ወይም ሶስት፣ ቢበዛ አስከ አምስት ድረስ እንዲወርድ ይጥራሉ፡፡ ሀገራችን በአሁኑ ወቅት የመድበለ ፓርቲ ሥርዓት አላት ትባል እንጂ በተግባር ግን ወደ አንድ ፓርቲ ሥርዓት ውስጥ ገብተን ከዚያም ባለፈ ወደ አንድ ሰው ተከለሰውነት አምልኮ ወርደን እንገኛለን፡፡

ታዲያ እውነታው ይህ ከሆነ አቶ ሴኮቱሬ ሰማዕታት ቀና ብለው አይዋት የሚሏት ኢትዮጵያ የትኛዋ ናት? ሰማዕታት ያይዋት ኢትዮጵያ በመሬት ላይ ያለችውን ኢትዮጵያ ሳይሆን በኢትዮጵያ ተሌቪዥን ውስጥ ያለችውን ‹‹ኢትዮጵያ›› ነው፡፡ እሷን ኢትዮጵያ እኛም ብንሆን እስከሚሰለቸን አይተናታል፡፡ አቶ ሴኮቱሬም በቃለ መጠይቃቸው የተረኩት ያንኑ የሰለቸንን ተረክ ነው፡፡

የህወሓት ሰማዕታት ሁለት ጊዜ ተሸውደዋል፡፡ መጀመሪያ በህይወት ሳሉ የያኔ መሪዎቻቸው፣ የዛሬ ቅምጥል መኳንት የሚታገሉት ለነፃነት፣ ለዴሞክራሲና ለመሳሰሉ የተቀደሱ ዓላማዎች ነው ብለዋቸው እውነት መስሏቸው ህይወታቸውን ሰውተዋል፡፡ ዛሬ ደግሞ ለአፍታ ቀና ቢሉ እውነተኛዋን ኢትዮጵያ ሳይሆን የቴሌቪዥንዋን ኢትዮጵያ አሳይዋቸው፡፡

የህወሓት ሰማዕታት ሊከበሩ ይገባል፡፡ በወቅቱ እንታገልለታለን ብለው ለአመኑበት፣ ለተቀደሰ ዓላማ ማለትም ነፃነትን፣ እኩልነትን ዴሞክራሲን ወ.ዘ.ተ ለማምጣት መስዋእት ሆነዋል፡፡ የያኔ መሪዎች የዛሬ የምጥል መኳንንት ግን ጓዶቻቸው የሞቱለትን ዓላማ ክደው የጓዶቻቸውን መስዋእትነት ‹‹ሕድሪ ስውኣት!›› (የሰማእታት አደራ) እያሉ መነገጃ አድርገውታል፡፡ እኛም የሰማዕታቱን የመጀሪያ የተቀደሰ ዓላማ ይዘን የቀድሞ ተጋዮችን የዛሬ ቅምጥል መኳንትንና አምባገነን መሪዎችን ለኢትዮጵያ ሕዝብ ፍላጎት ተገዥ እንዲሆኑ እንታገላቸዋለን፡፡

# መቼ ይሆን ...

ከ ገፅ 9 የዞረ.....

እንደ ፋሽን ችግሩ በስፋት ይስተዋላል፡፡ እዚህ ጋ እነኚህ እንስቶችን ለጥቃት የሚፈልጉ ሰዎች እህቶቻቸው ቢሆኑስ ያደርጉት ይሆን? ፍርዱን ለእያንዳንዳችን ልተወው፡፡

እውነት ግን ብዙ የእርዳታ ፈንድ የሚያገኘው የሴቶች፣ የህፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር እና የየወረዳና ክፍለ ከተማ መስተዳደሮች ስራቸው ምን እንደሆነ በይፋ ቢያሳውቁ መልካም ነው፡፡

በትዝብቴ ወቅት እነኚህን ወጣቶች "መንግስት ተደራጅታችሁ ብድር ውሰዱና ስሩ" እያለ እኮ ነው አልኳቸው፡፡ እንደሚባለውና እንደሚወራው ቢሆንማ ማንም ህይወቱንና ክብሩን ሸጠ አያድርም አሉኝ፡፡ በየወረዳው መስተዳደር የሰሞኑ መፈክር የሆነውን አንስቼ መንግስት "በአልባሌ ቦታ የሚባክን የወጣት ጉልበት አይኖርም" እያለ እኮ ነው አልኳቸው በተለይ ወይንእሸት "እኛ መንግስትና ሀገር አለን እንዴ?" ስትል ጠየቀችኝ፡፡ አስከትላም የሌላ ሀገር መንግስት እኮ ለዜጐቹ ያስባል፣ ይጨነቃል፡፡ እስኪ ስለሳሪስ ነዋሪ ብቻ ብታስብ የት እንዳለህ ግራ ይገባሃል አለችኝ፡፡

አስከትላም በአሁኑ ሰዓት ወጣቶች እንዲማሩ፣ የነገ ተስፋ እንዲሆኑና የእውነት ራሳቸውን እንዲለወጡ አይፈለግም፡፡ ለዚህ ማረጋገጫ ከፈለግህ ሳሪስ የደባል ሱስ መናሃሪያ ስትሆን የነዋሪ ራስን ችሎ የመኖር አቅም ግን ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ ሁሉም የምግብ እህሎች ቀረጥ ይከፈልባቸዋል፣ ምግብ ቤት ስትሄድ ደግሞ ጥረህ ግረህ ለምትበላው እንኳ ተጨማሪ ቀረጥ ትከፍላለህ፤ በኬላ ላይ ቁጥጥር የሚደረግባቸው የምግብ እህሎች ናቸው ጫት ግን አይቀረጥም ኬላዎችም ክፍት እንዲሆኑ መደረጉን ሰምተናል አለኝ፡፡ ከዚያም "እስኪ አስብ እኛ ምግብ እንድንበላና ጤናማ ኑሮ እንድንኖር ሳይሆን በጫትና በሺሻ እንድንደነዝዝ የሚያበረታታ ለእኛ መንግስት ነውን?" ስትለኝ በተመስጦ አቀርቅሬ ዝምታን መረጥኩ፡፡ ካጫወቱኝ እንስቶች ብዙ አሳዛኝ ታሪኮችን በቁጭት ከተጋትኩ በኋላ ወደ መጣሁበት ተመለስኩ፡፡ ታዲያ ምንስ አማራጭ አለኝ፡፡ ታዲያ አካባቢው በዚህ አካኋን አንዳንድ ተማሪዎች ከነ ደንብ ልብሳቸው (ዩኒፎርማቸው) በትምህርት ሰዓት በአቅራቢያቸው ስርቻ ባሉ መቃሚያ ቤቶችና ሺሻ ቤቶች ቢያገኛቸው ምን ይሰማዎታል? ወላጆችስ ልጆቻቸው ከእንቅልፋቸው ተነስተው ወደ ት/ቤት ሲሄዱ ያውም በጠዋት ሲጋራ ሲያጨሱ ቢያዩ ምን ይሉ ይሆን? በተግባር ብዙ ልጆችን ያያሉ፡፡ ይሄ ሁሉ በአካባቢው ያለው የደባል ሱስ እንቅስቃሴ ንግድ መበራከትና ሃይ ባይ ከመታጣቱ የመጣ ይመስለኛል፡፡ በዚህ ሁኔታ መቼ ይሆን ለትውልድ የሚታሰበው?

እስኪ ሌሎች ወጣቶች በስፋት የሚገኙባቸው ተቋማት አካባቢ ይቃኙና ምልከታዎን ያስተውሉ፡፡ ማን ይሆን ለወጣቱ የሚያስብ ብለን ካሰብን ኸረ የሰው ያለህ! ያስብላል፡፡ ወጣቱ የነገ ተስፋው እየጨለመበት ነውና ገዥው ፓርቲም ይሁን ተቃዋሚ እንዲሁም መጠቀሚያ ይሆናል፡፡ ማሙሽ ሌላ ፎቶው ሌላ ሆኖ በወሬ የወጣቱ ተጠቃሚነት ብዙ ይነገረናል በተግባር ግን የለምና ይታሰብበት፡፡

# መስከረም 2 ...

ከ ገፅ 6 የዞረ.....

ግብራቸው ልዩነት የለውም፤ ስልቻ ቀልቀሎ ቀልቀሎም ስልቻ ነው፡፡ ግንቦት 20ም ያው መስከረም 2 ሆነ፡፡

ትናንት ክቡር ህይወታቸውን ለእውነተኛ ዴሞክራሲ የገበሩ ሰማዕታት የተሰውለት ዓላማ ፈሩን ስቶ የኢትዮጵያ ህዝብ ደግሞ በአምባገነኖች እጅ መውደቁን ቢያዩ ምንኛ ያነቡ ይሆን? በህወሓት (ኢህአዴግ አመራር ውስጥ በነበረው የበረሃ ህይወት የሰፈነው ዴሞክራሲና የጋራ አመለካከት ፍጹም ተሸርሽሮ የአንድ ግለሰብ ትክለ ሰውነት ጎልቶ የወጣበት ሆኗል፡፡ አቶ መለስም እንደ ኮሎኔል መንግስቱ ኃ/ማርያም ግንቦት 20 ሲደርስ ፎቶ ግራፋቸውን በየአደባባዩ ማሰቀል ከጀመሩ ሰነባብተዋል፡፡ ዴሞክራሲን በጫማቸው ሶል እየረገጡ የግንቦት 20ን ድል ለማጉላት መሞከር ከንቱ ውዳሴ ነው፡፡ ኮሎኔል መንግስቱም ያደረጉት ይሄንኑ ነበር፡፡ ግንቦት 20 በመጣ ቁጥር በፈርደበት ኢቴቪ የትጥቅ ትግሉን አስከፊ ገፅታ የሚያጎሉ ፊልሞችን ከፋይል እያወጡ ለተራ ፕሮፓጋንዳ መጠቀም ጊዜው ያለፈበት አራዳነት ነው፡፡ እነዚያ ውድ የኢትዮጵያ ልጆች ህይወታቸውን ለበረሀ የገበሩት ለህዝብ ነፃነት እንጂ ለጥቂት ሹመኞች እድሜ ማራዘሚያና ለቤተ መንግስት የቅምጥል ኑሮ አይደለም፡፡ ዛሬ አቶ መለስም ሆኑ ደቀመዝሙርቶቻቸው እንደልባቸው ለሚፈነጩበት የሥልጣን መንበር የበቁት በእነዚህ ታጋዮች ደም ተዋጅተው ነው፡፡ እንደ ታላቅ የዴሞክራሲ ድል የሚቆጠረው የዘመነ ኢህአዴግ ህገ መንግሥት ካለፉት መንግስታት ህገ መንግስቶች በቅርፅም ሆነ በይዘት በእጅጉ የተሻለ መሆኑ ይታወቃል፡፡ በወረቀት ላይ ሠፈረ እንጂ የማይተገበር ነው፡፡ ህገ መንግስታዊ መብቶች በየአቅጣጫው ይጣሳሉ፡፡ ዛሬ ሠላማዊ ሠልፍ መውጣት፣ የሥራ ማቆም አድማ የማድረግ፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለጽ ኢህአዴግን በሰላማዊ መንገድ ከሚቀናቀኑ የፖለቲካ ድርጅቶች ጐን መሰለፍ ወንጀል ሆኗል፣ በሽብርተኝነት ያስፈርጃል፤ ከሥራ ገበታ ያፈናቅላል፤ አልፎም ወደ ቃሊቲ ያስወረውራል፡፡ ኢትዮጵያውያን ህገ መንግስታዊ መብታቸውን ተጠቅመው በሀገሪቱ ክልል ተዘዋውረው የመኖር ህልውናቸው ለአደጋ ተጋልጧል፡፡ ገበሬው ከእርሻ መሬቱ እየተፈናቀለ ከከፉ ድህነትና ችግር ጋር እየተጋፈጠ ይገኛል፡፡ ሙስና የሥርዓቱ ልዩ መገለጫ ሆኗል፡፡ ወጣቱ ሥራ አጥ በመሆኑ ለባዕድ አገር የስደት ኑሮ ተዳርጓል፡፡ ከሞት ጋር እየታገለ በረሀ አቋርጦ ከአገር ይወጣል፡፡ የኑሮ ውድነቱ የዜጎችን ቅስም ሰብሯል፡፡ እንግዲህ በነዚህ አስከፊ ችግር ውስጥ ለተቆራመደው የኢትዮጵያ ህዝብ ግንቦት 20 ምኑ ነው? እውነት የነፃነት ቀን ክብረ በዓሉ ነውን? መስከረም ሁለትም ግንቦት ሃያም የአንድ ሣንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው፡፡

# መለስ ኢትዮጵያን ...

ከ ገፅ 3 የዞረ.....

ምርታቸውን ለማጓጓዝ የመንግስት ንብረት ከሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ ውጭ እንዳይጠቀሙ በድንገት ተነገራቸው፡፡ ይህ ከሚያመርቱበት ማሳ እስከ አዲስ አበባ እና ከዚያ ወደ እውሮፓ መጫንን ይጨምራል፡፡ ኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ትላልቅ የአበባ እርሻዎች የአንዱ ባለቤት የሆነ ሰው በጭንቀት ተውጦ "ኢትዮጵያ እስካሁን እንዲህ አይነት ኩባኒያ የላትም" ቢለኝም ይህንን ተግባራዊ ያላደረገ ተቋም እንደሚቀማ ታውቋል፡፡ መንግስት የውጭ ኢንቨስትመንትን ወደ ሀገር ውስጥ ከሰበ በኋላ አሁን ግን እየተጫናቸው ትርፋቸውንም መቀማት ይፈልጋል፡፡

### መለስ የኢኮኖሚ እድገት የማይፈታው ችግር

ከየአቅጣጫው እያዋጣቸው ነው፡፡ የዋጋ ንረቱ በ50% እየጋለበ ነው፡፡ ያናገርኳቸው ኢትዮጵያዉያን የኑሮ ውድነቱ በህይወት ዘመናቸው ብዙ የማያውቁት መሆኑን ነግረውኛል፡፡ ዋነኛ የኢትዮጵያውያን ምግብ የሆነው ጤፍ ዋጋ በ4 እጥፍ በመጨመሩ ድሆች ሕይወትን የማይኖሩባት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ ዩኒቨርስቲዎች ስራ በሌለበት ተመራቂዎችን ያመርታሉ፡፡ በቅርቡ ያነጋገርኳት አንዲት ተመራቂ መቶ አካባቢ ሆነው ከተማሩ ጓደኞቿ አስሮቹ ብቻ ስራ ላይ እንዳሉ ነግራኛለች፡፡ የመንግስት ተስፋ ግን ኢኮኖሚው በፍጥነት ያድጋል የሚል ነው፡፡ ቀጣዩ የሀብት ምንጭ ማዕድን መሆኑን ተስፋ ያረገው መንግስት ነዳጅ ሊወጣ እንደሚችል አቶ መለስ በቅርቡ ፍንጭ ሰጥተዋል፡፡

ነገር ግን በቅርቡ ይህ ሊገጥመው ይችላል፤ አብዛኛው የከተማ ድሃ በምግብ እህል ላይ ባለው የዋጋ ንረት፤ ተመርቀው ስራ በማያገኙት የከተማ ወጣቶች፤ ነገሩ.... የአረቡ ዓለም መነሳሳት የኢትዮጵያውያንን ትኩረት አግኝቶ ነበር፡፡ ይህን በኢትዮጵያም መከሰቱ አይቀሬ ነዉ---ተመልከቱ!

/ሪቻርድ ዳዉደን የሮያል አፍሪካን ሶሳይቲ ዳይሬክተር ናቸው/

# የኢህአዴግ ፖለቲካና የህግ ...

ከ ገፅ 10 የዞረ....

ጠንካራ የተቀናጀ የሕግ ባለሙያና የሙያ ማህበራት እንደ ማህበርና ግለሰብ ተጠናክረው በፖለቲካው መስክ ያለመቆማቸው ነው የሚል ድምዳሜ አለኝ፡፡

ከፖለቲካ የራቁ ተምረው እንዳልተማሩ የሚሆኑ የሕግ ባለሙያዎች ከሚሊዮኖች ርሃብተኞች ከሚሊዮን እድለቢሶች ጋር ተጋፍተው ከሙስናና ከተፈጥሮ አደጋ የተረፈውን የዚችን ድሃ ሀገር ውድና ጥሪት ሃብት እምሽክ አድርገው በልተው የተማሩ የሕግ ባለሙያዎች እንደ "ክምር ፈጅ ዝንጀሮዎች" በየሰርቻው እየተንጎማለሉ የፖለቲካውን መድረክ መልቀቃቸው ለፀረ ኢህአዴግ ትግል ፍሬ አልባነት ጉልህ አስተዋፅኦ ከማድረጋቸው በተጨማሪ በራሳቸው ሀሳብ እና በተማሩት መሠረት በዳኝነት ስርዓት የራሳቸውን ውሳኔ እንዳያስተላልፉ "የመንግስት ጣልቃ ገብነት" በሰፊው እየታየባለባቸው ፍርድቤቶች አንድም የህግ ባለሙያ ከህዝብና ከጋዜጠኞች ጎን አለመቆም እንኳን ለተማረ ላልተማረውም ሰው ቢሆን የሚያሳፍር ምግባር ነው፡፡

በመሠረቱ የህግ ባለሙያዎች ቁብ ያልሰጡትን ህግ ፖለቲከኞች እነ ዶክተር መረራ፣ ዶክተር በየነ፣ እንዴት ብቻቸውን ይቻላቸዋል? የአንድ ሀገር ፖለቲካዊ ጉዳዮች የሚፃፉት የሚወጡ ሕግጋትን ተንተርሶ እንጂ ቤተመንግስት ጓሮ በሚጻፉ ልብ ወለድ አይደለም፡፡ የአቶ ግርማን አንደበት የሚሟገትበት፣ የዶክተር መረራን ዕውቀት የሚመክትበትን፣ የሚመክርበት፣ የእነ ፕሮፌሰር በየነ ወኔን የሚዋጋበት፣ የጋዜጠኞችን ስደት ለዓለም የሚያጋልጥበት እና የሚመሰክርበት የነፃውን ፕሬስ ጋዜጠኞች የተመሰገን፣ የእነ እስክንድርን ብዕር በህግ ትጥቅ እና ስንቅ የሚያጠናክር የሀገሪቱን ህግ አበጥሮ የሚያውቅ እና የሚመረምር በክፋት አቡጀዲ እና ቆዳ የተጠቀለሉትን የኢህአዴግ ህግጋት እየፈታ የዋህ ህዝባችንን ማስኮምኮም ለነፃነት ትግል የሚቆሙ በጣት የሚቆጠሩ እንኳን የህግ ባለሙያዎች በፖለቲካው ውስጥ ጠብ ካላሉ ትግሉን ከሌሊ ጎዞ እንደምን የአቦ ሸማኔ ጉዞ ልናደርገው ይቻለናል? ለማለት የፈለኩት ፖለቲከኞች እውነታውን ይዘው በወኔእና በቁርጠኝነት ሲሰለፉ ህጉ እንዲዘረጠጥ ወይም ህጉ እውነታውን እንደሚያጠፉ ወይም እንደሚንድ የትም እንደማያደርሰን እየተናሩ የፖለቲከኞችን ትግል ህጋዊ ጉልበት የሚሰጡ የህግ ባለሙያዎች ከሌሉ ትግላችን የፖለቲካ ሳይሆን የቀልድ የጨዋታ ይሆናል፡፡ ርግጥ ነው ኮተቤ ካለው ሰቪል ሠርቪስ ያልወጡ እውቅ የሕግ ባለሙያዎች አሉን፡፡ ካልሠሩበትና ሕጉ ሲጣስ ካልተሟገቱ ከንቱዎች ናቸው፡፡

ፖለቲካ ህይወትን ሊያሳጣ የሚችል ነፃ ትግል ነው ብለው የሚያስቡ የዋህ ወይም "ፈሪ የህግ ባለሙያዎች" ካሉ እነሱ ከፉኛ ተሳስተዋል፡፡ የሕግ ባለሙያዎች በሚፈለገው ልክ ወደ ፖለቲካው አለመግባት ኩራት ከሆነ በሀገር ጉዳይ አይኮራም፤ ፍርሃት ከሆነ ደግሞ ልብ እንዲሰጣቸው እንፀልይ፡፡ ለሀገር አይፈራም የሕግ ባለሙያዎች ነገሩን ወጣ ብላችሁ ብትመለከቱት እጅግ አብሻቂ ነው፡፡ ተቃዋሚዎች ኢህአዴግ ሃይሎች በግልም ወይም በድርጅትም በገጠርም በከተማም ከቤተመቅደስ ሳይቀር ከኢህአዴግ ግብግብ ገጥመው ቢታገሉም፣ ቢሰውም፣ ቢታሰሩም፣ ትግላችን እና በደላችን በዓለም ፊት ተመልካች እና ተቀባይ የማጣቱ ዋና ምክንያት የኢህአዴግ ህግ መሰል መጨቆኛ መሳሪያዎች በህግ አዋቂዎች እና ሊቃውንት ህጋዊ ትንተና አለመደገፉ ነው፤ በዚህ መቼም ይሁን መቾ ተጠያቂዎች ናችሁ፡፡ እያልኩ ከአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ለምትገኙ ኢትዮጵያውያን ውድ እና ጥቂት የህግ ባለሙያዎች ፖለቲካ እና ሀገራዊ ግዴታችሁን የምትወጡት መቼ እና እንዴት እንደሆነ ባገኛችሁት አጋጣሚ ብትነግሩን ቢያንስ አንታዘባችሁም፤ ዝምታው ይብቃችሁ፤ ሙያችሁን አክብሩ፤ አስከብሩ፡፡ ሕግ ድምጥማጡ ሲጠፋና ሲደፈጠጥ እያያችሁ ዝም ካላችሁ በምን የሞራል ብቃት የሕግ ባለሙያ ነኝ ማለት ትችላላችሁ?

# 10ሩ የድህረ-ግንቦት ...

ከ ገፅ 2 የዞረ....

በክልል አስተዳደሮች ውስጥ ጣልቃ ገብ ተሳትፎ ያላቸው፡፡ በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ በቁጥር 39 የተሰራጨው መረጃ እንዳመለከተው «ኦሮሚያ የምትተዳደረው በክልሉ ም/ቤት በተመረጡት አቶ አለማየሁ አቶምሳ ሳይሆን ከህወሓት በተመደቡት አቶ ገ/ተንሳይ ወ/ትንሳይ ነው፡፡» ይኸው መረጃ አያይዞም ቀደም ሲልም ሰለሞን ጢሞ የተባሉ የህወሓት ሰው ኦሮሚያን ከመጋረጃ ጀርባ ሆነው ያስተዳድሯት እንደ ነበር አስታውሷል፡፡ የሌሎች ክልሎች ብሄረሰቦችም ራስን በራስ የማስተዳደር ዕድል እንደሌላቸው ይነገራል፡፡

በብሄር ብሄረሰቦች ቀን ብቻ በጭፈራ የሚታየውና በስርአቱ ተቺዎች ዘንድ «የብሔር ብሄረሰቦች መብት እስከ መጨፈር» የሚል ስላቅ የሚገለፀው «እኩልነት» በፖለቲካው መድረክ አይታይም፡፡ ይህ ሁኔታ ተጨማሪ የድህረ-ግንቦት 20 ኪሳራ ሆኗል፡፡

## ፭
## ፍትሀዊ ያልሆነ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት መስፈን
## (corny capitalism)

የአቶ መለስ መንግስት በ21 አመት የስልጣን ቆይታው ሊያሳካ ካልቻላቸው መሰረታዊ የህዝብ ጥቅሞች መካከል ፍትሀዊ የኢኮኖሚ ተጠቃሚነት አለማረጋገጡ ዋንኛው ነው፡፡ መንግስት በኢኮኖሚ ውስጥ የሚያደርገው የበዛ ጣልቃ ገብነት፣ ኢትዮጵያውያን በኢኮኖሚው ውስጥ ፍትሀዊ ጥቅም እንዲያገኙ የሚያግዝ እንደሆነ ሹማምንቱ በተለያዩ መድረኮች ከመግለፅ አይታክቱም፡፡ መንግስትም የሚያንቀሳቅሳቸውን ግዙፍ ድርጅቶችም ከእጁ ለማውጣት አይፈልግም፡፡ የበታፈነ ደረጃ የተፈቀደው «የነፃ ገበያ ስርአት» ሁሉንም የንግድ ህብረተሰብ ክፍል እኩል ተጠቃሚ አላደረገም፡፡

ኢህአዴግ ራሱ ያወጣውን ህግ ተላልፎ የፈለፈላቸው፣ በቢሊየን የሚቆጠር ካፒታል የሚያንቀሳቅሱትን የገዢው ፓርቲ ንብረት የሆኑ ኩባንያዎችን በማጠናከር እንዲሁም ከመንግስቱ ጋር ቅርበት ያላቸው ግለሰቦች የተለየ ጥቅም የሚያገኙበት ሁኔታ ፈጥሯል፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎች ይህንን ስርአት ኮርኒ ካፒታሊዝም (crony capitalism) በሚል ይጠሩታል፡፡ ኮርኒ ካፒታሊዝም የሀገሪቱ ሀብት ከስርአቱ ጋር ስምም ወደ ሆኑ ጥቂት ባለፀጋ ግለሰቦች እንዲፈስ የሚያደርግ ስርአት ነው፡፡ ኢትዮጵያ እየገነባች ያለችው ኢኮኖሚም ሆነ ቁሳዊ ልማት ጥቂቶችን ብቻ ተጠቃሚ ማድረጉ የድህረ-ግንቦት 20 ኪሳራዎች መሀከል የሚጠቀስ ከመሆኑም በላይ አስተዳደሩ ለተዘፈቀበት ሙስና ምቹ ሁኔታን የፈጠረ ነው፡፡

## ፮
## የሙስና መስፋፋት

ፕሮፌሰር ሰይድ ሐሰን በኢትዮጵያ ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ ትንታኔዎችን በማቅረብ ይታወቃሉ፡፡ እኚህ ምሁር ሙስና ኢትዮጵያ ውስጥ ስር የሰደደ ስርአት እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ በቅርቡ «ሙስና ኡ! ኡ! እሪ! እሪ!» በሚል ርዕስ ባቀረቡት ጽሁፍ ዓለም ባንክ ባደረገው ጥናት ኢትዮጵያ ውስጥ ሙስና አደገኛ ስርአነት ወደ መሆን መሸጋገሩን ያብራራሉ፡፡ ፍርድ ቤት፣ ፖሊስ፣ ጉምሩክና የገቢዎች ባለስልጣን፣ የወረዳ አስተዳደርና ማዘጋጃ ቤቶች ሙስና በእጅጉ የተንሰራፋባቸው ናቸው፡፡

የህወሓት አንጋፋ መሪ የነበሩት አቶ ስብሀት ነጋም ሙስና በሀገሪቱ አደገኛ ደረጃ ላይ መገኘቱ እንዳሳሰባቸው በይፋ መግለፃቸውና አቶ መለስም የመንግስት አካላትም በአደገኛ ሙስና መዘፈቃቸውን ማመናቸው ሙስና ከድህረ-ግንቦት 20 ኪሳራዎች መሀከል የሚጠቀስ ሆኗል፡፡

## ፯
## ስርአቱን የሚተቹ አካላትን ማፈን

የህወሓት/ኢህአዴግ ታጋዮች ደርግን ከተዋጉበት ምክንያት አንዱ የደርግ ተቃውሞን የማፈን እርማጃ እንደሆነ ይናገራሉ፡፡ ታጋዮቹ ደርግን አስወግደው ሌላ «ደርግ» መተካታቸውን የሚያስረዱ በርካታ ማሳያዎች አሉ፡፡ ስርአቱን የሚተቹ አካላትን የአቶ መለስ መንግስት ማሰር የጀመረው በቅርቡ ባይሆንም፣ በአረብ ሀገራት የተከሰተውን መነሳሳት ተከትሎ የተቃውሞ ፖለቲካ አመራሮችንና ጋዜጠኞችን «በሽብር» ሰበብ ቃሊቲ አውርዷል፡፡ መንግስትን በይፋም በኢመደበኛ ወጎች መንግስትን መተቸት የሚያስጠይቅበት ደረጃ በመድረስ ላይ ይገኛል፡፡

መንግስት ስርአቱን የሚተቹ አካላትን ለማሸማቀቅ የሚጠቀምባቸው መንገዶች ሰላማዊ ትግልን የሚያደናቅፉ ከመሆናቸውም በላይ የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችን ብሶትና ተቃውሞ ወደ ግብታዊ አብዮት የመምራት ውጤትም ሊያስከትል ይችላል፡፡ በሰላማዊ ትግል ተስፋ ቆርጠው መሳሪያ ያነሱ ቡድኖችን ያበራከተው ይህ አካሄድ፣ ከኢህአዴግ ጋር ልዩነት ያላቸው የፖለቲካ ቡድኖች በሰላማዊ ትግል እንዲሳተፉ አለማበረታታቱ የአቶ መለስ ስርአት የድህረ-ግንቦት 20 ክስረት አንድ አካል ነው፡፡

## ፰
## ነፃ የሲቪክ ማህበራት አለመጠናከራቸው

ነፃ ማህበራት በአንድ ሀገር ላይ ዴሞክራሲ እንዲያብብ ትልቅ አስተዋፅኦ ያበረክታሉ፡፡ ሚካኤል ባራቶን (Michael Bratton) «CIVIL SOCIETY AND POLITICAL TRANSITION IN AFRICA» በሚል ፅሁፋቸው ከቀዝቃዛው ጦርነት መጠናቀቅ በኋላ ነፃ ማህበራት በዴሞክራሲ ግንባታ ያላቸው ሚና እየተጠናከረ እንደመጣ ያስረዳሉ፡፡ አያይዘውም ነፃ ማህበራት ይህን አበርክቷቸውን እንዲወጡ የመንግስትን ኃይል የሚዘውሩ አካላት ፈቃደኝነት አስፈላጊ መሆኑን አበክረው ይገልፃሉ፡፡ የነፃ ማህበራት አበርክቶ በኢትዮጵያ ከመዳከም አልፎ የተዳፈነ ይመስላል፡፡

ኢህአዴግ ከ1997 በፊት በአንፃራዊ መለኪያ ንቁ ተሳትፎ የነበራቸውን ማህበራት፣ ከድህረ 97 በኋላ ነፃነታቸውን የሚጋፋና ህልውናቸውን የሚፈታተን ህግ በማፅደቅ አልፈስፍሷቸዋል፡፡ የማህበራቱን ነፃነት በመጋፋት የፓርቲውን ፖለቲካ የሚያራምዱ ግለሰቦችን በአመራር ደረጃ በማስረግ ጭምር ተሳትፏቸውን አዳፍኗል፡፡

መንግስት ነፃ ማህበራት የህዝቡን ዴሞክራሲያዊ ባህልና ግንዛቤ በማዳበር የሚያበረክረቱትን አስተዋፅኦ ከማበረታታት ይልቅ፣ ከዚምባቡዌ፣ ሲንጋፖርና ሩሲያ የተወሰዱ አደገኛ ልምዶችን የቃረመ አደገኛ የበጎ አድራጎትና የሲቪክ ድርጅቶች አዋጅ አፅድቋል፡፡ በዚህ ህግ ምክንያት የመስራት አቅማቸው የተሽመደመደ እና ወደ ሌላ ዘርፍ ስራቸውን የቀየሩ ማህበራት ቁጥር በርካታ ነው፡፡

ይህ ማህበራትን የማዳከምና ነፃነታቸውን የማሳጣት ስትራቴጂ በቀጥታ የህዝቡን የነፃነት የመደራጀት መብት የሚጋፋ ከመሆኑም በላይ ዴሞክራሲ የማይዋጥላቸው አምባገነን መንግስታት ተግባር ነው፡፡ ከዚህ አንፃር 21 አመታትን በምኒሊክ ቤተመንግስት ያሳለፈው የአቶ መለስ መንግስት ነፃ ማህበራትን በስልት ማዳከሙ የድህረ-ግንቦት 20 ኪሳራዎች መካከል ይጠቀሳል፡፡

## ፱
## የነፃ ፕሬስስ ሀሳብን የመግለፅ መብት አለመከበሩ

ኢህአዴግ ወደ ስልጣን እንደወጣ ከወሰዳቸው አበረታች እርምጃዎች ውስጥ የፕሬስና ሀሳብን የመግለፅ መብትን "መፍቀዱ" ነው፡፡ መንግስት ይህ መብት ህገመንግስታዊ እንዲሆን ቢያደርግም በተግባር ግን አፋኝ እርምጃዎችን ከጅምሩ መውሰዱ ነፃ ፕሬስ እንዳይዳብር እንቅፋት ሆኗል፡፡

የአንድ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ መገለጫ የሆነው የፕሬስና ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት በኢትዮጵያ አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ መንግስት ላይ ትችት የሚያቀርቡ ጋዜጠኞች እና ሀሳባቸውን በይፋ የሚገልፁ ፖለቲከኞች መታሰር፤ ከኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ የአደባባይ ምሁራንን አርቋል፡፡

ሀሳባቸው የሚገልፁ ጋዜጠኞችና ተቺዎች ከእስር ጋር ተፋጠው ለመስራት ተገደዋል፡፡ ኢህአዴግ ያወጣቸው የፕሬስና የፀረ ሽብር አዋጆች ኢትዮጵያውያን ሀሳባቸውን በፕሬስ ውጤቶች እንዳይገልፁ የሚጠፍር ከመሆኑም በላይ በአንዳንድ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ መረጃዎችን እንዳያገኙ አግዷል፡፡ በተለይም ኢህአዴግ በቅርቡ በብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት በኩል ቅድመ ምርመራን ለመጀመር እንቅስቃሴ መጀመሩ ከላይ ያየናቸው የድህረ ግንቦት 20 ኪሳራዎች በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በሀገሪቱ የመድብለ ፓርቲ ስርዓቱ እንዲከስም አስተዋፅኦ አድርገዋል፡፡ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት እንዲያብብ በሚረዱት የፕሬስ ውጤቶች አለማደግ ብሎም መመናመን የድህረ ግንቦት 20 ኪሳራ ሌላው ማሳያ ነው፡፡

## ፲
## ሀገሪቱ በአንድ ጠቅላይ አምባገነን መሪ ስር መውደቋ

ጠቅላይ አምባገነንነት በአጭር ጊዜ የሚገነባ ሳይሆን ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ከመገንባት የበለጠ ጊዜና ወጪ ይጠይቃል፡፡ ይህን አምባገነናዊ ስርአት ለመገንባት መንግስት በህዝቡ ሁሉን አቀፍ የህይወት ፈርጅ ውስጥ ቁጥጥር ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በትምህርት ፣ በኢኮኖሚ ፣ ማህበራዊ፣ በባህልና ኪነጥበብ ውስጥ ፖለቲካዊ ቁጥጥር በማድረግ እንዲሁም ፖለቲካዊ እንነታቸውን በማጥመቅ አቶ መለስ ጠቅላይ አምባገነን መሆንን መርጠዋል፡፡

በ2002 ምርጫ 99.6 በመቶ በሆነ ውጤት ፓርላማውን የተቆጣጠረው የአቶ መለስ መንግስት አውራ ፓርቲ መሆኑን በመግለጽ የመድብለ ፓርቲ ስርዓት ተንኮታኩቶ ጠቅላይ አምባገነን ስርዓት መደላደሉን አብስሯል፡፡ ግንቦት 20 አቶ መለስን በኢትዮጵያ አንግሷል፡፡ በሀገሪቱ ላይ ብቸኛው አድራጊና ፈጣሪ አቶ መለስ ናቸው፡፡ ሙገሳቸውም ሆነ ወቀሳቸው ድጋፋቸውም ሆነ ተቃውሟቸው እንደ እግዜር ቃል ይታያል፡፡ ለግንቦት ሃያ የተከፈለው መስዋዕትነት አቶ መለስን የሀገሪቱን ቁንጮ ከማድረግ ያለፈ ውጤት ያመጣ አይመስለም፡፡ የድህረ ግንቦት 20 ኪሳራዎች የኢትዮጵያ ህዝብ ከህወሓት/ኢህአዴግ ነፃ የሚወጣውን የድል ቀን እንዲጠብቅ ሳያስገድዱት የሚቀር አይመስልም፡፡

ዜና

# መታወቂያችን አማራ ስለሚል ተመርጠን ታሰርን ሲሉ ቅሬታ አቀረቡ

ከሚዛን ተፈሪ ወደ ዲማ ለሥራ ስንሄድ ኬላ ላይ መታወቂያ እየተመለከቱ ሲፈትሹ መታወቂያችን ብሔር በሚለው ቦታ ላይ አማራ ስለሚል መርጠው እስር ቤት ከተቱን፡፡ ሲሉ ለዝግጅት ክፍላችን ገለጹ፡፡ እነዚህ እስር ቤት ቆይተን ተፈታን የሚሉ ሰዎች እንደሚሉት "ዲማ በጉልበትህ ሠርተህ የምታገኘው ገንዘብ አለ የሚል መረጃ ስለደረሰን ሥራ ፍለጋ በመጓዝ ላይ ነበርን፡፡ ሚዛን ተፈሪ ስንደርስ ለፍተሻ ከመኪና ውረዱ አሉን፡፡ ወርደን ለፍተሻ ዝግጁ ሆንን፡፡ መታወቂያቸው ኦሮሞ፣ ትግሬ፣ ጋምቤላ፣ አፋር የሚል እንዲሳፈሩ ተፈቀደላቸው፡፡ አማራ የሚለውን 16 ሰዎች ሰብስበው እናንተ እንድታልፉ አይፈቀድም ብለው ሚዛን ተፈሪ ፖሊስ መምሪያ ወሰዱን፡፡ ከዚያም እስር ቤት አስገቡን፡፡ ከዚያም ሌላ 20 አማርኛ ተናጋሪዎች ተይዘው ታሰሩ፡፡ ምን አጠፋን? ወንጀል ሳንፈጽም ለምን ታስሩናላችሁ? ብለን ስንጠይቃቸው ወደዚያ ከሄዳችሁ አደጋ ይደርስባችኋል፡፡ ወደዚያ አማራ ሄዶ እንዲሰራ አይፈቀድም ብለውናል፡፡" ሲሉ ቅሬታቸውን ይገልፃሉ፡፡

"ትኬት ቆርጣችሁ ወደ አማራ ክልል ተመለሱ ብለው ከሦስት ቀን በኋላ የተወሰነን ሰዎችን ለቀቁን፡፡ ብዙዎቹ አሁንም በእስር ላይ ናቸው፡፡ እኛ ወደ ትውልድ መንደራችን ለመሄድ ገንዘባችንን ጨርሰናል፡፡ ብንሄድም ቦታ ስለሌለን ማረፊያ የለንም፡፡ ለዚህ ነው የቀን ሥራ ሠርተንም ጉርጓድ ቆፍረንም ህይወታችንን እንቀይራለን ብለን ጉዞ ጀምረን የነበረው፡፡ ሆኖም ግን አማራ በመሆናችን ተዘዋውረን ሠርተን እንዳንበላ ተደርገናል፡፡" ሲሉ አማረዋል፡፡

በመቀጠልም ሲናገሩ "እኛ ታስረን መፈታት ችለናል፡፡ ዛሬም ሥራ ፍለጋ ወደ ምንፈልግበት እንድንሄድና በነፃነት ከቦታ ቦታ እንድንቀሳቀስ አልተፈቀደልንም፡፡ ህጋዊን መንገድ ትተው በእግራቸው ጫካ ለጫካ ጉዞ የጀመሩ በርካታ ሰዎች ተገላዋል፡፡ በአውሬ ተበልተዋል፡፡ ሲገደሉም በአውሬ ሲበሉም የአካባቢው ኃላፊዎች ምንም የሚሰማቸው ፀፀት የለም፡፡ ህገ ወጦች ናቸው፡፡ እንኳን ሞቱ እንኳን ተበሉ እያሉ ሲሳለቁ ይሰማል፡፡" ካሉ በኋላ "የሚመለከተው የመንግስት አካል ጉዳዩን በጥሞና ተመልክቶ ውሳኔ ይሰጠን፡፡ ተዘዋውረን የመኖርና ሠርቶ የመብላት መብታችን እንዲከበርልን አሳውቁልን፡፡" በማለት ጥሪያቸውን አቅርበዋል፡፡ የሚዛን ተፈሪ ፖሊስ መምሪያ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲሰጥበት ያደረግነው ጥረት አልተሳካም፡፡

# በአዲስ አበባ የውሃ ችግር ተባብሷል

በአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር የመጠጥ ውሃ ችግር መባባሱ ተገለፀ፡፡ የውሃ አገልግሎት በአንዳንድ ቦታዎች ከ15 ቀናት እስከ አንድ ወር ድረስ የተቋረጠ መሆኑን ነዋሪዎች ተናግረዋል፡፡

በተለይ የውሃ ችግር ከታየባቸው መካከል ንፋስ ስልክ ላፍቶ፣ አቃቂ ቃሊቲ፣ ኮልፌ ቀራንዮ፣ የካ እና በከፊል አራዳ ክ/ከተሞች ዋነኞቹ እንደሆኑ ተጠቁሟል፡፡

የፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ዝግጅት ክፍልም ስለጉዳዩ ለማጣራት በተለያዩ የአዲስ አበባ አካባቢዎች የተንቀሳቀሰ ሲሆን ከላይ በተጠቀሱ ክፍለ ከተሞች በሚገኙ አንዳንድ አካባቢዎች የአካባቢው ነዋሪ ውሃ ፍለጋ በብዛት ጀሪካን ይዘው በስፋት ሲንቀሳቀሱ ለማየት ተችሏል፡፡

ችግሩ እስከመቼ እንደሚቀጥልና ይህ የመጠጥ ውሃ ችግር ለምን እንደተፈጠረ አሁን በምን ዓይነት ሁኔታ ላይ እንዳለ መልስ እንዲሰጡን የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ውሃ ልማት ኤጀንሲን አነጋግረናል፡፡

የኤጀንሲው የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ የሁኑት አቶ ሱሌይማን በበኩላቸው "የውሃ ችግሩ ለ3 እና 4 ቀናት መፈጠሩን እናውቃለን፣ ችግሩ የተፈጠረው ግን አቃቂ ቃሊቲ ባለው ማሰራጫ በተፈጠረ የመብራት ችግር ሲሆን በአሁን ወቅት ሙሉ ለሙሉ ተቀርፏል፡፡" ብለዋል፡፡ አያይዘውም ምንም እንኳ በእኛ በኩል የነበረው ችግር ቢፈታም ወደ ህዝቡ በአግባቡ ለመድረስ ግን ጊዜ እንደሚያስፈልግ በተለይ ለዝግጅት ክፍላችን ገልፀዋል፡፡

# ማስታወቂያ

አንድነት ፓርቲውን ለማጠናከር የገቢ ማሰባሰቢያ ፕሮግራም የራት ግብዣ ለግንቦት 25 ቀን ማዘጋጀቱንና ዝግጅቱ የሚካሄድበትን የሆቴሉን ስም በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ግንቦት 14 ቀን ታትሞ በሚወጣው ለማሳወቅ ቃል ገብቶ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በሆቴሎች የፕሮግራም መጨናነቅ ምክንያት የራት ግብዣው ቀን ለሐምሌ 28 ቀን 2004 ዓ.ም መራዘሙን ከታላቅ ይቅርታ ጋር እየገለጽን የሆቴሉን ስምና አድራሻ ከዚያ ወዲህ በፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ የምናሳውቅ መሆናችንን በአክብሮት እንገልፃለን፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ

# የቀበሌውን መዝናኛው ለማሸግ የተደረገው ሙከራ በሠራተኛው ተቃውሞ ተደናቀፈ

በአራዳ ክፍለ ከተማ ወረዳ 6 በቀድሞ ቀበሌ 12 የህዝብ መዝናኛ ክበብ አካባቢው ለባለሀብት ተሸጧል ተብሎ ድርጅቱን ለማሸግ የተደረገው ሙከራ ሠራተኛው ከፍተኛ ተቃውሞ በመፍጠሩ መቋረጡን ሪፖርተሮቻችን ከሥፍራው ዘግበዋል፡፡ ሠራተኞቹ ክበቡ መታሸግ የለበትም ብለው በለቅሶና በዋይታ ድርጊቱን ሲከላከሉ ታይቷል፡፡

የክበቡን ሠራተኞች ማህበር ተወካይን አነጋግረን በሰጡን መልስ "ቦታው ተሰጠ የሚባለው አልሚአሌንዶ ለተባለ ኮንስትራክሽን ድርጅት ነው፡፡ ድርጅቱ በጨረታ ተወዳድሮ አሸንፎ ነበር የተባለው ስታዲዮም አካባቢ ነው፡፡ ቦታው ለሌላ ስለተፈለገ በልዋጭ ይህ የምንሠራበት ክበብ እንዲሰጠው ተወሰነ ይሉናል፡፡ እኛ ደግሞ ቀደም ሲል ለማልማት እንዲፈቀድልን ጠይቀናል፡፡ የድርጅቱ ሠራተኞች 83 ነን፡፡ በሥራችን ከ500 ሰው በላይ አለ፡፡ ከምንሠራበት ድርጅት ጀርባና ጐን ከተፈቀደው ቦታ በላይ ባዶ መሬት አለ፡፡ ይህንን እኛ ጠይቀነው ለመልሶ ማልማት የያዝነው ቦታ ነው፡፡ ባዶ ቦታውን ለምን አትሰጧቸውም ብለን አመልክተን ተነጋግረን እንነግራችኋለን ብለው መልስ ሰጡን፡፡ በዚህ ላይ እያለ በድንገት ዛሬ መጥተው እናሽግ አሉን መንግስት ዜጐችን ከየጐዳናው እየሰበሰበ ለሥራ በሚያደራጅበት ወቅት እኛን ለጐዳና ለምን እንዳረጋለን፡፡ ይህንን ተቃውመን ነው፡፡ ድርጊቱን የምናወግዘው፡፡" ብለውናል፡፡

ሌላው የክበቡ የሒሳብ ሠራተኛ ነች ያለችን የድርጅቱ ሠራተኛ እንዳለቺው "እና የአካባቢው የግንባታ ደረጃ ለመገንባት አቅም አለን፡፡ እንደዜጋ የምንሠራበት ቦታ ለማልማት ቅድሚያ ሊሰጠን ይገባል፡፡ ውሳኔ የሚሰጡ ኃላፊዎች ሊያደምጡን ይገባል፡፡ የሠራተኛውን መብትና ጥቅም እንደተራ ነገር ለመንጠቅ መንቀሳቀስ የለባቸውም፡፡ ፖሊስና ጥበቃን ሰብስቦ ለማሸግ መሞከር ተገቢ አይደለም ስትል" ሐሳቧን ሰጥተዋል፡፡

"28 ዓመት በዚህ ክበብ አገልግያለሁ" ያሉ አንድ የዕድሜ ባለፀጋ እንባቸውን እየዘሩ ድርጊቱን አምርረው አውግዘዋል፡፡ ሠራተኛዋ እንዳሉት "ጊዜን ጉልበቴን የጨረስኩት እዚህ ክበብ ውስጥ ነው፡፡ አቅሜ በደከመበት ወቅት አውጥተው ሜዳ ላይ ሊጥሉን ነው፡፡ በዚህ ዕድሜዬ ጐዳና ልወጣ ነው፡፡ መንግስት ባለበት አገር እንዴት ሰሚ እናጣለን፡፡ መለስ ዜናዊ ሠርቶ የሚያበላን ደሃን እያወጣችሁ ሜዳ ላይ ወርውሩ ብሏቸዋል?" ሲሉ በለቅሶ ሲናገሩ በዙሪያቸው የተሰበሰቡት በጠቅላላ "ይህ ክበብ ህይወታችን ነው፡፡ ክበቡ ከተዘጋ ቤተሰባችን ይበተናል፡፡ እባካችሁ በደሃ እንባ ኪሳቸውን የሚያደልቡ የወረዳና የክፍለ ከተማ ኃላፊዎችን መንግስት እንዲያቸው አድርጉልን፡፡ እኛ ልማትን አንቃወምም፡፡ ልማቱን ለማልማት እየጠየቅን ነው፡፡ እኛ እየተቃወምን ያለነው በልማት ስም የግል ጥቅማቸውን የሚያሳድዱትን ነው፡፡ በልማት ስም ህዝብ ላይ ግፍ እየተፈፀመ ነው፡፡ ጩኸታችንን የምናሰማበት ቦታም የለም" ብለዋል፡፡

በሥፍራው የነበሩ የወረዳው ኃላፊዎች ሐሳብ እንዲሰጡበት ብንሞክርም መታወቂያችን ከተመለከቱ በኃላ የጋዜጣችሁን ፍቃዱ አሳዩን፡፡ በከተማ ውስጥ እየተዘዋወርክ ዜና እንድትሰራ የተፈቀደልህን ደብዳቤ አምጣ የሚልና ወከባ ለመፍጠር ሞክረዋል፡፡ የወረዳው መስተዳድር በጉዳይ ላይ አስተያየት ለመስጠት ቢፈልግም ዛሬም መድረኩ ክፍት መሆኑን ዝግጅት ክፍሉ በዚህ አጋጣሚ መግለጽ ይወዳል፡፡


አንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ
(አንድነት)

## የገቢ ማሰባሰቢያ የራት ፕሮግራም

አንድነት ፓርቲ የኢትዮጵያ ህዝብ የስልጣኑ ባለቤት እንዲሆን ለማድረግ በቁርጠኝነት እየታገለ ይገኛል፡፡ ለትግሉ ስኬት የርሶ ድጋፍ ወሳኝ ነዉ፡፡

የአንድነት ፓርቲ የፋይናንስ ቋሚ ኮሚቴ የራት ዝግጅት ፕሮግራም አዘጋጅቷል፡፡ መግቢያ ባለ 1,000፣ 500ና 300 ብር መግቢያ ካርዶች ተዘጋጅተዋል፡፡

በራት ፕሮግራሙ ላይ ታዋቂ ግለሰቦች ንግግር ያደርጋሉ፡፡ የራት ግብዣዉ ሐምሌ 28 ቀን 2004 ዓ.ም ይደረጋል፡፡ የሆቴሉ ስም ሐምሌ 24 በሚወጣዉ ፍኖተ ነፃነት ጋዜጣ ላይ ይገለፃል፡፡

በዉጭ ሀገር የምትኖሩ ኢትዮጵያዉያን በሚኖሩ ቤተሰቦችና ጓደኞች ካርዱን መግዛት ትችላላችሁ፡፡

ለተጨማሪ መረጃና ካርድ ለመግዛት
በሚከተለዉ አድራሻ ይጠቀሙ፡-

በቢሮ ስልክ ቁጥር፡- 01 18 40 08 11

ሞባይል 09 11 61 84 34

ኢ-ሜይል

andinetfinance@yahoo.com

andinet@ andinet.org

የአንድነት ለዴሞክራሲና ለፍትህ ፓርቲ
(አንድነት)

ንብ ባንክ ዑራኤል ቅርንጫፍ

የሂሳብ ቁጥር 510

ለዴሞክራሲ ስርዓትና ለህግ የበላይነት ሁላችንም ካርዱን በመግዛት ድርሻችንን እንወጣ!